# የሕይወት ታሪኬ

እንገታችንን ዝቅ አድርገን ለአፍታ እንጸልይ።

ቸር የሰማይ አባት ሆይ፡ አምላክ እና አዳኛችን ወደሆንከው ወደ አንተ መቅረባችን፡ በእውነት መታደል ነው። **እንዴት ድንቅ ነህ፡** የሚለውን ይህ ድንቅ መዝሙር ሰንሰማ፡ አንተ ታላቅ እንደሆንክ ስለምናውቅ ደስ ይለናል። ዛሬ ከሰአት በኋላም፡ ሰንናገር፡ ታላቅነትህ በአዲስ መልክ እንዲገለጥልን ጸሎታችን ነው። ከብዙ ዘመን በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ወደ ቀድሞ ህይወት ታሪክ ለመዳሰስ፡ ዕጣዬ ሆኖልኛልና፡ በዚህ ጊዜ፡ ጌታ ሆይ፡ የሚያስፈልገኝን ሁሉ እና—ብርታትን እንድትሰጠኝ እጸልያለሁ። በህይወቴ የተሳሳትኳቸው ስህተቶቼ ሁሉ ለሌሎች ወደ አንተ መቅረቢያ፡ እንደ መረጋገጫ-ድንጋይ ይሁኑ። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። ኃጢአተኞች በዘመን አሸዋ ላይ የተሳለ የእግር ኮቴ አይተው፡ ወደ አንተ ይመሩ። እነዚህን ነገሮች በጌታ በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። ኣሜን።

አረፍ አረፍ በሉ።

2 [ወንድም ግሎቨር መጥቶ፡- "ከመጀመርህ በፊት ለእነዚህ መሃረብ ትጸልያለህ? በማለት ተናገረ"—እርታዒ።] እሺ፡ ጌታዬ፡ አመሰግናለሁ። ደስ ይለኛል። ["የሚጸለይላቸው **እነዚህ** እና **እነዚያ** አሉ።"] ወንድም ግሎቨር፡ ለተወሰኑ ዓመታት የማውቀው፡ ቅዱስ ሰው ነው፡ ትላንት ምሽት አብረን ጥቂት ጊዜ አሳልፈናል። ለተወሰነ ጊዜ፡ እርፎ እንደነበረ... ነግሮኛል። አሁን ግን፡ በሰባ-አምስተኛው አመቱ፡ ጌታን ወደ ማገልገል ተመልሷል። ደክሜአለሁ ብዬ አስቤ ነበር፡ አሁን ግን—ደክሜአለሁ ብዬ አላምንም። ይሄን ከሰማሁ በኋላ የድካሜን ግማሽ ያህል እንኳን አይደክመኝም። አንዳንድ መሀረቦችን፡ በፖስታዎችና—በልዩ ልዩ መልክ፡ ከፊቴ አቅርበውልኛል፡ ውስጥ ታጭቀው ሞልተዋል።

3 አሁን፡ እዚህ ሆናችሁ፡ ወይም በራዲዮ ውስጥ የምትከታተሉን፡ ከእነዚህ መሀረቦች ውስጥ አንዱን የምትመኙ ሁላችሁ፡ እንዲህ አድርጉ... የኤንግለስ ቤተ መቅደስ ያለማቋረጥ፡ ሁል ጊዜ ይልካቸዋል። እናንተም ወደ ኤንግለስ ቤተ መቅደስ ብትጽፉላቸው ይጸልዩበታል፡ የእግዚአብሄር ቃል እንደሆነ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። የእግዚአብሄር ቃል ኪዳን ነውና።

4 እናንተ እኔ እንድጸልይላችሁ ከፈለጋችሁ ግን፡ እንዴታ፡ ደስ እያለኝ እጸልያለሁ። በፖስታ ሣጥን ቁጥር 3-2-5፣ 325፣ ጄፈርሰንቪል፣ በፊደል ጂ-ኢ-ኤፍ-ኤፍ-ኢ-አር-ኤስ-ኦ-ኤን-ቪ-አይ፡ ድርብ ኤል፡ እና ኢ። ጄፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና። ወይም ስለ ፖስታ ቤት ሳጥኑ መያዝ ካልቻላችሁ፡ "ጀፈርሰንቪል" ብላችሁ ብቻ ጻፉልን። ሠላሳ-አምስት ሺህ ያህል ሕዝብ የሚኖርባት ትንሽ ከተማ ነች። ሁሉም ሰው ያውቀኛል። መሀረብ ላይ ጸልየን ሰንልክላችሁ ደስ ይለናል።

5 እና፡ አሁን፡ ይህን በማድረግ ትልቅ ስኬት አግኝተናል፡ ምክንያቱ... የምትሞሉት አባሪ ቅጽ አብሮ ይላክላችኋልና፡ ይህም የሚጸልዩ ሰዎች በመላ ዓለም ዘወትር ጠዋት ዘጠኝ ሰዓት ላይ፣ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ፣ እና

ሶስት ሰዓት ላይ የሚጸልዩ መኖራቸው ነው። እናም ይህን ጸሎት ለማድረግ በመላው ዓለም ሰዎች በየትኛው ሰዓት እንደሚነሱ መገመት ይቻላል። ስለዚህ እነዚህን የሚያክሉ በሺዎች የተባዙ፡ አስር ሺዎች፡ ስለ ጤናችሁ እና፡ ስለዚህ አገልግሎት፡ ጸሎታቸውን በእግዚአብሄር ፊት አንድ ላይ ያቀርባሉ፡ እግዚአብሄርም ችላ አይለውም። እና አሁን እኛ፡ እንደነገርኳችሁ፡ አንዲት ሳንቲም ወይም ገንዘብ ለመልቀም፡ ምንም አይነት ፕሮግራም የለንም። እኛ ብቻ... እናንተን መርዳት ከቻልን፡ ለዚያ ነው የመጣነው። እና እስቲ...

ሌላም ሰውን ተጨማሪ መሀረቦች እያመጣ ነው።

6 አሁን፡ መላክ የምትፈልጉት መሀረብ ከሌላችሁ፡ አትጨነቁ፡ ዝም ብላችሁ፡ ደብዳቤ ጻፉልን። አሁን ካልፈለጋችሁት፡ መጽሐፍ ቅዱሳችሁ ውስጥ፡ በሐዋርያት ስራ መጽሐፍ፡ 19ኛው ምዕራፍ ላይ አስቀምጡት። አነስ ያለች ነጭ ሪባን፡ እንዴት ቀድማችሁ ንስሓ እንደምትገቡ የሚያስረዳ መመርያ አብሮ እንልክላችኋለን። (አመሰግናለሁ) እና እንዴት ንስሓ እንደምትገቡ። መጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ትክክል ሳትሆኑ ከእግዚአብሔር ምንም ነገር ለማግኘት በፍጹም መሞከር የለባችሁም። ግልጽ ነው? እና ጎረቤቶቻችሁን እና ፓስተራችሁን እንድትጠሩ፡ መመርያው ላይ አለ። በልባችሁ ውስጥ የያዛችሁበት ማንም ቢኖር፡ ሄዳችሁ አስተካክሉ፡ ከዚያ በኋላ ተመለሱ። ከዚያ ጸልዩ፡ በቤት ውስጥ የጸሎት ጊዜ ይኑራችሁ፡ መሀረቡም ከውስጥ ልብስ ላይ ሰክታችሁ፡ እግዚአብሄርን እመኑ። እና በእነዚያ ሦስት ሰዓታት ውስጥ፡ በመላው አለም ውስጥ፡ በየቀኑ፡ ሰንሰለታዊ ጸሎት የሚጸልዩ ሰዎች፡ በአለም ዙሪያ አሉ።

7 እና አሁንም የእናንተ ነው፡ ፍፁም በነፃ ነው፡ ዝም ብላችሁ ላኩልን። እና—እና፡ አሁን፡ እናንተን ለማታለል ወይም ያለንን ፕሮግራም ልንነግራችሁ መልስን አንጽፍላችሁም። ፕሮግራሙን እንድትደግፉ እንፈልጋለን፡ እኛ ግን—እናንተን የምንደግፍበት ድጋፍ የለንም። አያችሁ? ስለዚህ... አድራሻችሁን ለማግኘት አይደለም፡ ማስፋፋት የምንፈልገው፡ የጌታን አገልግሎት እና ስራን ነው።

8 አሁን አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። እና በሬዲዮ ለምትከታተሉን፡ መሀረባችሁን ከፊታችሁ አርጉት፡ በምንጸልይበት ጊዜ እጃችሁን ጫኑበት።

9 ጌታ ሆይ፡ እነዚህን ትናንሽ እሽጎችን በፊትህ እናቀርባቸዋለን፡ ምናልባት አንዳንዶቹ ምናልባት ትንንሽ የህጻን ልጅ ልብሶች፡ ወይም—ወይም ካናቲራ፡ ወይም ትንንሽ ጥንድ ቡቲ ጫማዎች፡ ወይም—ወይም፡ ለታማሚዎች እና ለተጎዱ ሰዎች የሚላኩ መሀረብ የመሳሰሉ ናቸው። ጌታ ሆይ፡ እኛ ይህን እንደ ቃልህ እናደርገዋለን። ከባሪያህ ከጳውሎስ አካል፡ መሀረብና የልብስ ቁራጭ፡ ይወሰዱ እንደነበር፡ በሐዋርያት ሥራ መጽሀፍ፡ እናነባለንና፡ ይህም መንፈስህ በዚያ ሰው መኖሩን ስላመኑ ነው። በዚያም ርኩሳን መናፍስትም ከሰዎች ይወጡ ነበር፡ ስላመኑም፡ መከራና ደዌ ይተዉአቸው ነበር። አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ቅዱስ ጳውሎስ አለመሆናችንን ይገባናል፡ አንተ ግን አሁንም ያው ኢየሱስ እንደሆንክ እናውቃለን። ስለሆነም ደግሞ የእነዚህን ሰዎች እምነት እንድታከብርላቸው እንጸልያለን።

10 እንደሚባለውም እስራኤል፡ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በሞከሩ ጊዜ፡ ወጥመድ ውስጥ ተይዘው እንደነበሩ ይነገራል፡ ባሕር በፊታቸው፣ ተራሮች

በኅናቸው፣ የፈርዖንም ሠራዊትም እየቀረበ መጣባቸው። አንዱ ሲናገርም፡ እንዲህ አለ፦ "እግዚአብሄርም በእሳቱ አምድ ውስጥ አልፎ በቁጣ አየ፡ ባሕር ደንግጦ በራሱ ወደ ኋላው ሸሸ፡ ለእስራኤልም ወደ ተስፋይቱ ምድር መንገድ አበጀ ብሎ ተናግሯል።"

11 ጌታ ሆይ፣ ስለ ሕያው ቃልህ ክብር እነዚህ እሽጎች በታመሙ አካላት ላይ ሲያርፉ፡ አሁንም እየን። ለዚህ ስርየት ስለ ሞተው፡ ስለ ልጅህ ኢየሱስ ደም፡ አልፈህ ተመልከት፡ እና በሽታዎች ሁሉ ይደንግጡ። እነዚህ ሰዎችም ወደ ተስፋው ቃል ይገቡ ዘንድ፡ ጠላት ደንግጦ ይራቅ፡ ይህም "ከምንም በላይ፡" "እኛ በጤና እንኖር ዘንድ፡" መሻትህ ነውና። አባት ሆይ፡ እንዲህ ያሉ አመለካከት በልባችን አዝለን፡ እነዚህን እንልካለንና—ልመናችንን ፈጽምልን። ግባችንም ይህ ነው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንልካለን። አሜን።

እናመሰግናለን፡ ወንድም ግሎቨር። አመሰግናለሁ፡ ጌታዬ።

12 አሁን፡ ዛሬ ማታ የዚህ የሪቫይቫል ክፍል መዝጊያ በመሆኑ፡ ስርጭት መኖሩን አላመኖሩን ባላውቅም፡ (ካልሆነም) ለብዙ ብዙ ዓመታት ካደረግኳቸው ጉባኤዎች፡ መካከል ይሄኛው እጅግ ደስ የሚል እንደነበረ በሬድዮ ለሚያዳምጡ ሰዎች መናገር እፈልጋለሁ። ከረጅም ጊዜ በኋላ፣ ጤናማ፣ እጅግ ተወዳጅ፣ ትብብር ያለው ስብሰባ አካሂጃለሁ።

13 [አንድ ወንድም፦ "እስከ አራት ከሩብ ድረስ በራድዮ ላይ እንቆያለን፡ ወንድሜ።።። በደቡብ ካሊፎርኒያ፣ በዙርያ ባሉ ደሴቶች ሁሉ፡ እና በመርከቦች ውስጥ፡ ብዙዎች ያደምጡሃል። መልዕክቶችን እያደረሱን ይገኛሉ። እጅግ ብዙ አድማጭ አለ፡ ሺ ጊዜ አስር ሺዎች ያደምጡሃል አለው።"—አርታዒ] አመሰግናለሁ ጌታዬ። በጣም ጥሩ። ይሄን መስማቴ ደስትኛ ነኝ። እግዚአብሔር ሁላችሁንም ይባርካችሁ።

14 በእውነት ኤንገለስ ቤተ መቅደስ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ባላቸው ጽናት፡ ሁሌም ቢሆን በልቤ ውስጥ ልዩ ቦታ አላቸው። አሁን፡ ደግሞ፡ የባሰውን—የራሴ እስኪመስለኝ ሆኗል። እያንዳንዳቸው በአካል አግኝቼ፡ መልካሙን ፍሬአቸውን ካየሁ በኋላ፡ ከእናንተ ጋር እንደ አንዱ መሆኔን ከፊት ይልቅ ይሰማኛል። ጸሎቴ፡ እግዚአብሄር ይባርካችሁ ነው። እ… [ጉባኤው ዕልል አለ—አርታዒ።] አመሰግናለሁ፡ ክብር ይስጥልኝ።

15 አሁን፡ ዛሬ ከእናንተ ጋር **የሕይወት ታሪኬን** በጥቂቱም ቢሆን እንድናገራችሁ ተሰጥቶኛል። ይሄን ከብዙ ዓመታት በኋላ እንደገና እንድናገረው የምሞክረው ገና ዛሬ ነው። ለእኔም እጅጉን—ከባዱ ነገር ይህ ነው። ዘልቄ ለመዘርዘር ጊዜ ስለማይኖረኝ፡ እንዳንዱን ብቻ አጫውታችኋለሁ። በእነዚያም፡ ብዙ ስሕተት ሰርቻለሁ፡ ብዙ የተሳሳቱ ነገሮችን፡ አድርጌአለሁ። ለእናንተም፡ በራድዮ እና በአካል እዚህ ላላችሁ ሁሉ ጸሎቴ፡ ስሕተቴ ሁሉ ወደ ጌታ ኢየሱስ እንዲያቀርባችሁ መረጋገጫ-ድንጋይ ይሁናችሁ እንጂ፡ የመሰናከያ-ድንጋይ እንዳይሆን ነው።

16 ከዚያም፡ ዛሬ ምሽት፡ የጸሎት ካርዶች ዛሬ ምሽት ለፈውስ አገልግሎት ይሰጣሉ። አሁን፡ ስለ **ፈውስ አገልግሎት** ስንናገር፡ አንድን ሰው እንፈውሳለን ማለት አይደለም፡ "ለአንድ ሰው" እንጸልያለን ማለታችን ነው። የሚፈውስ እግዚአብሄር ነው። ለእኔ ግን ጸሎቴን በመመለስ፡ ምሕረቱ አግኖልኛል።

17 እዚህ የሆነ ጊዜ ላይ፡ ከአንድ እጅግ ታዋቂ የወንጌል ስራ ማናጀር ጋር ተነጋግሬ፡ እና—እና ይሄኛው ወንጌላዊ ለበሽተኞች ለምን አትጸልይም ተብሎ ተጠይቆ ነበር። ይህ ወንጌላዊ በመለኰታዊ ፈውስ ያምናል። ወንጌላዊውም ለጉባኤዎች—ማኔጀራችንን መለሰለት፡ እንዲህ አለው፦ "ከጸለይኩ… " ጉባኤዎቼ በአብያተ ክርስትያናት ስፖንሰር የተደረጉ ስለሆኑ፡ ለታመሙ ሰዎች መጸለይ ከጀመርኩ ያቆሙኛል አለው። ምክንያቱ ብዙ አብያተ ክርስትያናት፡ አብዛኛዎቹ፡ በመለኰታዊ ፈውስ አያምኑም።

18 ስለዚህ ቦታውን እና ኃላፊነቱን ስለጠበቀ፡ ለወንጌላዊው አክብሮት እና ክብር አለኝ። እሱ ምናልባት… እኔ የእሱን ቦታ በፍፁም መውሰድ አልችልም፡ እሱም የእኔን ቦታ ሊወስድ እንደማይችል አምናለሁ። ሁላችንም በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ቦታ አለን። ሁላችንም አንድ ላይ ነን። ልዩ ልዩ ስጦታዎች፡ መንፈሱ ግን አንድ ነው። ማለት የፈለግኩት፡ ልዩ ልዩ መገለጫዎች፡ መንፈስ ግን አንድ ነው።

19 አሁንም፡ ጉባኤዎቹ፡ ዛሬ ማታ ይጀምራሉ… ኮንሰርቱ ሰድሰት-ተኩል ይጀምራል ያሉ ይመስለኛል። አሁንም፡ በራድዮ ስርጭት እያደመጣችሁ ያላችሁ ይሄን ሰሙት። እጅግ… ድንቅ ይሆናል፡ ሁሌም ድንቅ ነው።

20 ሌላው መናገር የምፈልገው ከጉባኤው በኋላ ልክ ጉባኤው እስኪጠናቀቅ ከቆያችሁ፡ እና የጸሎት ካርድ ከፈለጋችሁ፡ የጸሎት ካርዶች ወዲያውኑ ይሰጣል። ከአፍታ በፊት ማሳሰብያው ደርሶኛል፡ ልጄ ወይም አቶ/ ሜርሴር ወይም አቶ/ ጓድ፡ የጸሎት ካርዶችን ይሰጣሉ። በየወንበሮቻችሁ ቁጭ በሉ። ጉባኤው እንደተጠናቀቀ፡ ሰዎቹ መጥተው የጸሎት ካርዶችን በተቻለ ፍጥነት በየመሰመሩ ማደል እንዲችሉ በያላችሁበት በየወንበራችሁ ቁጭ በሉ። በበረንዳውም ይሁን በወለሉ፡ የትም ይሁን፡ በታችኛውም ወለል ወይም በሌላ ብትሆኑ፡ የጸሎት ካርድ መፈለጋችሁ ሰዎቹ እራሳቸው ስለሚያውቁ በየወንበሮቻችሁ ቁጭ ብላችሁ ጠብቁ። ስለዚህ ዛሬ ማታ ለታመሙ ሰዎች እንጸልያለን። ጌታ ሀሳቤን ካልቀየረ በቀር ዛሬ ማታ፡ **አብን አሳየን እና ይበቃናል፡** በሚል ርዕስ ጉዳይ መሰበክ ፈልጌአለሁ።

21 አሁን የከሰዓቱ **የሕይወት ታሪክ** ለመጀመር ያክል፡ መነሻ የሚሆነን ቃል እናንብብ፡ ዕብራውያን መጽሐፍ ምዕራፍ 13፡ ከሚገኘው፡ ምናልባት እስኪ… ከቁጥር 12 ጀምረን እናነባለን።

> **ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ።**
>
> **እንግዲህ… ነቀፌታውን እየተሸከምን፡** ወደ **እርሱ ወደ ሰፈሩ ውጭ እንውጣ።**
>
> **በዚህ የምትኖር ከተማ** የለችንምና፡ **ነገር ግን ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን።**

22 ይሄ እንደ መነሻ ቃል ነው። ምክንያቱ፡ አያችሁ፡ የሕይወት ታሪክ፡ ወይም ስለ ሰው የሚነገሩ ነግሮችን፡ ምንም ይሁኑ፡ በተለይም—እንደ እኔ ዓይነት፡ የጨለመ ታሪክ ያለው ሲሆን አናንቆለጳጵሰም። እንደሚመስለኝ ግን፡ ቅዱስ ቃል ካነበብን፡ እግዚአብሄር ቃሉን ይባርክልናል። ስለዚህ ሐሳቤ፤

**በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና፡ ነገር ግን ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን** ይሆናል።

23 አሁን፡ ሎስ አንጀለስን በጣም እንደምትወዷት አውቃለሁ። የመውደድ መብትም አላችሁ። ድንቅ እና፡ ቆንጆ ከተማ ነች። ጭጋግ እና ሌላ-ነገር ቢኖራትም፡ መልካም የአየር ጠባይ ያላት፡ ውብ ከተማ ናት። ከተማዋ ግን ለዘላለም አትኖርም፡ ፍጻሜዋ ይመጣል።

24 (ታላላቅ ነገስታቶቿ) ለዘለአለም አትጠፋም ብለው የገነቧትን የሮም ከተማ ገብቼባታለሁ፡ ፍርስራሾቿን ለማየት ሃያ ጫማ ያህል ወደ ታች ተቆፍራ ወጥታለች።

25 ፎርኦኖች ታላላቅ መንግስታቶቻቸውን ያቆሙባት ስፍራም ገብቼባታለሁ፡ ታላላቅ ፎርኦኖች የመሩባት ስፍራ ለማግኘት እጅግ መቆፈር ይጠበቅባችኋል።

26 እኛም ስለ ከተማችን እና መንደራችን ማሰብ እንወዳለን። ይሁን እንጂ፡ እንደማይጸኑ፡ አስታውሱ።

27 በእኛ አገር ብዙ ጠንካራ ዛፎች አሉ። እና ህጻን እያለሁ ማፕል ወደ ተባለው ዛፍ ዘወትር እሄድ ነበር። ያኔ ይህ ማፕል የተባለው ዛፍ፡ ሹገር ማፕል እና ማን ነው "ሃርድ ማፕል" እና "ሶፍት ማፕል፡" የተባሉ ዛፎች ነበሩን። ይህ እጅግ ግዙፍ ዛፍ፡ ልዩ ውበት የነበረው ዛፍ ነበር። በሳር እርሻ ስራ፡ እና—በአጨዳ ውዬ በመጣሁ ቁጥር፡ ወደዚህ ትልቅ ዛፍ ስር መጥቼ—ወደ ላይ እያየሁ—ቁጭ ማለት እውድ ነበር። በዚያም ታላላቅ ቅርንጫፎቹ፣ እና ትልልቅ ግንዶቹ፣ በንፋስ ሲወዛወዝ አይ ነበር። እና እኔም፡- "እየህ፡ ይህ ዛፍ ለብዙ መቶዎች እና መቶዎች ዓመታት እንደሚኖር አምናለሁ እል ነበር።" በቅርብ ጊዜ እነዚያ ጥንታውያን ዛፎች ጎበኘኋቸው፡ ባዶ ቀርቷል።

28 "በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና።" በምድር የምታዩት ነገር ሁሉ፡ በፍጹም አይቀጥልም። መጨረሻ አለው። ሟች የሆነ ነገር ሁሉ ለማይሞተው መንገድ መልቀቅ አለበት። ስለዚህ ምንም ያክል አውራ ጎዳናዎች ብንገነባ፡ ምንም ያህል ህንጻዎች ብናሳምር፡ መጥፋቱ አይቀርም። በዚህ ቀጣይነት ያለው አንድም ነገር የለምና። የማይታየው ግን ለዘለአለም ይኖራል።

29 ያደግንባት ቤት ትዝ ትለኛለች፡ በጭቃ የተመረገች ያረጀች የዛፍ ቤት ነበረች። እንደው... ምናልባት ብዙዎቻችሁ በጭቃ የተመረገ ቤት አላያችሁም ይሆናል። ይሁን እንጂ በጭቃ ተመርጋ ነበር፡ በዚያች አሮጌት ቤት ውስጥ የነበሩ ታላላቅ ዛፎች፡ ለብዙ መቶ ዓመታት ጸንታ የምትኖር ቤት ትመስለኛ ነበር። ዛሬ ግን፡ ቤቷ የነበረችበት ስፍራ ብታዩት፡ የቤት ግንባታ ፕሮጀክት ሰፍሮበታል። በጣም ተቀያይሯል። ያልተቀየረ ነገር የለም። ግን...

30 ሌላም አባቴ፡ አጭር፡ ሞላ ያለ፡ ጠንካራ ነበር፡ ከማውቃቸው አጭር ሰዎች ዋነኛ ጠንካራ እሱ ነበር። ዛፍ ቆራጭ ነውና፡ ዛፍ ቆራጭ የነበረው ጓደኛው፡ አቶ/ ኮትስ፡ ለእኔም በጣም መልካም ወዳጄ ነው፡ በመጀመርያዋ የባፕቲስት ቤተክርስትያን ዲያቆን ነበር፡ እና ከአቶ/ ኮትስ ጋር የዛሬ አመት ተገናኝተን፡ ቢሊ "አንተ'ኮ፡ የእውነት እጅግ ሐይለኛ ወንድ መሆን አለብህ፡" አለኝ።

እኔም "እረ፡ እኔ አልሆንም፡ አቶ/ ኮትስ፡" አልኩት።

31 እርሱም “የአባትህን ፈለግ ከተከተልክ፡ ትሆናለህ፡” አለኝ። እንዲህ አለኝ፡- “ሰውዬው አንድ መቶ አርባ ፓውንድ፡ ሲያነሣ አይቻለሁ፣ ዘጠኝ መቶ ፓውንድ ክብደት ብቻውን ፉርጎ ላይ ሲጭን አይቼው አውቃለሁ።” አሰራሩን ያውቅበታል። እጅግ ጠንካራ ሰው ነበር። እናቴ ሰትጠራው፡ ወደ ቤት መጥቶ ተጣጥቦ ሲዘጋጅ አየው ነበር።

32 ቤታችን ፊት ለፊት ባለው ሜዳ የአፕል ዛፍ ነበረች፡ ከጓሮም ሦስት ወይም አራት ትንንሽ ነበሩ። እና በዛፉ መካከል እጅግ ያረጀች መስታወት፡ ትልቅ፡ የመስታወት ሰባሪ ነበረች። በዛፉ ግንድ ጎን ታጥፈው በተሰኩ ሚስማሮች ተጠርቋል። የእንጨት ባለሞያዎች የሆናችሁ “የኮት ማንጠልጠያ፡” የምትሉት አይነት ነው። መስታወቱን በቦታው ለመሸከም ታጥፎ ተሰክቶበት ነበር። በዚያም ከቆርቆሮ ብረት የተሰራች የድሮ ማበጠርያ ነበረች። የድሮ ብረት ማበጠርያ... ዘመናዊ-ያልሆነ የብረት ማበጠርያ አይቶ የሚያውቅ አለ? ይታየኛል።

33 ሌላም አነስተኛ መታጠቢያ ወንበር ነበረች፡ ከቦርድ የተሰራች ከበታችዋ ዝርግ እግሮች ያሏት አነስተኛ ወንበር፡ ከዛፉ ጋር ተጠርቃ ነበር። ሌላም፡ ውሃ የምንቀዳባት፡ ያረጀች አነስተኛ የሳልፈር ማውጫ ፓምፕ፡ ቀድተንም በዛፏ ስር እንታጠብ ነበር። ሌላም ማማ ከምግብ ጆንያ ፎጣዎችን ታዘጋጅልናለች። የምግብ-ጆንያ እንደ ፎጣ ተጠቅሞ የሚያውቅ ሰው አለ? አሁን ገና፡ በቤቴ እንዳለሁ ተሰማኝ። እነዚያ ትላልቅ፡ ሻካራ ፎጣዎች! እሷ... እኛን ልጆች ገላችን ስታጥበን፡ ባሸችን ቁጥር ሰሜቱ ቆዳችንን የመነሣት ያህል ነበር። እና ያ የምግብ ከረጢት ትዝ ይለኛል። አንዳንድ ገመዶችን አውጥታ፡ ለማስጌጥ፡ ትንሽ ዘርፎች ትሠራበታለች።

34 ሰንቶቻችሁ በገለባ ፍራሽ ተኝታችሁ ታውቃላችሁ? እሺ፡ እንዲህ—እላችኋለሁ! የገለባ ትራስ የምታውቁ ሰንቶቻችሁ ናችሁ? እንደው፡ ወንድም ግሎቨር፡ አሁን የእውነት፡ ቤት ቤት ብሎኛል! መቼም፡ ከገለባ ፍራሽ፡ ከወረድኩ ብዙ ዘመናት አልፏል፡ ቢሆንም እንደው... ኦህ፡ መኝታው—ደስ፡ ይላል። ክረምት ሲሆን፡ የድሮውን ላባ አልጋ ወሰደው በላዩ ላይ ይደርቡበታል። ከዚያ በኋላ—በቤቱ—ንቃቃት የሚነፍሰውን ቅዝቃዜ ለመከላከል የሸራ ቁራጭ ይደረብበታል፡ የግድግዳ ጣውላዎች ወደ ላይ ሲነሡ፡ ታስታውሳላችሁ፡ በዚያም፡ እንደምታውቁት በረዶው ውደ ውስጥ ይዘልቃል። አቤት፡ አሁንም በደንብ፡ አስታውሰዋለሁ።

35 ቀዳዳው የጺም ብሩሽ መያዣችን ነበር። እንደው... ይሄኛው ያስቃችኋል። ከበቆሎ ልጣጭ የተሰራ ነበር፡ ከበቆሎ ልጣጭ የተሰራ የጺም ብሩሽ። ቀምማ ያዘጋጀችው ባህላዊ ሳሙና ከእናቴ ተቀብሎ ይቆነጥርና፡ በበቆሎው ልጣጭ ፊቱን ይቀባል፡ ከዚያ በትልቁ ባህላዊ ምላጭ፡ በደንብ ይላጨዋል። እሁድ ሲደርስ ትንሽ—ቁራጭ ወረቀት ወሰዶ፡ በአንገትጌው እንዲህ ያጣብቀዋል። ያኔ ሴሉሎይድ አንገትጌ አንንገታቸው ዙርያ ይለብሱ ነበር ይህም ቆዳው—ከሸሚዙ—አንገትጌ ጋር እንዳይነካካ በማለት ነው። እንደዚያ ሲደረግ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ይገርማል፡ ማይ፡ ማይ!

36 ለሚጠጣ ውሃ የምንቀዳባት፡ አንዲት ትንሽ ምንጭ ታች ነበረች ትዝ ትለኛለች፡ እና ውሃውን ባረጀ የቅል መቅጃ እንቀዳው ነበርን። እስኪ የቅል

መቅጃ ሰንቶቻችሁ ታውቁታላችሁ? እሺ፡ ለመሆኑ ከኬንታኪ የመጣችሁ ሰንት ትሆናላችሁ? አዎን፡ በጣም ጥሩ፡ ኬንታኪያውያንን እዩአቸው። እሺ፡ አቤት፡ እዚያው—አይደል ያለሁት... ኦኪሳውያን እና አርኪሳውያን ብቻ መሰላችሁኝ ነበር፡ ኬንታኪያውያኑም እየበዙ ይመሰላል። አዎን፡ ባለፉት ጥቂት ወራቶች በኬንታኪ ውስጥ ነዳጅ ቆፍረዋል፡ ምናልባት፡ በዚህ ምክንያት ይሆናል ጥቂቶቹ የመጡት።

37 ለማንኛውም አባቴ እራቱን ለመብላት ሲተጣጠብ ትዝ ይለኛል፡ እጅጌውን ወደ ኋላ ሰብሰብ ያደርገዋል፡ እና አጫጭር ፈርጣማ ክንዶቹን አስታውሳለሁ። እና ፊቱን ለማጠብ፡ ክንዶቹን አጥፎ ውሃውን በፊቱ ላይ ሲወረውር፡ ጡንቻዎችሁ በትንሹ እጆቹ ውስጥ ሰብሰብ ይላሉ። እኔም "ታውቃለህ፡ አባቴ መቶ ሃምሳ አመት ይኖራል፡" እል ነበር። በጣም ጠንካራ ነበርና! እርሱ ግን በሐምሳ-ሁለት ዓመቱ አለፈ። አያችሁ? "በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና።" አዎን። ዘወትር አንኖርም።

38 አሁን ሁላችንም፡ ትንሽ ጉዞ እናድርግ። እኔ የህይወት ታሪክ እንዳለኝ ሁሉ፡ እዚህ ያላችሁ ሁላችሁም ታሪክ አላችሁ፡ አንዳንድ ጊዜ የትዝታ ጎዳናውን መራመድ ጥሩ ነው። አይመስላችሁም? ወደ ኋላ መለስ በሉ፡ እና ሁላችሁንም ወደ ኋላ መለስ ብለን፡ ህጻናት ሆነን የገጠሙንን ተመሳሳይ አጋጣሚዎችን እናስታውስ።

39 አሁን ይህ የህይወት ታሪክ አንደኛው ክፍል ነው። አብዛኛውን መጽሐፉ ውስጥ ሰላለ፡ ብዙዎቻችሁም መጽሐፉ ሰላላችሁ ነካ አድርጌ አልፋለሁ።

40 በኬንታኪ ተራሮች መካከል በአንድ ኮረብታ ራስ ላይ በነበረች ጎጆ ውስጥ ተወለድኩ። የምንኖርባት አንድ ክፍል ቤት ብቻ ነበረቻቸው፡ የቤቷ ወለል የእንጨት ርብራብም ይሁን፡ ምንጣፍ አልነበረባትም፡ ባዶ ምድር ቤት ነበረች። እና ጉቶ፡ ጠረጴዛችን፡ ባለ ሶስት እግር ጉቶ ነበር። የብራንሃም ልጆች ሁላችንም በዚያ ተደራርበን፡ በትንሿ ጎጆ ደጅ አፍ፡ ሰንርመሰመስ፡ ታውቃላችሁ፡ ታናናሽ ወንድሞቼ ሁላችንም አቧራ ውስጥ የሚንከባለሉ፡ የኦፖሶም ቡችሎች እንመስል ነበርን። ዘጠኝ ወንዶች፣ እና አንድ ምስኪን ሴት ልጅ ነን፣ እሷም በወንዶቹ መካከል አስቸጋሪ ጊዜ አሳልፋለች። ያኔ ሰለበደልናት ዛሬ ሁላችንም እናከብራታለን። ገና ትንሽ ሴት ሰለነበረች፡ አብራን የትም አትሄድም፡ በላይዋ እንሮጣለን። እንደው፡ አልቻለችም።እና ሁላችንም... እንዲህ ነበርን...

41 ከጠረጴዛው ጋር ሁለት ከተቆረጠ ልጥ የተሰሩ ወንበሮች፡ እንደነበሩን አስታውሳለሁ። የሂከሪ ችግኝ አንድ ላይ በመገመድ፡ ከሰራቸው በሂከሪ ልጥ ይሸፈናል። የሂከሪ ልጥ ወንበር አይቶ የሚያውቅ ሰው አለ? አዎን። እስከ አሁን ድረስ እማዬን እሰማታለሁ። በኋላ በእንጨት የተረበረበ ወለል ያለበት፡ ቤት በገባን ጊዜ፡ አቤት፡ እነዚያን ህጻናት ጉልበቷ ላይ **እንዲህ** ይዛ፡ ወንበሩን እየደለቁ፡ ወለሉን ላይ እየዘለሉ ይመቱታል። ሰራ ሰትሰራ ወይም ሰታጥብ፡ ወደ በር እንዳይሄዱ ህጻናቱን ሰትከለክላቸው አስታውሳለሁ፡ ውሃን ለመቅዳት ወይም የሆነ ነገር ለማድረግ ምንጩ ወዳለበት ሰትሄድ፡ ልጆች ወደ ውጭ እንዳይወጡ፡ ወንበር አሰደግፋ በበሩ አጠገብ ትቀረቅረዋለች።

42 እኔ ስወለድ፡ እናቴ የአስራ አምስት አባቴም አስራ ስምንት አመታቸው ነበሩ። ከዘጠኙ ልጆች በኩር እኔ ነኝ። እንደነገሩኝ እኔ የተወለድኩባት ማለዳ...

43 ሌላው፡ በጣም ድሆች ነበርን፡ የድሃ ድሆች። በዚያች ጎጆ ውስጥ መስኮት እንኳን አልነበረንም። አነስ ያለች ተከፋች የእንጨት በር ነበረቻት። እንደዚያ አይነት ነገር አይታችሁ ታውቃላችሁ ብዬ አላስብም። ከመስኮት ይልቅ የሚከፈት የእንጨት በር ነበረችባት፡ ቀን ይከፈታል ማታ ይዘጋል። የኤሌክትሪክ ይሁን የፋኖስ ብርሃን ማብራት አንችልም፡ ማን ነው "ኩራዝ" ግን ነበረን። ምናልባት፡ ኩራዝ ታውቁ እንደሆነ አላውቅም። ሌላስ፡ ምን ታውቃላችሁ... የፈረንጅ ጥድ አንጓ ገዝታችሁ... አንድዳችሁ ታውቃላችሁ? የፈረንጅ ጥድ አንጓን ለኩሳችሁ ክዳን ላይ ብታስቀምጡት፡ ይነዳል። በመጠኑም ቢሆን... ጭስ ይተፋል፡ ይሁን እንጂ፡ ጭሱ የሚያበላሽባቸው፡ የቤት ንብረት አልነበራቸውም። ጭሱን... ጎጆው እራሱ ይቀበለዋል። በደንብ የሚቀበል ጣርያ ስለነበረው በደንብ አርጎ ይቀበለዋል። ስለዚህ...

44 በሚያዝያ 6—1909 ተወለድኩ። ይህም፡ ታውቃላችሁ፡ አሁን ትንሽ ከሃያ-አምስት በላይ ሆኖኛል ማለት ነው። እናቴ እንደነገረችኝ፡ እኔ በተወለድኩባት ማለዳ፡ መስኰቱን ከፈቱት አለችኝ። ያኔ፡ አዋላጆች እንጂ፡ ዶክተሮች አልነበሩም። አዋላጁ... አያቴ ነበረች። እንደተወልድኩ ገና ማልቀስ ስጀምር፡ እናቴ—ልጇን ለማየት ጓጓች። እሷ—እራሷ ገና ከልጅነት አልወጣችም። ገና ሊነጋጋ፡ ጠዋት አምስት ሰዓት ሲል፡ ትንሿን መስኰት ከፈቱ። ሁላችሁም በትንሿ የህይወት ታሪክ መጽሐፍ ውስጥ... ስዕሉን አይታችሁ ይሆናል። እና—ቊጥቋጦ ላይ ያረፈ ሮቢን የሚሉት ወፍ ነበር። እና ይህ ምስኪን ሮቢን ባለው አቅም ሁሉ ይዘምር ነበር።

45 ሮቢኖችን ሁሌ እወዳቸዋለሁ። እናንተ፡ በራድዮ ስርጭት የምታደምጡኝ ልጆች፡ ወፌ ላይ አትወርውሩ። አያችሁ፡ እነሱ—እነሱ—እነሱ... ወፎቹ ናቸው። ሮቢን ደረቱ ላይ ቀይ ህብር እንዴት እንደወጣበት፡ ታሪክ ሲነገር ሰምታችኋል? ለአፍታ ቆም ላርገውና። ደረቱ እንዴት ቀይ እንደሆነ... ከእለታት አንድ ቀን መስቀል ላይ የሞት ጣር የያዘው የነገስታት ንጉስ ነበር፡ ስቃይ በዝቶበት ነበር የሚረዳው ግን አንድ አልነበረም። የሚረዳው አልነበረም። ምስኪኑ ቡናማው ወፍ የወጉት ሚስማሮችን ከመስቀል መንቀል ፈለገ፡ ወደ መስቀሉ እየተመላለሰ ሚስማሮችን ለመነተት ይታገል ነበር። ሚስማሮቹን ለመነተት አቅም አልነበረውም፡ ስለዚህም ደረቱ በቀይ ደም ራሰ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ደረቱ ቀይ ሆነ። እናንተ ልጆች፡ አትወርውሩበት። ተዉት።

46 በመስኰቱ ጠርዝ አርፎ፡ ሮቢኖች እንደ-ሚዘምሩት ይጮኽ ነበር። አባቴም—መስኰቱን መለሰው። የበሩን መስኰት በመለሰው ጊዜ፡ በሰዕሉ ላይ የምትመለከቱት ብርሃን እየተሽከረከረ በመስከቱ በኩል ገባ፡ በአልጋው ራስ ላይም ቆመ፡ ትላለች እናቴ። አያቴ የምትለው ጠፋባት።

47 ያኔ፡ ቤተሰባችን... ሐይማኖተኛ ቤተሰብ አይደለም። ዘመዶቼ ሁሉ ካቶሊኮች ናቸው። በሁለቱም በኩል አይርሽ ነኝ። አባቴ መሉ በሙሉ፡ ብራንሃም አይርሽ ነው። እናቴ ሃርቬይ፡ ብቻ ናት፡ አባቷ ቸርኬ ኢንዲያን አግብቷልና፡ ስለዚህ የአይርሽን ደም በሰሱ የቀየረው ይህ ነው። እናቴ እና አባቴ ቸርች አይሄዱም ነበር፡ ሐይማኖት ስላልነበራቸው የተጋቡት ከቸርች ውጭ ነው።

በተራሮቹ ዘንድ አንድም የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን አልነበረም። ስለዚህ በመጀመሪያዎቹ ሰፋሪዎች ውስጥ፡ ሁለት ብራንሃሞች መጡ፡ እና ከዚያም የብራንሃም ትውልድ በሙሉ ወጣ፡ የቤተሰቡ ዘር ሐረግ ይህ ነው።

48 ከዚያ በኋላ መስኮቱን ከፈተች... በተከፈተም ጊዜ ብርሃኑ ቆሞ ነበር፡ የሚያደርጉት አጡ። (እናቴ ስትነግረኝ) አባቴ ሁለት ባለ ማንገቻ ሱሪዎችን ለዚህ ቀን ብሎ ገዝቶ ነበር። በዚያ ዘመን እንጨት እና ዛፍ ቆራጮች እንደሚያደርጉት፡ እጆቹን በማንገቻዎቹ ላይ አርጎ... ቆሞ ነበር። እና እጅግ ፈሩ።

49 ከዚያ፡ በተወለድኩ ምናልባት በአስር ቀኔ፡ አካባቢ፡ "ኦፖሰም ኪንግደም፡" ኦፖሰም ኪንግደም የባፕቲስት ቤተክርስትያን ወደሚባለው አነስተኛ ቤተ ክርስትያን ወሰዱኝ። እስቂኝ ስያሜ ነው። በዙር የሚሰብክ አንድ ሽማግሌ ነበረ፡ የድሮው ዘመን የባፕቲስት-ሰባኪ በየሁለት ወሩ አንድ ጊዜ ወደዚያ ይመጣ ነበር። ሲመጣ... ሰዎቹ አብረው ትንሽ አገልግሎት ይኖራቸዋል፣ አንዳንድ ዝማሬዎችን አብረው ይዘምሩ ነበር፣ አልፎ አልፎ ግን ብዙ ጊዜ የዙር ጋላቢ ሰባኪዎች በመጡ ቁጥር ሰብከት ነበረ። በየአመቱ አንድ ጆንያ ዱባ እና ጥቂት ነገሮች ይከፍሉታል፡ እንደምታውቁት፡ ሰዎቹ ሰጦታውን ለምሰጠት ይሰበሰባሉ። እናም ሽማግሌው ሰባኪ በመጣ ጊዜ፣ ለልጅ እንደሚጸለይ ጸሎት አሳረገልኝ። ወደ ቤተ ክርስቲያን ያደረግኩት የመጀመሪያ ጉዞ ያ ነበር።

50 በአመቱ ይመስለኛል... ከሁለት አመት በላይ ገደማ ሰደርስ፡ የመጀመርያ ራዕይ አየሁ።

51 እንግዲህ፡ ይህ ብርሃን እንደ ገባ በተራሮቹ ዙርያ ተወራ፡ ለማወቅ ፈለጉ። አንዳንዶቹ በቤቱ ውስጥ ባለው መስታወት ላይ የፀሐይ ብርሃን አንጸባርቆ መሆን አለበት አሉ። በዚያ ግን መስታወት አልነበረም። ገና በማለዳ፡ አምስት ሰዓት ስለነበረ፡ ፀሐይም አልወጣችምና። እና ከዚያ፡ እንደው፡ በቃ ዝም ብለው አለፉት። እና እኔ ወደ ሦስት ዓመቴ... ገደማ እንደ ደርስኩ...

52 አሁን፡ እውነት መናገር አለብኝ። እዚህ መናገር የማልፈልጋቸው ነገሮች አሉ፡ እና ሳልናገር ማለፍ ብችል ደስ ባለኝ ነበር። ግን ደግሞ፡ እውነቱን ለመናገር፡ በራሳችሁ ወይም በዘመዶቻችሁ ላይ ከሆነ እውነት መናገር አለባችሁ። ብቻ እውነተኛ ሁኑ፡ ከዚያ አንድ አይነት ነው።

53 አባቴ ሐይማኖት ከመከተል እጅግ የራቀ ሰው ነበር። በየቀኑ፡ አከታትሎ የሚጠጣ የገጠር ሰው ነበር። እና በሆነ ወቅት ተጣልቶ ችግር ገጥሞት ነበር፡ ሲጣሉም ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች እስከ ሞት ድረስ ተዳርሰው ነበር፡ በገጠር ተራሮች ድግስ ላይ፡ በጠመንጃ፡ በስለት በመወጋጋት ተጣሉና። አባቴም የጥሉ ዋና መሪ ነበር፡ ጓደኛውን አንድ ሰው በወንበር አንስቶ መትቶት፡ ጎድቶበት። እና ያ ሰው... ስለቱን አውጥቶ የአባቴ ጓደኛን መሬት ላይ ጥሎ ልቡን በስለት፡ ሊወጋው ሲከጅል፡ አባቴ ጣልቃ ገባና። የነበረው ነገር ከባድ ጥል ሳይሆን አይቀርም፡ ብዙ ማይሎችን፡ ርቃ ከምትገኝ ቡርከስቪል ድረስ፡ አባቴን ለመያዝ፡ በፈረስ፡ ፖሊስ ልከውበት ነበር።

54 ስለዚህ ሰውየው በሞት አፋፍ ላይ ነበር። ምናልባት አንዳንድ ዘመዶቹ እየሰሙ ይሆናል። ሰሙን እጠራዋለሁ፣ ሰሙ ዊል ያርቦሮ ይባላል። ምናልባት... ባልሳሳት ከልጆቹ ጥቂቶቹ፡ ካሊፎርኒያ ናቸው። ጉልበተኛ ነበር፡ በጣም ታላቅ ሰው፡ የገዛ ልጁ በአጥር ብረት መትቶ ገድሏል። እና በጣም

ብርቱ—እና ክፉ ሰው ነበር። እና በሱ እና በአባቴ መካከል ታላቅ የሆነ የሰለት ጥል ነበር። እና አባቴ ሰውየውን ሊሞትበት ሲል፡ ሮጦ ኬንታኪን ለቆ ወንዙን ተሻግሮ ወደ ኢንዲያና መጣ።

55 እናም በዚያን ጊዜ፡ በሉዊስቪል፡ ኬንታኪ፡ የሚኖር ወንድም ነበረው። በኬንታኪ፣ በሉዊስቪል ውስጥ የእንጨት ሞዛይክ መቍረጫ ረዳት የበላይ ተቆጣጣሪ ነበር። አባቴም ታላቅ ወንድሙን ፍለጋ መጣ። አባቴ ከአስራ ሰባት ልጆች መካከል፡ የመጨረሻው ልጅ ነበር። አንድ አመት ያህል ተሰውሮ በነበረበት ጊዜ፡ ታላቅ ወንድሙን ፍለጋ መጣ። በሕግ ይፈለግ ስለነበር፡ መመለስ አልተቻለውም ነበር። ነገር ግን በሌላ ሰው ሰም የተፈረመበት ደብዳቤ፡ ከእርሱ በተላከልን ጊዜ፡ እናቴ ደህንነቱን የምትሰማበት መንገድ ነግሯት ነበር።

56 አንድ ቀን በጸደይ ወራት አስታውሳለሁ (ትንሽ ጎጆ) ከቤቱ ጀርባ ነበረች። በእኔ እና በታናሽ ወንድሜ መካከል የዘጠኝ… የአስራ አንድ ወራት ልዩነት ነበር፡ እና—ከእነዚያ ቀናት በኋላ… እና ገና ዳዴ እያለ ነበር። እና በእጄ አንድ ትልቅ ድንጋይ ይዤ፡ድንጋዩን ጭቃ ውስጥ ምን ያህል እንደምወረውር ላሳየው እየሞከርኩ ነው። ጸደይ አልፎ ስለነበር ጉድጓዶቹ ስለ ደረቁ ጉድጓዶቹ ጭቃ ብቻ ቀርተው ነበር። እና በዛፍ ላይ የሚዘምር፡ የወፍ ድምጽ ሰማሁ። ወደ ዛፉ ቀና ብዬ ተመለከትኩ ወፉም በረረ፡ እናም፡ በበረረ ጊዜ፡ ድምፅ ተናገረኝ።

57 አሁን፡ እናንተ ይሄን ማሰብ እና ማስታወስ እንደማይቻለኝ እያሰባችሁ እንደሆነ አውቃለሁ። የሁሉ ፈራጅ የሆነው ሰማይ እና ምድር፡ እና በእነርሱ ውስጥ ያሉትንም ሁሉ የሰራ ጌታ አምላክ ያውቃል፡ እውነት እናገራለሁ።

58 ያ ወፍ፡ በበረረ ጊዜ፡ ወፉ ከነበረበት ዛፍ ውስጥ፡ በጫካ እንደተያዘ ንፋስ ድምፅ መጣ፦ "ኒው አልባኒ ከሚባል ከተማ አጠገብ ትኖራለህ፡" አለኝ። ከዚያ በኋላ ከሶስት አመቴ ጀምሮ፡ እስከ አሁን ድረስ፡ ከኒው አልባኒ በሶስት ማይልስ ርቀት በምትገኝ፡ ኢንዲያና ኖረናል።

59 ገብቼ ለእናቴ ነገርኳት። እሷም፡ የቃዠሁ ወይም የሆነ ነገር የሆንኩ መሰላት።

60 በኋላ ግን ወደ ኢንዲያና ተዛወርን አባቴም አቶ/ ዋተን ከተባለ ሀብታም ሰው ጋር ለመስራት ሄደ። ሰውየው የዋተን መጠጦች ባለቤት ነው። የብዙ ሚልዮን ባለ ሀብት ነው፡ የሎይስቪል ኮሎኔልስ፡ ቤዝ ቦል፡ እና—ሌሎች ላይ፡ ባለ ብዙ ድርሻ ነበር። እና በዚያ አጠገብ ተቀመጥን። እና አባቴ ምንም ድሃ ሰው ቢሆንም፡ ያለ መጠጥ ስለማይንቀሳቀስ፡ በማጥመቂያ ውስጥ—ዊስኪ—ማዘጋጀት ጀመረ።

61 ከልጆቹ ሁሉ የመጀመርያ ልጅ እኔ ስለነበርኩ ሰራው በእኔ ላይ እጅግ ጫና ፈጠረብኝ። የማጥመቂያው ቱቦዎች ዊስኪ በሚሰሩበት ወቅት ቅዝቃዜአቸውን እንዲጠብቁ፡ በየጊዜው እየሄድኩ ውሃ መቅዳት ይጠበቅብኝ ነበር። ሁለት ሶስት ማጥመቂያዎች ነበሩት፡ ከዚያ በኋላ ይሸጠዋል። አሁን፡ መናገር ያልፈለግኩት ክፍል ይህ ነው፡ ቢሆንም ግን እውነት ነው።

62 አንድ ቀን፡ ከመጋዘኑ፡ ወደ ቤት፡ እያለቀስኩ ሰመጣ አስታውሳለሁ። ከዚያ ቦታ በስተጀርባ… በረዶ የሚሰባብሩበት ኩሬ ነገር ነበረ፡ በረዶን ሰብረው ሳጋቱራ ላይ ሲጨመር ብዙዎቻችሁ የምታስታውሱት ነገር ነው። እንግዲያውስ፡

አቶ/ ዋተንም በዚያ አገር በረዶውን የሚያከማችበት መንገድ ይህ ነበር። አባቴም—ሹፌሩ ነው፡ የግል ሹፌሩ ነበር። እና በኩሬው… አሳዎችን በሚበዙ ጊዜ እና በረዶውን እየቆረጡ በማምጣት ሳጋቱራው ላይ ያስቀምጡታል፡ በጋ ላይ በረዶው እየቀለጠ በሚሄድበት ጊዜ፡ እንደ በረዶ ሐይቅ ነገር፡ በጣም እየጠራ ይሄዳል ይመስለኛል፡ ውሃን ለማቀዝቀዣ እንጂ ለመጠጣት አይጠቀሙበትም፡ ዘምቢላቸው ላይ ወተታቸው እና ወዘተ ላይ ያደርጉታል።

63 እና አንድ ቀን ሰፈሩን ተሻግሮ ከሚገኘው፡ የውሃ ፓምፕ ውሃን እየቀዳሁ ነበርኩ። ከትምህርት ቤት መድረሴ ስለነበር፡ የሰፈር ልጆች ሁሉ አሳን ለማጥመድ ወደ ኩሬው ስለ ሄዱ፡ ማንም ላያጽናናኝ እያለቀስኩ ነበር። አቤት አሳ ማጥመድ ሰወድ። ልጆች አሳ ወደ ማጥመድ ሲሄዱ፡ እኔ ግን መጠጥ መሰርያ የሚሆን ውሃ መቅዳት ነበረብኝ። ተከልክዬ ነበር፡ እርግጥ ነው፡ እንደው፡ ማምጣት ያለባት'ኮ እናቴ ነበረች። እና… ከባድ ውጣ ውረድ ነበር። አስታውሳለሁ ሰመለሰ የተደናቀፈው የእግር ጣቴን፣ ከአቧራው ለመከላከል ከጣቴ ስር የበቆሎ ኮብል አሰሬበት ነበር። አርጋችሁ ታውቃላችሁ? ከጣታችሁ ስር የበቆሎ ኮብል **እንዲህ** አርጋችሁ በክር ታሰሩታላችሁ። እንደዚህ፡ ወደላይ አጣብቆ፡ ጣታችሁን እንደ ኤሊ ራስ ቀና ያደርገዋል። ታውቃላችሁ፡ ከጣቴ ስር ባለው ኮብል፡ የኮቴ አሻራ አይታችሁ፡ በሄድኩበት ማወቅ ትችላላችሁ። የምረግጠው ጫማ አልነበረኝም። ጫማ ተጫምተን አናውቅም፡ አንዳንዴ የክረምቱን አጋማሽ ድረስ አንለብሰም። ከለበሰን ግን፡ ምናልባት… ከምጽዋት የምናገኘው ይሆናል፡ የሆነ ሰው ይሰጠናል። ልብስም ከሌላ ሰው፡ ወይም ከበጎ አድራጎት የሚሰጠን ነው።

64 ያኔ የሰባት አመት ልጅ ነኝ፣ (መስከረም ወር ነበርና) እና ዓሳ ወደ ማጥመድ መሄድ ስለፈልግኩ፡ ዛፍ ስር ቆምኩኝ ብዙ የምሞላቸው ሳፋዎች ቀርተውብኝ ነበር፡ ገና **እችን** በምታክል ማሽ ጋሎን፡ የሞላሰሰ ባልዲ ለሞምላት ሳሰበው፡ ቁጭ ብየ እያለቀስኩ ነበር። አምጥቼ ወደ ትልቅ ሳፋ ገልብጩ በድጋሚ ሄጄ ሁለት ባልዲዎችን ይዤ፡ እራሴ ፓምፕ አድርጌ ቀድቼ እመለሳለሁ። ውሃችን እንዲህ ነበር። እናም በዚያች ምሽት አባቴ እና ጓደኞቹ፡ በቤታችን የበቆሎ ውስኪ ለማዘጋጀት ተቀጣጥረዋል።

65 እና እያለቀስኩ ነበር፡ ወዲያውኑ እንደ አውሎ ንፋስ የሆነ ድምጽ ሰማሁ፣ እንዲህ አይነት (ጩኸት፡ እንዳላበዛ ተሰፋ አደርጋለሁ)፡ ድምጹም "ዉሽሽሽሽሽሽ፣ ውሽሽሽሽሽሽ፡" የሚል አይነት ድምጽ ነበር። ዙርያው፡ በጣም ጸጥታ የሰፈነበት ነበር፡ እና ዙሪያዬን እየሁ። እንደው እንደምታውቁት፡ ትንሽ አውሎ ንፋስ፡ ሳይክሎን ብላችሁ የምትጠሩት ነው አይደል? በዝናብ ወቅት በበቆሎ ማሳ ሲያልፍ፡ ቅጠሎች እና ሌሎች፡ እንዴት እንደሚሆኑ ታውቃላችሁ፣ መኸር ሲሆን ግን፡ ቅጠሎች ሁሉ መቀየር ይጀምራሉ። እና በቤቱ እና በመጋዘኑ መካከል—ግማሽ መንገድ ላይ ደርሼ፡ ከትልቅ ነጭ ፖፕላር ዛፍ ስር ቆምኩ። እና ድምጹን ሰማሁ። ዙርያዬን እየሁ፡ ዙርያው ሁሉ በዚህ ክፍል ውስጥ እንዳለ ጸጥታ ጸጥ ብሏል። በንፋስ የሚወዛወዝ ቅጠል ይሁን ሌላ ነገር፡ አልነበረም። እኔም "ታድያ ይህ ድምጽ ከየት መጣ? " ብየ ማሰብ ጀመርኩ፤ ገና ህጻን ልጅ ነኝና፡ እንጃ፦ "በዚያ በኩል መጥቷል።" ብየ አሰብኩ። ከዚያ በኋላ እየጨመረ እየጨመረ መጣ።

66 ትንንሽ ባልዲዎቼን አንስቼ ሁለቴ እሪ አልኩና፡ ካረፍኩበት መንገድ ፈቀቅ አልኩ። ከትልቁ ዛፍ ቅርንጫፎች ስር፡ ጥቂት ጫማ ፈቀቅ አልኩና፡ እና፡ ኦህ፡ ማይ፡ ወደ አውሎ ንፋስ ድምጽ ተቀየረ። እና ለማየት ዞር አልኩ፡ ከዛፉ አጋማሽ ላይ ሌላ አውሎ ንፋስ ነበር፡ ከዛፉ ከአንደኛው ጥግ ወደሌላኛው ጥግ፡ በቅጠሎቹ መካከል ይመላለሳል። እንጃ፡ የአመቱ መጨረሻ ጊዜ ስለነበረ የተለየ ነገር ማሰብ አልቻልኩም፡ የመኸር ወቅት ነው፡ ስለዚህ፡ አውሎ ንፋሶች ይመጣሉ። ትንንሽ… "አውሎ ንፋሶች፡" እንላቸውለን። አቧራን ያነሳሉና። ምድረበዳ ላይ አይታችኋቸዋል። ያው ናቸው። እና አየሁት፡ ነገር ግን አይሄድም። ብዙ ጊዜ ለአፍታ ይቆያል፣ ከዚያ ይሄዳል፣ ይሄ ግን ሁለት ደቂቃዎች ወይም ከዚያ በላይ ቆይቷል።

67 ውድያው፡ እንደገና እርምጃዬን ጀመርኩ። እንደገናም ለማየት ዞር አልኩ። ዞር ስል፡ የእኔ ድምጽ እንደሚሰማ፡ የሚሰማ የሰው ድምጽ እንዲህ አለኝ፦ "አንተ ስታድግ እንድትሰራው የተዘጋጀልህ ስራ አለ። ስለዚህ ሰውነትህን እንዳታረክስ ተጠንቀቅ፣ ፈጽመህ እንዳትጠጣ ወይም እንዳታጨስ።" እንዴት ነው፡ እስከ ሞት ድረስ በጣም ፈራሁ! መቼስ ህጻን ልጅ ሲፈራ መገመት ትችላላችሁ። ባልዲዎቼን ጥዬ፡ ባለኝ አቅም ሁሉ እያለቀስኩ፡ በቻልኩት ፍጥነት ሮጬ ወደቤት ሄድኩ።

68 እና በዚያ ምድር፡ ኮፐርሄድስ የሚሏቸው፡ መርዛማ እባቦች አሉ። እናቴም አትክልት ካለበት ቦታ፡ ኮፐርሄድ እግሬን የነደፈኝ መስሏት ልትቀበለኝ እየሮጠች ወደ እኔ መጣች። እኔም እያለቀስኩ፣ አቅፍኳትና እየሳምኳት ወደ እቅፏ ውስጥ ዘለልኩ። ምነው "ምን ሆንክ፡ እባብ ነደፈህ እንዴ? " አለችኝና፡ ሁለመናዬን ፈተሸች።

"አይደለም ማማ! ዛፉ ላይ እዚያ ጋር ሰው አለ፡" አልኳት።

69 "አይ፡ ቢሊ፡ ቢሊ! ተው እንጂ? " አለችኝ፤ "አልተኛህም እንዴ? " አለችኝ፤

70 እኔም "አይደለም ማማ! ዛፉ ላይ ሰው አለ፡ እርሱም እንዳላጨስ እና መጥጥ እንዳልጠጣ ተናገረኝ፡" አልኳት።

71 "ዊስኪዎችን እና—መሰል ነገሮች እንዳልጠጣ።" በሰዓቱ ግን፡ ለሙንሻይን ማጥመቂያ የሚሆን ውሃ እየቀዳሁ ነበርኩ። እርሱ ግን "በጭራሽ እንዳትጠጣ ወይም ሰውነትህን በምንም መንገድ እንዳታረክስ፡" አለኝ። ታውቃላችሁ፡ እኔ በልጅነቴም፡ ወጣትነታችሁ ከሴቶች ጋር ወዘተ… ብልሹነት ነው። እኔ እስከማውቀው ድረስ፡ አንድም ቀን እንኳን በዚህ ነገር አልወደቅኩም። ጌታ ከእነዚህ ነገሮች ጠብቆኛል፡ እየቀጠልኩ ስሄድ ይገባችኋል። ስለዚህ፡ "እንዳትጠጣ ወይም እንዳታጨስ፣ ወይም ሰውነትህን እንዳታረክስ፣ አንተ ስታድግ የምትሰራው ስራ አለና።"

72 እና፡ ለእናቴ ነገርኳት፡ እና—በቃ ሳቀችብኝ። እኔም ግራ ተጋባሁ። ዶክተር ጠርታ፡ ዶክተሩም፦ "ምንም አልሆነም፡ ስለተጨነቀ ብቻ፡ ነው፡" አላት። እና አስተኛችኝ። ከዚያች ቀን በኋላ፡ እስከዛሬ ድረስ፡ ዛፏ ባለችበት አልፌ አላውቅም። ፈርቼ ነበር። ከዛፍ ላይ የተናገረኝ ሰውዬ እዚያው ስለሚኖር፡ ድምጹም እጅግ ጥልቅ ንግግር ነበረና፡በሌላኛው የአትክልቱ ሰፍራ በኩል መሄድ መረጥኩ።

73 ከዚያ በኋላ ከአንድ ወር በኋላ ይመስለኛል፡ ከታናናሽ ወንድሞቼ ጋር፡ ከቤታችን ፊት ባለው ሜዳ ብዬ እየተጫወትን ነበር። ድንገት ለየት ያለ ስሜት በሰውነቴ ላይ ተሰማኝ። እናም ቆም ብዬ አንድ ዛፍ ስር ተቀመጥኩ። እና ከኦሃዮ ወንዝ ዳርቻ ከፍ ብለን ነበርን። ወደ ጀፈርሰንቪል ቁልቁል ተመለከትኩ፣ እና ወንዙን የሚሻገር ድልድይ ተነስቶ፡ ወንዙ ላይ ሲሰራ አየሁ። አስራ ስድስት ሰዎች ናቸው (ቆጥሬአቸዋለሁ) ከዚያ ድልድይ ወድቀው ህይወታቸው ሲያልፍ አየሁ። በፍጥነት ሮጬ ለእናቴ ነገርኳት፣ እና የቃዠሁ መሰላት። ነገር ግን በአእምሮዬ ቆይቷል፡ ከሃያ-ሁለት ዓመታት በኋላ የማዛጋጃ ቤቱ ድልድይ (ወደዚያ ስትሻገሩ ብዙዎቻችሁ የምትጠቀሙበት) በዚያች ቦታ ተሰራ፡ ወንዙን የሚሻገር ድልድይ ሲሰሩ አስራ ስድስት ሰዎች ህይወታቸውን አጡ።

74 በፍጹም እውነት ከመሆን ተሳስቶ አያውቅም። እዚሁ አዳራሽ እንደምታዩት፡ ሁሌም እንዲህ ነበር።

75 እና፡ ስለፈራ ነው ብለው አሰቡኝ። በነገራችን ላይ፡ እውነትም፡ የሚጨንቀው ሰው ነኝ። አስተውላችሁ ከሆነ፡ የመንፈሳዊ ህይወት—ዝንባሌ ያላቸው ሰዎች ሁሉ ይጨነቃሉ።

76 ገጣሚዎችን እና ነብያትን ሁሉ ተመልከቷቸው። ታዋቂውን ዝማሬ የጻፈውን ዊልያም ኮፐርን እዩት፦ "ከአማኑኤል ደም ስር የሚፈስስ፡ የደም ምንጭ አለ።" የሚል ዝማሬ... ዝማሬውን ታውቁታላችሁ። በቅርብ ጊዜ መቃብሩን ጎብኝቼአለሁ። ይመስለኛል፡ ወንድም ጁልየስ ነው፡ በመቃብር ስፍራው፡ አብሮን ነበረ፡ አይ... አዎን፡ እርሱ ነው እንጂ። እና—እና፡ ያን የመሰለ መዝሙር ከጻፈ በኋላ፡ እንዲጽፍ የነካው መንፈስ ትቶት ሲሄድ፡ ከዚያ በኋላ—እራሱን የሚያጠፋበት ወንዝ ፍለጋ ወጣ። አያችሁ፡ ያ መንፈስ ተወው። እና ገጣሚያን እና ደራስያን እና... ወይም... ነብያት ማለቴ ነው።

77 ኤልያስ ተመልከቱት፡ በተራራው ላይ ቆሞ እሳትን ከሰማይ በጠራ ጊዜ ዝናብም ከሰማይ አውርዷል። መንፈስ ለቆት ከሄደ በኋላ ግን፡ በሴት ዛቻ ፈርጥጧል። እግዚአብሄርም ከአርባ ቀናት በኋላ፡ በዋሻ ውስጥ ተደብቆ አገኘው።

78 ዮናስን ተመልከቱ፡ ሴይንት ሎይስን የምታክል ከተማ ሙሉ ማቅ ለብሰው ንስሓ እስኪገቡ ድረስ፡ ወደ ነነዌ ከተማ ወርደህ—ሰበክ ብሎ ጌታ በታላቅ ቅባት ነክቶት ነበር። መንፈስ ትቶት ከሄደ በኋላ ግን፡ ምን ገጠመው? መንፈስ ከተወው በኋላ ወደ ተራራው ወጥቶ፡ እግዚአብሄር ሆይ ህይወቴን ውሰድ ብሎ ሲጸልይ እናያለን። ስለዚህ፡ አያችሁ፡ ምሪት ነው። እና እነዚህ ነገሮች ሲፈጸሙ፡ በህይወታችሁ—የሚሰሩት አንዳች ነገር ይኖራል።

79 ከዚያ በኋላ እያደግኩ ስሄድ አስታውሳለሁ። ወጣትነት ጀመረኝ። (በጥቂት ደቂቃዎች ለመጨረስ እሞክራለሁ።) ወጣት መሆን ስጀምር እንደ ሌሎች ወጣቶች ሀሳቦች ነበሩኝ። ወደ... ትምህርት ቤት ስሄድ፡ ልጃገረዶች አያለሁ። ታውቃላችሁ፡ ብታውቁኝ፡ በጣም አይናፋር ነበርኩ። በስተመጨረሻ ግን—አንዲት ሴት ጓደኛ አገኘሁ። እንደ ማንኛውም ታዳጊ ልጆች፡ የአስራ አምስት ዓመት፡ ትመስለኛለች። እና—በጣም ቆንጆ፡ አቤት፡ የምታምር ነበረች። አቤት፡ የእርግብ አይን የመሳሰሉ አይኖች፣ ዕንቊ የመሳሰሉ ጥርሶች፣ የስጎን የመሰለ አንገት ነበራት፣ እና በጣም—ታምራለች።

80 ሌላም ታዳጊ ጓደኛ ነበረኝ፡ ከእሱ ጋር... ጓደኛሞች ነበርን፡ እና የአባቱን ሞዴል-ቲ ፎርድ መኪና ይይዝ ነበር፡ ከሴቶቻችን ጋር ቀጠሮ ነበረን። እና ሽርሽር ልንወስዳቸው፡ ፈለግን። ሁለት ጋሎን ናፍጣ ለመግዛት በቂ ገንዘብ አለን። መኪናውን ለመቀስቀስ የኋላውን ጎማ ማንሻ ይዘናል። ምናልባት፡ ታስታውሱት አታስታውሱት አላውቅም እንጂ፡ መኪና መቀስቀሻም። ነገር ግን—ችግር ሳይገጥመን በመልካም ሄድን።

81 እና ጥቂት ሳንቲሞች ኪሴ ውስጥ ስለነበር፡ አንድ ቦታ ላይ አቁመን ሃም ሳንድዊች ገዛን... አንዷን በአምስት ሳንቲም ትሸጥ ነበር። ስለዚህ፡ አራቱን መግዛት እችላለሁና፡ አቤት! ሃብታም ነኝ፡ አያችሁ? እና ሳንድዊቹን በልተን ኮካችንን ከጠጣን በኋላ፡ ጠርሙሶችን ለመመለስ ሄድኩ። በጣም የገረመኝ፡ እንደወጣሁ፡ (ልጅቷ ወድያው ከጸጋው፡ ወይም ከሴትነቷ መውደቅ ጀመረች) እርግቤ ስጋራ እያጨሰች አገኘኋት።

82 እና፡ ሲጋራን በሚያጨሱ ሴቶች ላይ ድሮም የራሴ አቋም አለኝ፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ አቋሜን አልቀየርኩም። እውነቴን ነው። ሴት ልታደርግ ከምትችላቸው ነገሮች እጅግ የረከሰ ድርጊት ይህ ነው። ፍጹም እውነት ነው። እና አሰብኩ—እና... ልንገራችሁ፡ ይሄን በማለቴ፡ የትንባሆ ኩባንያ ሊያሳድደኝ ይችላል፡ ይሁን እንጂ፡ የዲያብሎስ መሣርያ ነው። በዚህች አገር ከሚገኙ ነገሮች ዋና ገዳይ አጥፊ እሱ ነው። ልጄ አጫሽ ከሚሆን ሰካራም ቢሆን እመርጣለሁ። እውነቴን ነው። ሚስቴ ስታጨስ ከማያት፡ ስክራ፡ ደጅ ላይ ወድቃ ባያት ይሻለኛል። እንዲህ ነው...

83 (ምናልባት ጥያቄ መጠየጠየቃችሁ አይቀርምና) አሁን፡ በእኔ ያለው የእግዚአብሄር መንፈስ፡ የእግዚአብሄር መንፈስ ከሆነ፡ እናንተ ሲጋራ የምታጨሱ ሰዎች... በተደጋጋሚ፡ ተናግሬልና፡ ወደዚያ ለመድረስ ጥቂት እድል ብቻ ይኖራችኋል። ከዚህ መድረክ፡ እንዴት እንደሚኰንነው አስታውላችኋል። አስከፊ ነገር ነው። ከእናንተ አርቁት። እመቤቶች ሆይ፡ በዚህ ጉዳይ ጥፋተኞች ከሆናችሁ፡ ይጎዳችኋልና፡ እባካችሁ፡ በክርስቶስ ስም! ከራሳችሁ አርቁት። ይገድላችኋል። የ... የመኪና ጭነት የሚያክል—ካንሠር ነው።

84 ዶክተሮች ያስጠነቅቋችኋል። መልሰው ግን እንዴት እንደሚሸጡላችሁ! መድኃኒት ቤት ሄዳችሁ፡- “ባለ ሐምሣ-ሳንቲም ካንሰር... አለ ብላችሁ ለመግዛት ብትጠይቁ።” እያችሁ፡ መጥተው ይዘጉባቸዋል። ሄዳችሁ ግን ባለ ሐምሣ-ሳንቲም ሲጋራ ስትገዙ፡ ያው እራሱን ይሸጡላችኋል። ዶክተር ብሏልና። አቤት፡ ይቺ በገንዘብ-ያበደች አገር። በጣም ከባድ ነው። ገዳይ ነው። ተረጋግጧል።

85 እንጃ፡ እቺ ምስኪን ልጅ ሲጋራ በእጇ ይዛ፡ አራዳ አራዳ ስትጫወት ሳያት፡ እጅግ ወድጃታለሁ ብዬ አስቤ ስለነበር፡ በጣም አዘንኩ። “እንጃ እንግዲህ... ” አልኩ፤

86 አሁን፡ እንደምታውቁት፡ “የሴት-ጠላት፡” ብለው ይጠሩኛል፣ ምክንያቱ ብዙ ጊዜ ሴቶችን እቃወማለሁ፡ እናንተ እህቶች ላይ ግን አልቃወምም። እኔ የምጠላው የዘመኑ ሴቶች የሚሆኑት ነገር ነው። አዎን። መልካም ሴቶች መደነቅ አለባቸው።

87 አባቴ አሁንም በዚያ ስራ ተጠምዶ ሳለ፡ ውሃ እና ሌላ ነገሮች ለማምጣት ሰወጣ፡ ከአስራ ሰባት፡ አስራ ስምንት አመት የማይበልጡ ሴቶች፡ አሁን ባለኝ እድሜ ክልል ከሆኑ ወንዶች ጋር ሲስኩ፡ አይቻለሁ። ከዚያ በኋላ ወደ ቤታቸው ሄደው ለባሎቻቸው እራት መስራት እንዲችሉ፡ የሚያነቃቸው ጥቁር ቡና ይሰጧቸዋል። ኦህ፡ እንደዚህ ያለ ነገር ላይ፡ “እኔም... ” ያኔ አስተያየቴ ይህ ነበር፦ “እነዚህን ለመግደል የሚበቃ ዋጋ ያለው ንጹህ ጥይት የለም።” በእውነት። ሴቶችን ጠላሁ። እውነት ነው። እና አሁንም ተመሳሳይ ነገር እንዳላሰብ፡ እያንዳንዱን እንቅስቃሴ እመረምራለሁ።

88 አሁን፡ መልካም ሴት በወንድ ዘውድ እንዳለች ጌጥ ናት። ሙገሳ ያስፈልጋታል። እናቴ... ሴት ናትና፣ ሚስቴም እንዲሁ፡ እና እጅግ የተወደዱ ናቸው። እና እጅግ የማከብራቸው በሺዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያን እህቶች አሉኝ። ይህ ግን—እግዚአብሄር እውነተኛ ንግስት አድርጎ የሰጣቸውን እናትነት ካከበሩ ብቻ፡ መልካም ይሆናል። ከመዳን ቀጥሎ እግዚአብሄር፡ ለሰው ከሚሰጣቸው ድንቅ ስጦታዎች ሚስት ናት። ሚስት መልካም ሚስት ከሆነች፡ ልዩ ነገር ናት። ካልሆነች ግን ሰሎሞን እንዲህ አለ፦ “መልካም ሴት በወንድ ዘውድ እንዳለች ጌጥ ናት፣ ክፋ ሴት ወይም አሳፋሪ-ሴት ግን—በደሙ ውስጥ እንደገባ ውሃ ናት።” ይህ እውነት ነው፡ ከዚህ የከፋ ነገር የለም። ስለዚህ መልካም ሴት... ወንድሜ፡ መልካም ሚስት ካለችህ፡ አብዝተህ ልታከብራት ይገባል። መልካምን ሴት! እውነት ነው፡ ማክበር አለብህ። እናንተም፡ ልጆች፡ እንክብካቤ የምታደርግላችሁ፣ ንጽህናችሁ የምትጠብቅ፣ ከቤትዋ የማትርቅ፣ ትምህርት ቤት የምትልካችሁ፣ ስለ ኢየሱስ የምታስተምራችሁ፣ እናት ካለቻችሁ፣ እቺን ምስኪን እናት በእናንተ ውስጥ ባለው አቅም ሁሉ አክብሯት። ትክክለኛ እናት ስለሆነች፡ አዎን፡ ወዳጄ፡ ይህችን ሴት ልታከብሩ ይገባል።

89 ስለ ኬንታኪ ተራሮች መሃይምነት ይናገራሉ። እዚህ ጨረቃ ስፈር ላይ የሆነውን አይታችሁታል። በዚያ ከሚኖሩ አንዳንድ አሮጌት እናቶች ወደ ሆሊውድ መጥተው እናንተን ዘመናዊ እናቶች ልጆቻችሁን እንዴት ማሳደግ እንደምትችሉ ሊያስተምሯችሁ ይችላሉ። ጽጉሯ ተንጨባርሮ፡ ከንፈሯ ቀብታ... በውስጥ ልብስ ወጥታ ማደር ትፈቅዳለች፡ (ምን ብላችሁ ነበር የምትጠሩት? ) ሜክ-አፕ እና አሸንክታብ ፊቷን ለቅልቃ፡ በአንድ ጎኗ የተገለጠ ልብስ ለብሳ፡ ሌሊቱን ሙሉ፡ ትስክራለች፡ ወንድሜ፡ ከነዚህ የጥድ ቅርንጫፎች አንዱ ከላይዋ ተቆርጦ ያጣች እለት ከዚያ በኋላ አትሄድም። ልንገርህ፡ እንደውም... እነዚያን አይነት ጥቂት ቢኖሯችሁ፣ የተሻለ ሆሊውድ ይኖራችሁ ነበር፡ የተሻለ ሀገር ይኖራችሁ ነበር። ትክክል ነው። ከዲያብሎስ ዘዴዎች አንዱ—ይህ ነው። “ዘመናዊ ሁን’ጂ፣” እውነት ነው።

90 አሁን፣ ይቺ ምስኪን ልጅ፣ ሰመለከታት ልቤ ደማ። “ምስኪን ሴት፡” ብዬ አዘንኩላት።

እሷም “ቢሊ፡ ሲጋራ ትፈልጋለህ? ” አለችኝ፡

“አልፈልግም፡ እመቤት፡” አልኳት። “ሲጋራ አላጨስም፡” አልኳት።

91 “እንዴ፡ ቅድም ወደ ዳንስ አልሄድም ብለኸኛል፡” አለችኝ። ቀደም ብሎ ጭፈራ ቤት ለመግባት አልሄድም ብያቸው ነበርና። ሲካሞር ጋርደንስ ብለው በሚጠሩት ቦታ፡ ዳንስ ተዛጋጅቷል ተብሏል።

“አይ፡ እኔ አልደንሰም፡” ብያቸው ነበር።

92 እና እንዲህ ብላ ጠየቀችኝ፦ “እንዴ፡ አትደንሰም፣ አታጨሰም፣ አትጠጣም። እንዴት ነው የምትዝናናው? ”

93 “ዓሳ ማጥመድ እና አደን ማደን፡ እወዳለሁ፡” አልኳት። ብዙም አልመሰጣትም።

እና “እንካ ይሄን ሲጋራ ሞክር፡” አለችኝ።

እኔም “ይቅርብኝ፡ እመቤት፡ አመሰግናለሁ። እኔ አላጨሰም፡” አልኳት።

94 መረገገጫው ላይ ቆሜ ነበርኩ። የድሮዎቹ ፎርዶች መረገገጫ ቦርድ ነበረባቸው፡ ካስታውሳችሁ። መረገገጫው ላይ ቆሜ ነበር፡ እኔ እና እሷ ከኋላ ወንበር፡ ነበርን። እርሰዋም፡ “ሲጋራ አታጨሰም ማለት ነው? ” “እና እኛ ሴቶች ካንተ የተሻለ ነርቭ አለን፡” አለችኝ።

“አይ፡ እመቤት፡ እኔ ይሄን ማድረግ የምፈልግ አይመስለኝም፡” አልኳት።

95 “አንተ’ማ፡ ወደል ሴታሴት ነህ!” አለችኝ፤ ኦህ፡ ማይ! ሴታሴት——መባል ስለማልፈልግ፡ ከባድና አደገኛ ቢል ሁን ሁን አለኝ። እያችሁ፡ የህይወት ምኞቴ፡ ከባድ የነጻ ትግል ተፋላሚ መሆን ነበር። ስለዚህ... እኔን “ሴታ ሴት! ሴታ ሴት!”

96 መቋቋም አቃተኝና፡ እጄን አውጥቼ፦ “አምጪው ሥጭኝ!” አልኳት፡ “ሴታ ሴት መሆኔን አለመሆኔን አሳያታለሁ፡” አልኩኝ። ሲጋራውን ይዤ ክብሪቱን መምታት ጀመርኩ። አሁን፡ የምታሰቡትን አውቃለሁ... እኔ ግን ስለሐሳባቹ አልጠየቅም፡ የምጠየቀው፡ ስለተናገርኩት ሐቅ ብቻ ነው። ያን ሲጋራ መለኮስ ስጀምር፣ ይህን መጽሐፍ ቅዱስ ለማንሳት የወሰንኩትን ያህል፡ ለማጨስ ወስኜ ነበር፡ እና፡ የሆነ “ውሽሽሽሽሽሽ!” የሚል ነገር ሲያልፍ ሰማሁ፤ ድጋሚ ሞከርኩ፡ አፌ ውስጥ ማስገባት አልቻልኩም። መሬት ላይ ጥዬ፡ ማልቀስ ጀመርኩ። እነርሱም ሳቁብኝ። በማሳው በኩል አልፌ፡ ቁጭ ብዬ፡ አልቅሼ፡ ወደ ቤት ሄድኩ። እና በጣም ከባድ ህይወት ነበር።

97 አስታውሳለሁ አንድ ቀን አባዬ ከጓደኞቹ ጋር ወደ ወንዝ ይወርድ ነበር። እኔና ወንድሜ፡ ውስኪውን የምንቀዳበት ጠርሙሶች ፍለጋ በጀልባ ተሳፍረን ወደ ወንዙ ማዶ መውጣት ነበረብን። ከወንዙ ዳር ለቅመን አስራ ሁለት ካመጣን፡ አምስት ሳንቲም እናገኛለን። እኔ ከአባቴ ጋር ነበርኩ፡ እና አንዷን ትንሿን ጠፍጣፋ ይዞ ነበር... ግማሽ ጠርሙዝ የሚባሉትን ዓይነት ይመስለኛል። የወደቀ ዛፍም ነበር፡ አባቴ እና... ሰውዬው ማለት አቶ ዶርንቡሽ አብረው ነበሩ። እኔ ታንኳውን ይዣት... ቆንጆ ታንኳ ነበረችው፡ እና እኔ መያዝ ስለፈለግኩ፡ እሺ እንዲለኝ ፈልጌአለሁ። ጀልባው ጥሩ ቋሚ መቅዘፊያ ነበረባት፡ የእኔ ግን ባዶ ነበረች። ያረጀ ቦርድ ለጣጥፈናት ነበርና። ሰውዬው፡ ለአባቴ ብየዳ ይሰራለታል... እና ጀልባውን ባስያዘኝ ተመኘሁ። እነርሱ... እግራቸውን ዛፉ ላይ ሰቅለው፡ አባቴ እጁን ኪሱ ውስጥ ከትቶ ትንሿን ጠርሙዝ ዊስኪ አወጣት፡ አቀበለውና ጎንጨት አድርጎ፡ ወደ አባቴ መለሰለት እርሱም ጠጥቶ፡ ከዛፉ ጎን በወጣው ጉቶ ላይ ቁጭ አረገው። አቶ/ ዶርንቡሽ አንሥቶ፡ “ቢሊ፡ እንካ፡” አለኝ።

“አመሰግናለሁ፡ አልጠጣም” አልኩት።

98 እንዲህ አለ፦ “ብራንሃም ሆኖ፡ የማይጠጣ አለ'ዴ?” ከጥቂቶቹ በቀር፡ ሁሉም እስከነ ጫማቸው ነው የሞቱት። በድጋሚም “ብራንሃም ሆኖ፡ የማይጠጣ አለ?” ብሎ ተናገረ፤

“አልጠጣም፡ ጌታዬ፡” አልኩት።

አባቴም “አይደልም፡” “አንድ ሴታሴት አሳድጌአለሁ፡” አለው።

99 እንዴ አባቴ ሴታሴት ይለኛል! “ጠርሙሱን አቀብለኝ!” አልኩት፤ ከላዩ ላይ ያለውን ክዳን ሳብ አድርጌ ለመጠጣት፡ ቀና ሳደርገው፡ “ውሽሽሽሽሽሽ!” ጠርሙሱን መልሼ ሰጥቼው እያለቀስኩ፡ የቻልኩትን ያህል ከሜዳው ወረድኩ። የሆነ ነገር እንዳደርግ አልፈቀደልኝም። አያችሁ? ጥሩ ሰው ነኝ ማለት አልችልም (ለመጠጣት ቆርጬ ነበርና) ነገር ግን እነዚህን ነገሮች እንዳላደርግ የከለከለኝ እግዚአብሔር፣ ጸጋው፣ አሰደናቂ ጸጋ ነው። እኔ ራሴ ላደርጋቸው ፈልጌ ነበር፣ ግን እንዳደርገው አልፈቀደም።

100 በኋላ የሃያ ሁለት ዓመት ልጅ እያለሁ አንዲት ልጅ አገኘሁ፤ ፍቅረኛዬም ነበረች። የጀርመን ሉተራን፡ የቤተ ክርስቲያን ልጅ ነበረች። ስሟ ብራውምባች ትባላለች ቢ-አር-ዩ-ኤም-ቢ-ኤ-ሲ-ሄች፣ ብራውምባው ከሚባል ስያሜ ነው። እና ጥሩ ልጅ ነበረች። አታጨስም አትጠጣም፡ ወይም—አትጨፍርም ምንም የማታደርግ፡ ጥሩ ልጅ። ከእሷ ጋር ለጥቂት ጊዜ ከቆየን በኋላ፡ እና እኔ... ከዛ፣ ሃያ-ሁለት ዓመት ሲሞላኝ፡ አሮጌ ፎርድ የምገዛበት በቂ ገንዘብ ያዝኩ፡ እና... አብረን በፍቅር ቆየን። ከሃዋርድ ፓርክ፡ ወደዚያ፡ ገና መምጣታቸው ስለነበር፡ በወቅቱ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን በቅርብ አልነበረም።

101 ሌላው እንደዚሁ... በሚሰዮን ባፕቲስት ቤተክርስቲያን የሾመኝ፡ ዶክተር ሮይ ዴቪስ የሚባል አገልጋይ ነበር። እህት አፕሻው፡ ወንድም አፕሻውን ወደ እኔ የላከችኝ፡ ወይም ስለ እኔ ዶክተር ሮይ ዴቪስ አነጋገረችው። እና የመጀመሪያዋ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን አገልጋይ፡ እየሰበከ ነበረ፣ ወይም—የ... በርግጥ፡ የመጀመሪያዋ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን እንደሆነች አላምንም፣ ሚሽነሪ-... ሚሽነሪ ባፕቲስት ቤተክርስቲያን በጄፈርሰንቪል ነበር መጠርያዋ። እናም ያኔ ይሰብክ ነበር፡ ማታ ወደ ቤተክርስቲያን እንሄዳለን፡ ከዚያ በኋላ... ተመልሰን እንመጣለን። ያኔ የቤተክርስትያን አባል ሆኜ አላውቅም ነበር፡ ከእሷ ጋር መሄድ ግን እወድ ነበር። ምክንያቱም ዋናው ሃሳቤ የነበረው፡ እውነት መናገር ካለብኝ፦ “ከእሷ ጋር መሄዴ ነው።”

102 ከጥሩ ቤተሰብ የወጣች ነበረች። ስለዚህ አንድ ቀን ከእርሷ ጋር ስሄድ... ከዚያ እንዲህ ማሰብ ጀመርኩ፦ “ታውቃለህ፡ ታውቃለህ፡ የዚህችን ሴት ጊዜ ማባከን የለብኝም። መልካም ሴት ስለሆነች፡ ይህ ትክክ—ትክክል አይደለም፡ እኔም ድሃ ነኝ—እና...” አባቴም የጤና እክል አለበት፡ እና እኔ—እኔ... እንዲህ አይነት የወለል ምንጣፍ ላይ በቅምጥል ያደገች ሴት ትዳር አድርጌ፡ ማስተዳደር የምችልበት ምንም አይነት አይኖረኝም።

103 ምንጣፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ሳይ፡ ምን እንደሆነ አላወቅኩትም ነበር። በሕይወቴ ካየኋቸው ነገሮች ሁሉ የሚያምር ነገር ነበር። አስታውሰዋለሁ “እንዴት እንደዚህ ያለ ነገር መሬት ላይ ያስቀምጣሉ?” ብየ አሰብኩና ጎን ጎኑን ነበር የረገጥኩት። ለመጀመርያ ጊዜ ያየሁት ያንን ምንጣፍ ነበር። “ስሌን ምንጣፍ፡”—የሚሉት... አንደኛ ምንጣፍ ይመስለኛል። ካልተሳሳትኩ በቀር።

እንደ “ክር” ወይም እንደዚያ ያለ ነገር በአንድነት ተገምዶ፡ ወለል ላይ የተዘረጋ ነገር ነበር። ታውቃላችሁ፡ ቆንጆ አረንጓዴ እና ቀይ፡ እና መሃል ላይ ትልቅ ጽጌረዳ ተሰሎበታል። በጣም ቆንጆ ነገር ነበር።

104 እና ትዝ ይለኛል እራሴን—አሳምኜ እንጋባ አላታለሁ ወይም ደግሞ፡ ሌላ መልካም ሰው እንዲያገባት ለቀቅ ማድረግ አለብኝ፡ ለእሷ ጥሩ የሆነ፡ ሊያስተዳድራት የሚችል እና ደግ ሊሆንላት ለሚችል ሰው መልቀቅ። ደግ ሰው ልሆንላት እችላለሁ፣ እንጂ እኔ—እኔ—ገቢዬ በሰአት ሃያ ሳንቲም ብቻ ነበር። ስለዚህ እሷን ማስተዳደር አልችልም። እና እኔ... አባቴም ጤና በማጣት ስለደከመ፣ ቤተሰብ በሙሉ ማስተዳደር ስላለብኝ፣ ቤተሰብ ማስተዳደር ሀላፊነት በእኔ ላይ ስለወደቀ፡ በጣም አስቸጋሪ ጊዜ በማሳለፍ ላይ ነበርኩ።

105 እና፡ “እኔ፣ ማድረግ ያለብኝ ብቸኛው ነገር እሷን መንገር ነው እኔ—እኔ... እሷ... እሷን እጅግ ባሰባትም ህይወቷን አባክና ከእኔ ጋር ትታለላለች፡ ስለዚህ—ወደ ኋላ መመለስ አልፈልግም።” እንዲህ አሰብኩ፦ “ምናልባት አንድ ሰው ወስዶ ካገባት፡ ጥሩ ቤት ውስጥ ያኖራታል። ምናልባትም እኔ ባላገባትም፡ ደስተኛ ህይወት—እየኖረች እንዳለች ማወቅ እችላለሁ።”

106 ግን ድግሞ ሌላ ሐሳብ ገባብኝ፦ “ዝም ብዬ’ማ—እሷን—አሳልፌ አልሰጥም!” በቃ ግራ የተጋባሁበት—ጊዜ ነበር። ከቀን ወደ ቀን አሳቤ እሱ ብቻ ሆነ። እንጋባ ብዬ ለመጠየቅ በጣም አሳፈረኝ። ዘወትር ማታ “ዛሬ እጠይቃታለሁ፡” በማለት አእምሮዬን አሳምናለሁ። ስንገናኝ ግን፡ ኧረ፡ ታድያስ፡ ያ ምንድን ነው፡ ቢራቢሮ፡ የሆነ ነገር አርፎብሻል... ? ወንድሞች ሆይ ሁላችሁ ምናልባት ተመሳሳይ ተሞክሮ አጋጥሟችሁ ይሆናል። እና እውነተኛ ፈታኝ ስሜት ነበር፡ ፊቴ ይሞቃል። አኔ—አላውቅም። ልጠይቃት አልቻልኩም።

107 ስለዚህ እንዴት እንዳገባሁ ትገረማላችሁ ብዬ እገምታለሁ። ታውቃላችሁ? ደብዳቤ ጽፌ ጠየኳት። እና የላኩላት... ነገር፡ “የተከበርሽ ወይዘሪት፡” በሚል አልነበረም፣ ከዚያ ይልቅ ግን (እንደምታውቁት) ፍቅር አዘል ነበረበት። ሰምምነት—አይነት አልነበረም፡ እንደውም... በተቻለኝ አቅም—ድንቅ አድርጌ፡ ጻፍኩላት።

108 እና እናቷን ትንሽ ፈርቻት ነበር። እናቷ ... ትንሽ ከባድ ሴት ነበረች። አባቷ ግን፡ ጨዋ የደችማን ሽማግሌ፡ ደስ የሚል ሽማግሌ ወዳጄ ነበር። በባቡር ሐዲድ ላይ፡ የወንድማማቾቹ፡ የባቡር ሰራተኞች አስተባባሪ ሲሆን፡ ያኔ በየወሩ አምስት መቶ ዶላር ያህል የሚከፈለው ሰው ነበር። እኔ በሰዓት ሀያ ሳንቲም እየተከፈለኝ፡ ልጁን ላገባት አሰባለሁ። አይይ! እንደማይሰራ ገባኝ። እናቷም በጣም... በርግጥ፡ ጥሩ እመቤት ነች። ቢሆንም—በማሕበረሰቡ ከፍ ያለች ሴት፡ እንደው፡ የተከበረች፡ ዓይነት ናት፡ ስለዚህ እኔ ምንም ያህል ጥቅም እንደሌለኝ ታሰባለች። እኔ ገና ፍሬ አልባ ጥሬ ሳሳፋራስ ባላገር ነኝ፡ ሆኖ ከእኔ የተሻለ ስልጡን ወንድ ቢወስዳት ይሻላል ብላ ታሰባለች፡ እ—እኔም—ትክክል ነች ብዬ አሰባለሁ። እና ያኔ ግን... ይሄን ማሰብ—አልቻልኩም።

109 አሰብኩት፦ “እሺ፡ አሁን፡ እንዴት እንደሆነ አላውቅም። እ—አባቷን መጠየቅ አልችልም፣ እ—እናቷን መጠየቅ እንደማልችል እርግጠኛ ነኝ። በቃ አስቀድሜ እሷን ልጠይቅ አሰብኩ።” ስለዚህ ደብዳቤ ጻፍኩኝ። እና በዚያ ቀን ጠዋት ወደ ሥራ ስሄድ፡ በፖስታ ሳጥን ውስጥ ጣልኩት። እሮብ ማታ... ቤተ

ክርስትያን ሄደን፡ ፖስታው ግን ሰኞ ጠዋት አደረስኩት። ማግባት እንደምፈልግ ልነግራት እሁድ እለት ቀኑን ሙሉ ሞከርኩ፣ በቂ ልብ ግን አልነበረኝ።

110 ስለዚህ በፖስታ ሳጥን ውስጥ ጣልኩት። እና በዚያ ቀን በስራ ቦታ ላይ ሆኜ “ደብዳቤው ግን እናቷ ብትቀበለውስ?” ፈራሁ፤ ወይ፡ ‘ኔ! እሷ ከተቀበለችው—በቃ አለቀልኝ እንደሚበላሽ አውቀዋለሁ፡ ስለ እኔ ግድ የላትም። በቃ፡ ላብ በላብ ሆንኩኝ።

111 አቤት፡ እሮብ ማታ፡ በመጣሁ ጊዜ፡ አረ እንዴትስ ብዬ፦ “እንዴት ብዬ እሄዳለሁ? ደብዳቤው እናቷ እጅ ከደረሰ ትጫወትብኛለች፡ በሷ እጅ እንዲገባ ተሰፋ አደርጋለሁ።” ይድረስ “ለሆፕ፡” ብዬ ነበር የጻፍኩት። ሆፕ ስሟ ነው። እና “ወደ ሆፕ ብዬ እጽፋለሁ፡” አልኩ። ደግሞም… ላታገኘውም’ኮ ትችላለች ብዬ አሰብኩ።

112 ስለዚህ ውጭ ቆም ብዬ ጥሩንባውን ነፍቼላት እንድትወጣ ከማድረግ ይልቅ የተሻለ አውቃለሁ። አቤት፡ አቤት! እና ወደ ቤቷ ሄዶ በሩን አንኳኩቶ ልጅቷን ለመጠየቅ ድፍረት የሌለው ወንድ ልጅ፣ በምንም መልኩ ከእሷ ጋር ለመሆን ምክንያት የለውም። በእውነት ትክክል ነው። በጣም ሞኝ ነው። አይረባም።

113 የቆየች መኪናዬን አቁሜ፡ ደግሞም፡ በድንብ አጥቤ ወልውያታለሁ። እናም ወደ ላይ ወጥቼ በሩን አንኳኳሁ። ወይኔ፡ እናቷ ወደ በሩ መጣች! ትንፋሼን መቆጣጠር አልቻልኩም፡ እና፦ “እን—እንዴ—እንዴት ዋላችሁ ወይዘሮ ብሩምባች?” አልኳት።

114 “እንዴት ዋልክ ዊልያም፡” አለችኝ።

“እሀ-ኦህ፡ ዊልያም!” ብዬ አሰብኩ፤

እና—እርስዋም “ትገባለህ?” አለችኝ፤

115 “አመሰግናለሁ፡” አልኳት። ወደ በሩ ገባሁ። “ሆፕ ተዘጋጅታለች?” ብዬ ጠየቅኳት፤

116 ወድያውም ሆፕ ከጓዳ በፍጥነት መጣች፡ የአስራ ስድት ዓመት ገደማ ኮረዳ ነበረች። እና “ታድያስ፡ ቢሊ!” አለችኝ፤

117 እኔም “ታድያስ፡ ሆፕ፡” አልኳት። ‘ቸርች ለመሄድ ተዘጋጅተሻል?” አልኳት፤

“አንድ ደቂቃ ብቻ ጠብቀኝ፡” አለችኝ።

118 እንዲህ ብዬ አሰብኩ፦ “ኦህ፡ ማይ! አሪፍ ነው፣ አሪፍ ነው፣ አሪፍ ነው። በፍጹም አላገኘችውም። በፍጹም አላገኘችውም። ሆፕም በፍጹም አላገኘችውም፡ ስለዚህ መልካም ነው፡ ብታገኘው ታነሳብኝ ነበርና አልኩኝ።” እና ቀለል አለልኝ።

119 እናም ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደገባን፣ በአጋጣሚ እንዲህ ብዬ አሰብኩ፦ “አግኝታው ቢሆንስ?” እያችሁ? እና ዶክተር ዴቪስ የሚናገረውን መስማት አልቻልኩም። እሷን አየኋት እና አሰብኩ፦ “ምናልባት ነገሩን እኔ እንድጠይቃት፡ እና ከወጣን በኋላ ልትነግረኝ ፈልጋ፡ ዝም ብላ ይዛው ከሆነስ።” እና ወንድም ዴቪስ የሚናገረውን መስማት አልቻልኩም። እና—ዞር ብዬ አየኋት፡ “ሳስበው፡

እሷን አሳልፌ መስጠት አንገሸሸኝ፡ ግን… ደግሞ እ—እኔ… ትዕይንቱ መገለጡ አይቀርም።”

120 እናም ከቤተክርስቲያን በኋላ አብረን በመንገድ ላይ፡ ወደ ቤት መሄድ ጀመርን፡ እና—ወደ አሮጌው ፎርድ አመራን። ከዚያ በኋላ፡ ታውቃላችሁ፡ ጨረቃዋ ደምቃ ታበራለች ወደላይ ተመለከትኩ እና በጣም ታምራለች። እሷንም አየኋት፡ አረ በለው፡ “አቤት፡ እንዴት እንደተመኘኋት፡ ግን አልችልም፡” ብዬ አሰብኩ።

121 ትንሽ መንገድ ከሄድኩ በኋላ፡ ታውቃላችሁ፡ ሰረቅ አድርጌ አየኋት። “ዛሬ ማታ—ምን ተሰማሽ? ” አልኳት፤

“ኦህ፡ ደህና ነኝ፡” አለችኝ።

122 እና አሮግጌውን ፎርድ ወደታች አስቆምነው እና መውጣት ጀመርን፡ ታውቃላችሁ፡ መንገድ ዳር አቁመን፡ ጥግ ጥጉን ይዘን ወደ ቤቷ ደረስን። በር ድረስ አብሬአት ሄድኩ። አሰብኩትና፦ “ታውቃላችሁ፡ ምናልባት ደብዳቤውን አላየችውም፡ እኔም ዝም ብል ይሻለኛል አልኩ። ሌላ ተጨማሪ የጸጋው ሳምንት አገኛለሁ እንጂ።” እና ቀለል ያለ ስሜት ይሰማኝ ጀመረ።

“ቢሊ? ” አለችኝ፤

“ወዬ፡” አልኳት።

“ደብዳቤህ ደርሶኛል፡” አለችኝ። ኦህ፡ ማይ!

“ደርሶሻል? ” አልኳት፤

123 “እህ-ሀህ፡” አለችኝ። እና፡ ሌላ ቃል ሳትተነፍስ፡ መንገዷን ቀጠለች።

124 “ሴትዮ፡ የሆነ ነገር ንገሪኝ እንጂ። ወይ አባርሪኝ ወይም የሆነ ነገር በዪኝ፡” ብዬ ማሰብ ጀመርኩ። “እና አነበብሽው—አነብበሽዋል? ” ብዬ ጠየቅኳት፤

“እህ-ሀህ፡” አለችኝ።

125 አቤት፡ ታውቃላችሁ አይደል ሴቶች ልብ ማንጠልጠል ይችሉበታል። ኦህ፡ ማለቴ፡እንዲህ—ለማለት ፈልጌ አይደለም። እያችሁ? እናንተም፡ ይገባችኋል፡ እኔ—አሳቤ፦ “የሆነ ነገር ለምን አትነግረኝም? ” በማለት፡ እያሰብኩ መንገዴን ቀጠልኩ። “ሁሉንም አነብበሽዋል? ” አልኳት፤

እሷም… [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] “እህ-ሀህ።”

126 ወደ በሩ ለመድረስ ተቃርበናል፡ እኔም፦ “አረ፡ በረንዳው ድረስ አትውሰጂኝ፡ እነርሱን ረግጨ መሄድ ይከብደኛልና፡ አሁን ንገሪኝ።” እያሰብኩ ጠበቅኳት።

127 እንዲህ አለችኝ፦ “ቢሊዬ፡ ተቀብዬሃለሁ።” “አፈቅርሃለሁ፡” አለችኝ። እግዚአብሄር ነፍሷን ይባርክ፡ አሁን ወደ ክብር ሄዳለችና። “አፈቅርሃለሁ፡” አለችኝ። “ለቤተሰብ መንገር ያለብን ይመስለኛል… ነገሩን ለቤተሰቦቻችን አይመስልህም? ” አለችኝ፤

128 እኔም “ይሄውልሽ ሃኒ፡ አድምጭኝ፡ ይሄን ጉዳይ ሃምሳ-ሃምሳ እንካፈለው፡” አልኳት። ገና ከጅምሩ፡ ከባዱን ጫና በእሷ ላይ ጣልኩባትና። “አንቺ ለእናትሽ ከነገርሻት አባትሽን እኔ እነግረዋለሁ፡” አልኳት።

“ይሁን፡ አንተ ግን አስቀድመህ አባቴን መናገር አለብህ፡” አለችኝ።

“ይሁን፡ እሁድ ማታ ላይ እነግረዋለሁ፡” አልኳት።

129 ስለዚህ እሁድ ምሽት ደረሰች፣ እሷን ከቤተክርስቲያን ወደ ቤት አመጣኋት... ደጋግማ ታየኛለች። እኔም ሳይ፡ ዘጠኝ ተኩል ሆኗል፡ የምሄድበት ጊዜ ደረሰ። ቻርሊ ጠረጴዛው ላይ ተቀምጦ እየጻፈ ነበር። ወይዘሮ/ ብሮምባች ጥግ ላይ ቁጭ ብላ፡ ዳንቴል ትሰራለች፡ ምን ብላችሁ እንደምትጠሯቸው አላውቅም። ታውቃላችሁ፡ ነገሮች ላይ የሚንጠለጠሉ ክብ ክብ ናቸው። እና እንደዚህ አይነት ነገሮችን ትሰራ ነበር። ሆፕ አሁንም አይን አይኔን ታያለች፡ ታውቃላችሁ፡ አባቷ ወዳለበት አቅጣጫ፡ በቅንድቦቿ ደጋግማ ጠቆመችኝ። እኔ ደግሞ... ኦህ፡ ማይ! “‘አይሆንም’፡ ቢለኝስ? ” ብዬ አሰብኩ፤ ለመውጣት ወደ በር ጠጋ እያልኩ፦ “እሺ በሉ፡ አሁንስ ልሂድ፡” አልኳቸው።

130 እና ወደ በሩ ሄድኩኝ፡ እና—እርስዋም ከእኔ ጋር ወደ በሩ መጣች። እሷ ሁል ጊዜ ወደ በሩ ትመጣና “ደህና እደር” ትለኛለች። እናም ወደ በሩ መሄድ ስጀምር “አትነግረውም’ዴ? ” አለችኝ፤

131 እንዲህ አልኩ፦ “አሀህ!” “በርግጥ እየሞከርኩ ነው፡ እንዴት እንደምነግረው-ግን—እኔ—ማወቅ አልቻልኩም፡” አልኳት።

132 “እኔ እመለሳለሁ አንተ ወደ ውጪ ጥራው፡” አለችኝ። እና ብቻዬን ትታኝ ተመለሰች።

እኔም “ቻርሊ፡” አልኩት።

ዞር አለና “አቤት፡ ቢል? ” አለኝ።

“አንድ ደቂቃ ብቻ ላናግርህ እችላለሁ? ” አልኩት፤

133 “ይቻላል፡” አለኝ። ከጠረጴዛው ዞር አለ። ወይዘሮ ብሩምባች እሱን አየችው፣ ሆፕንም አየች እና እኔን ተመለከተችኝ።

“በረንዳው ላይ ላናግርህ? ” አልኩት፤

“እሺ፡ እመጣለሁ፡” አለኝ። ወድያውም ወደ በረንዳው መጣ።

“ቆንጆ ምሽት ነው፡ አይደል? ” አልኩት፤

እርሱም “አዎን፡ ነው፡” ብሎ መለሰልኝ።

“በእርግጥ ሞቃት ነበር፡” አልኩት።

“አዎን ይሞቃል፡” ብሎ አየኝ።

134 እንዲህ አልኩት “ስራ በጣም ጠንክሬ እየሰራሁ ነው፡” “ታውቃለህ፡ እጆቼ እንኳን በስራ ዶልድሟል፡” አልኩት።

እርሱም “ውሰዳት፡ ቢል፡” አለኝ። “ውሰዳት።” ኦህ፡ ማይ!

135 “ኦህ፡ ደስ ሲል፡” ብዬ አሰብኩ። “እውነትህን ነህ፡ ቻርሊ? ” አልኩት፡ እርሱም... ይሄውልህ ቻርሊ፦ “ልጅህ እንደሆነች፡ አንተም፡ ሀብታም እንደሆንክ፡ ይገባኛል አልኩት።”

136 እጁን ዘርግቶ ያዘኝና። ሰማኝ ቢሊ፦ “በሰዎች ልጆች ዘንድ ገንዘብ ብቻ አይደለም መልስ አይደለም አለኝ።” አለኝ...

137 አልኩትም፦ “ቻርሊ፡ እኔ—በሰአት ሃያ ሳንቲም ብቻ ነው የማገኘው፣ ግን እወዳታለሁ እሷም ትወደኛለች። እና ቻርሊ፡ እኔ እሷን ለማኖር፡ እነዚህ በእጄ ላይ ያሉት ድልዱሞች… እስኪላጡ ድረስ፡ እሰራለሁ። የምችለውን ያህል ሁሉ እውነተኛ እሆንላታለሁ።”

138 “እምንሃለሁ፡ ቢል፡” አለኝ። “ሰማኝ ቢል፡ እንድነግርህ የምፈልገው ነገር አለኝ፡” አለኝ። እንዲህ አለኝ፦ “ታውቃለህ፡ ደስታ፡ ገንዘብ ብቻውን ደስተኛ አያረግህም።” ብቻ “ጥሩ ሰው ሁንላት። እንደምትሆን አውቃለሁ፡” አለኝ።

“አመሰግናለሁ ቻርሊ። እርግጠኛ ነኝ ያንን አደርጋለሁ፡” አልኩት።

139 ለእናቷ ለመናገር እሷ ተራ ነበር። እንዴት እንዴት እንዳረገች አላውቅም፡ ብቻ ተጋባን።

140 እኛ፡ በተጋባን ጊዜ፡ ምንም አልነበረንም፡ የቤት እቃ አልነበረንም። ሁለት ሶስት ዶላር የነበረን ይመስለኛል። ቤት ተከራየን፡ በወር አራት ዶላር እንከፍላለን። ቤታችን የቆየ ባለ ሁለት ክፍል ቤት ናት። አንድ ሰው አሮጌ ታጣፊ አልጋ ሰጠን። ታጣፊ አልጋ አይቶ የሚያቅ ሰው ካለ ይገርመኛል? እና እሱን ሰጡን። ሲርስ ኤንድ ሮይባክስ ጋር ሄጄ፡ ባለ አራት ወንበር፡ ታውቃላችሁ—ያልተቀባ ጠረጴዛ ገዛሁ፡ ያንን በጊዜ ገዝተናል። ከዚያ በኋላ ያገለገሉ እቃዎች ገዢና ሻጭ ወደ ነበረው አቶ/ ዌበር ሄጄ የማብሰያ ምድጃ ገዛሁ። ምድጃውን ሰባ-አምሰት ሳንቲም፡ ማሰቀመጫውም አንድ ዶላር ከጥቂት ሳንቲሞች ከፈልኩበት። ቤታችንን አደራጀን። ወንበሮቹን ቀለም ሥቀባቸው፡ የሻምሮክ ሥዕል ሥሥልባቸው አስታውሳለሁ። እና ግን፡ እቤት፡ ደስተኞች ነበርን። እርስ በርሳችን እንደጋገፋለን፡ ዋናው ነገር እርሱ ነውና። እግዚአብሔርም፡ በምህረቱ እና በቸርነቱ፡ በምድር ካሉት ደስተኛ ጥንዶች በጣም ደስተኞች እኛ ነበርን።

141 ይሄን ተረድቻለሁ፡ ደስታ ለእኛ በተመደበልን ነገር ምን ያህል ረክተናል እንጂ፡ በዓለም ባካበትነው ሀብት ብዛት እንደማይለካ ገብቶኛል።

142 እና፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እግዚአብሔር ወርዶ፡ ቤታችንን በወንድ ልጅ ባረከን። ስሙም ቢሊ ፖል ይባላል፡ አሁንም እዚህ አገልግሎት ላይ ነው። እና ከዚያ ትንሽ ቆይቶ፡ አስራ አንድ ወር አካባቢ፡ እንደገና ሻሮን ሮዝ በምትባል ሴት ልጅ ባረከን፣ “የሳሮን ጽጌረዳ፡” ከሚለው ቃል የተወሰደ ነው።

143 እናም አንድ ቀን ገንዘቤን አጠራቅሜ ፓው ፓው ሐይቅ ወደ ሚባለው ቦታ፡ ዓሳ በማጥመድ፡ ለመዝናናት፡ ሰሄድ ትዝ ይለኛል። እና እየተመለስኩ ሳለሁ…

144 አሁን እዚህ ጋር… የምናገረውን ብዙውን ትቼዋለሁ። እና ተቀይሬአልሁ። በባፕቲሰት ሚሺነሪ ቤተክርስትያን፡ በዶክተር ሮይ ዴቪስ ተሹሜ፣ እና አሁን በጀፈርሰንቪል የምሰብክባት ቤተክርሰትያን ውሰጥ አገልጋይ ሆኜአለሁ። እና በዚህች ትንሿ ቤተ ክርስቲያን እረኛ ነበርኩ። እኔም…

145 ገንዘብ የለም፡ እረኛ ሆኜ ቤተ ክርስቲያን አሥራ ሰባት ዓመት አገልግያለሁ ተከፍሎኝ አያውቅም። በመቀበል አላምንም ነበር-… መባ መሰብሰብያ እቃም አልነበረንም። ከሰራ ቦታ የማገኘውን አሰራት እና ሌላ፡ ማጠራቀሚያ ሳጥን፡ ከህንጻው ጀርባ ነበረች፡ በላይዋም፡ እንዲህ የሚል ጽሑፍ ነበረባት፦ “ከእነዚህ ከሁሉ የሚያንሱትን ከታናናሾች ለአንዱ ያደረጋችሁት፡ ለእኔ አደረጋችሁት።” የቤተክርሰትያኗ ክፍያ በዚህ መልኩ ነበር የተከፈለው። ለመክፈል የአሥር

ዓመት ብድር ነበረብን፡ ሁለት አመት በማይሞላ ጊዜ ከፍለን ጨረስን። እና ምንም አይነት መባ ወሰጄ አላውቅም።

146 እና ኦህ፡ ከዚያ ለእረፍት ያጠራቀምኩት ጥቂት ዶላሮች፡ ነበሩኝ። እሷም በፋይንስ ሸሚዝ ፋብሪካ ውስጥ ትስራ ነበር። ቆንጆ የምታምር ኮረዳ ነበረች። መቃብሯ ምናልባት ዛሬ በረዶ ሸፍኖት ይሆናል፡ አሁንም ግን በልቤ ውስጥ አለች። እና ወደ ሀይቁ ሄጄ ዓሣ ለማጥመድ የሚያስችል በቂ ገንዘብ እንዳገኝ ለመርዳት ጠንክራ ስትሠራ አስታውሳለሁ።

147 እና ከሀይቁ ስመለስ፣ ሚሻዋካን እና ደቡብ ቤንድ፣ ኢንዲያና፣ እያየሁ መምጣት ጀመርኩ፡ እና ከኋላቸው የሚል የተጻፈ ምልክት ያላቸው መኪኖች፡ ማስተዋል ጀመርኩ። “ምንድር ነው ‘ኦንሊ ጂሰስ፡’” አሳብ ገባብኝ። እና ምልክቱን ማስተዋል ጀመርኩ። እና በብስክሌቶች፣ ፎርዶች፣ ካዲላኮች፣ እና ሌላ-ምን አለ፣ በየትኛውም ቦታ ላይ “ኦንሊ ጂሰስ፡” ይላል። እና አንዱን ተከትዬ፡ ወደ ታላቅ እና ግዙፍ ቤተክርስቲያን ደረስኩ። ጴንጤቆስጤ መሆናቸውንም ተረዳሁ።

148 ስለ ጴንጤቆስጤዎች ሰምቼ አውቃለሁ፡ የሰማሁት ግን “ወለል ላይ የሚንከባለሉ ወንበር-ሰባሪዎች በአፋቸው የሚንተባተቡ፡” ወዘተ ነበር የሰማሁት። ስለዚህ ከእነርሱ ጋር ለመተባበር ምንም ፍላጎት አልነበረኝም።

149 ሁሉም ሲጮኹ ሰማኋቸው፡ እና “ዝም ብዬ እገባለሁ፡” ብዬ አሰብኩ። ስለዚህ የድሮዋን ፎርዴን አቁሜ ወደ ውስጥ ገባሁ፡ በዘመናችሁ ሁሉ የሰማችኋቸው ዝማሬዎች ሁሉ እየዘመሩ! በኋላ እንዳስተዋልኩት ሁለት ታላላቅ አብያተ ክርስትያናት እንደነበሩ፡ አንደኛው ፒ/ኤ/ ኦፍ ጄ/ሲ/፣ እና ፒ/ኤ/ ኦፍ ደብልዩ/፣ ብዙዎቻችሁ የድሮዎቹ ድርጅቶችን እንደምታስታውሱ አስባለሁ-... የአሁን፡ መጠርያቸው፡ ዩናይትድ ይመስለኛል፣ አሁን የተባበሩት ጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ተብለው ይታወቃሉ። አንዳንድ ሰባኪዎቻቸውን አዳመጥኳቸው። በዚያም ቆመው፡ ኦህ፣ ስለ ኢየሱስ እና እንዴት ታላቅ እንደሆነ፡ ነገሩ ሁሉ እንዴት ታላቅ እንደሆነ ያስተምሩ ነበር፣ ሌላው ደግሞ “ስለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡” አስተማሩ። “ምን እያወሩ ነው? ” ብዬም አሰብኩ፤

150 እና፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ አንድ ሰው ዘሎ በልሳኖች መናገር ጀመረ። ከዚያ በፊት፡ እንዲህ አይነት ነገር ሰምቼ አላውቅም። አንዲት ሴት ባላት ኀይል ያህል ሁሉ እየሮጠች ወደዚያ ወጣች። ከዚያም ሁሉም ተነስተው መሮጥ ጀመሩ። “ወንድሜ፡ እርግጠኛ ነኝ ምንም ዓይነት የቤተ ክርስቲያን ስነ ምግባር፡ የላቸውም!” ብዬ አሰብኩ፤ ያለቅሳሉ ይጮኻሉ ወዲያ ወዲህ ይላሉ፡ “ይህ እንዴት ያለ ሰብሰባ ነው!” ብዬ አሰብኩ። ታውቃላችሁ ግን፡ የሚገርማችሁ ነገር፡ አብዝቼ፡ በተቀመጥኩ ቁጥር፡ እየወደድኩት መጣሁ። በትክክል እውነት የሚመስል ነገር ነበረው። እና መከታተል ጀመርኩ። እና ቀጠለ። እንዲህ አሰብኩ፦ “በሩ አጠገብ... ስለነበርኩ፡ እስኪ ጥቂት ልታገሳቸው። የሆነ ነገር ከጀመሩ፡ በበሩ እሮጣለሁ። መኪናዬም ያቆምኩበት ጥግ፡ ቅርብ ነው አውቀዋለሁ።”

151 እና አንዳንዶቹ ሰባኪዎች ሰማኋቸው፣ ጥቂቶች ምሁራን እና ተማሪዎች ናቸው። ይህ ነገር፡ “ጥሩ ነው፡” አልኩኝ።

ስለዚህ የእራት ሰዓት ደረሰና፦ “ሁሉም ወደ እራት ይውጡ፡” ተባለ።

152 ትዝ ሲለኝ፦ “ወይ ጉድ። ወደ ቤት የሚያደርሰኝ አንድ ዶላር ከሰባ-አምስት ሳንቲም ብቻ አለኝ፡ እና ደግሞ... ” ለነዳጅ የሚሆን ያለኝ ይህ ብቻ ነው። ወደ ቤቴ ብቻ የሚያደርሰኝ ነበር። መኪናዬም የቆየች ፎርድ ነበረች፡ በጣም ቆንጆ የቆየች ፎርድ ናት። ወደ ኋላ ተከፋች አልነበረችም፡ ልክ እዚህ ጋር እንዳሉ አይነት ናት፡ አርጅታ ነበር እና... ፎርድ በሰዓት ሠላሳ ማይል እንደሚሄድ አምናለሁ፣ በርግጥ ግን **በዚህ** አሥራ አምስት እና አሥራ አምስትም **በዚያ** ነው። እያችሁ፡ አንድ ላይ፡ ሠላሳ ይሆናል። እና ደግሞ... አሰብኩና፦ “ይመስለኛል፡ ከ... በኋላ የሄድኩ ይመስለኛል” ለማታው ጉባኤ እዚያው ቆየሁ።

153 እና፡ ይገርማል፡ እንዲህ አለ፡ “በየትኛውም የሐይማኖት ተቋም፡ ሰባኪዎች የሆናችሁ ሁሉ ውደ መድረክ ውጡ ተባለ።” እና፡ ወደ ሁለት መቶ የምንሆን ሰዎች ነበርን፣ እኔም ወጣሁ። እና እንዲህ አለ፦ “አሁን፡ ሁላችሁ እንድትሰብኩ ጊዜ የለም።” “ማን መሆናችሁ እና ከየት እንደመጣችሁ እየተናገራችሁ ብቻ እለፉ፡” አሉን።

154 ተራዬ ደርሰና፡ “ዊልያም ብራንሃም፡ ባፕቲስት። ከጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና።” አልኩና፡ ወረድኩ።

155 የተቀሩት ሁሉ እራሳቸውን ሲያስተዋውቁ እሰማለሁ፣ “ጴንጤቆስጤ፣ ጴንጤቆስጤ፣ ጴንጤቆስጤ፣ ፒ/ኤ/ ደብልዩ/፣ ፒ/ኤ/ጄ/ሲ/፣ ፒ/ኤ/ ደብልዩ/፣ ፒ... ”

156 ወረድኩ። “እንግዲህ፡ አሰቀያሚ ዳኪዬ እኔ ብቻ ነኝ ማለት ነው፡” አልኩ። እና ቁጭ ብዬ፡ ጠበቅኩ።

157 እና፣ በዚያ ቀን፣ በመካከላቸው፡ጥሩ ወጣት ሰባኪዎች ነበሯቸው፣ እናም በኃይል ሰበኩ። ከዚያ በኋላም እንዲህ አሉ፦ “የዛሬ ምሽት መልዕክት የሚያስተላልፍልን... ” “ሽማግሌ፡” ብለው የሚጠሯቸው ይመስለኛል። አገልጋዮቻቸውም ጭምር፡ “ሬቨረንድ፡” ከመባል ይልቅ “ሽማግሌ” ብለው ይጠሯቸዋል። እና አንድ ሽምገል ያለ ጥቁር ሰባኪ አመጡ፡ እርሱም እንደ ጥንቱ-ፋሽን ሰባኪዎች አለባበሰ ኮት ለብሶ መጣ። አይታችሁ የምታውቁ አይመስለኝም። ታውቃላችሁ፡ ከኋላው ረዘም ያለ፡ የእርግብ-ጭራ መሳይ፡ ከቬልቬት አንገትጌ ጋር ለብሶ፣ በራሱ ጠርዝ ዙሪያ ጥቂት ነጭ ፀጉር ነበረው። ታውቃላችሁ፡ ምስኪን ሽማግሌ፡ **እንዲህ** ብሎ ወጣ። እና ቆመና ዘር ዘር አለ። በዚያ ስለ ኢየሱስ ከሰበኩ ሰባኪዎች ሁሉ ይልቅ ድንቅ ነበር... ልዩ ነበር፣ የተለየ፣ ሽማግሌው የሰብከቱ ቃል ከእዮብ ነበር። “የዓለምን መሰረት ባደረግሁ ጊዜ ወይስ የንጋት ከዋክብት፣ በአንድነት ሲዘምሩ የእግዚአብሔርም ልጆች እልል ሲሉ አንተ የት ነበርክ? ”

158 ምስኪን ሽማግሌ፡ “ለምን ከእነዚህ ወጣቶች አንዱን ሰባኪ አይመድቡም? ” አልኩኝ ለራሴ፤ ድንቅ... ቤቱ ጥቅጥቅ ብሎ ተጨናንቋል። “ለምን እንዲህ አላደረጉም? ” ብዬ አሰብኩ፤

159 እና ሽማግሌው ግን፡ በምድር ስለሚሆኑ ነገሮች ከመሰበክ ይልቅ፣ በዘመናት ሁሉ በሰማያት የሆነውን ነገር ሁሉ መሰበክ ጀመረ። እና፡ ወደ ጊዜ አጀማመር—ወደ መጀመርያ መመለስ ግድ ሆነበት፣ ከዚያ በኋላ ወደ ዳግም መምጣት ወደ ጎንዮሽ ቀስተ ደመና ተመለሰ። እንዴ፡ በህይወቴ እንዲህ ያለ ግሩም ሰብከት ሰምቼ አላውቅም! በዚያን ጊዜም መንፈሱ ነካው፣ **ወደዚያ**

ከፍታ ዘሎ ሄዶ ተረከዙን አንድ ላይ ጠቅ አደረገ፡ ትከሻውን ሰበቅ አድርጎ ከመድረኩ እየዘለለ ወጣ፣ ከዚያ “ለእኔ የሚሆን የምሰብክበት በቂ ቦታ እናንተ የላችሁም፡” አለ። ነገር ግን አሁን እኔ እንኳን እዚህ ካለኝ ይልቅ ነበረው።

160 “ያን ሽማግሌ እንዲህ እንዲሆን ካደረገው፣ በእኔ ላይ ቢወደርሰ ምን ያደርገኝ ይሆን? ” ብዬ አሰብኩ፤ “እኔም ይሄን ሳያስፈልገኝ አይቀርም፡” ብዬ—አሰብኩ። እንዴ፡ ሰውዬው ወደ መድረክ ሲወጣ፡ በጣም አዘንኩለት። ከመድረክ፡ ሲወርድ ግን፡ በራሴ አዘንኩ። ሲሄድም ተመለከትኩት።

161 በዚያች ሌሊት ወጣሁ፣ “አሁን፣ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት የት እንደሆንኩ፡ ለማንም ሰው አላሳውቅም፡” ብዬ አሰብኩ። ሄድኩና፡ ሱሪዬን አጥብቄ አሰርኳቸው። ጥቂት ነገር ይዤ... ጥቂት ሰቴል ሮል ገዝቼ መጣሁና፡ በበቆሎ ማሳ ለማደር ወረድኩ። በአምሰት ሳንቲም ደርዘን ያክል... መግዛት ትችላላችሁ። የቦኖ ውሃ በአካባቢው ስለነበረ፡ ቀድቼ መጣሁ። ጥቂት እንደሚያቆየኝ አውቃለሁና፡ ውሃዬን ጠጣሁና፡ ሄጄ ሮሎቹን በላሁ። እንደገናም መጥቼ ውሃዬን ጠጣሁ። ወደ ቦቆሎ ማሳ ወርጄ፡ ሁለቱን ወንበሮች አጋጠምኳቸውና ከፈይ ሱሪዬን አንጥፌ፡ በወንበሩ ላይ ተኛሁባቸው።

162 እና፣ በዚያች ሌሊት፣ እጅጉን ጸለይሁ። “ጌታ ሆይ፡ ይህ የገባሁበት ነገር ምንድነው? በሕይወቴ እንዲህ ዓይነት ሃይማኖተኛ ሰዎችን አይቼ አላውቅም፡” አልኩት። “ይህ ምን እንደሆነ እንዳውቅ እርዳኝ፡” አልኩት።

163 በነጋታው ማልጄ ገባሁ። ቁርሰ ጋበዙን። በርግጥ፡ አብሬአቸው አልበላም፡ ምክንያቱ የማስቀምጠው መባ አልነበረኝምና። ተመልሼ ሂድኩ። እና በነጋታው ማለዳ ላይ ሰገባ፡ በርግጥ (ጥቂት ሮሎችን በልቼ ነበርና)፡ ቁጭ አልኩ። ማይክራፎንም በዚያ ነበር። እኔ ማይክራፎን አይቼ አላውቅም ነበር፡ እንደውም እፈራው ነበር። እና በዚያም... የተንጠለተለ ገመድ ነገር ነበረበት፡ ወደታች ወርዶ የተንጠለጠለ ነበር። ድሮፕ ማይክ የሚባሉት አይነት፡ ነበር። እርሱም፦ “ትናንት ማታ፡ ከባፕቲሰት የሆነ ወጣት ሰባኪ፡ መድረክ ላይ፡ ወጥቶ ነበር።”

“እህ-ወይኔ፡ አሁን አለቀልኝ እኔ-እጠቅማለሁ’ዴ፡” ብዬ አሰብኩ።

164 ቀጠለና፦ “በመድረክ ላይ ከወጡት ትንሹ ሰባኪ። ብራንሃም ይባላል አለ። የት እንዳለ የሚያውቅ ሰው አለ? እንዲመጣ ንገሩት፣ የጠዋቱን መልእክት እንዲያመጣ እንፈልጋለን በሉት።”

165 ኦህ፡ ማይ! ታውቃላችሁ፡ ትንሽ ቲ-ሸርት፣ እና ከፈይ ሱሪ ለብሼ ነበር። ታውቃላችሁ፡ ባፕቲሰቶች ወደ ፑልፒት ሰንወጣ ሱፍ መልበሰ እንዳለብን እናምናለን። ስለዚህ... አልተነሳሁም—ዝም አልኩ። ያኔ በወቅቱ... (የዓለም አቀፍ ኮንሽንሽን) በሰሜን ተዘጋጅቶ ነበር የዚህ ምክንያትም በደቡብ ከተዘጋጀ ጥቁሮች መምጣት ሰለማይችሉ ነበር። ጥቁሮች በዚያ ይኖሩ ነበርና፡ እኔም ከደቡብ ነበርኩና፡ እኔም አንገቴ ላይ ትንሽ ትዕቢት ቢጤ ነበረችብኝ፡ እያችሁ፡ ከሌላ ይልቅ የተሻልኩ ይመስለኝ ነበር። በዚያ ቀን ማለዳ—አንድ ጥቁር ሰው፡ ከጎኔ ቁጭ ብሎ ነበር። እኔም ቁጭ አልኩና አየሁት። “ምንም ይሁን፡ ወንድሜ ነው፡” አልኩኝ።

166 “ዊልያም ብራንሃም የት እንዳለ የሚያውቅ አለ? ” ቀጠለ፡ እኔ ወንበር ውሰጥ ሸርተት ብዬ ወደ ውሰጥ ገብቼአለሁ። አሁንም ተናገረ፡ በድጋሚ ጠየቀ፡ “ከውጭ ያላችሁ” አለ፤ (ትንሿን ማይክ ሳብ አረገና) “ዊልያም ብራንሃም የት

እንዳለ የሚያውቅ አለ? ስለ ማለዳው መልእክት መድረክ ላይ እንደሚፈለግ ንገሩት። ከደቡብ ኢንዲያና የመጣ የባፕቲስት ሰባኪ ነው።"

167 ወደ ታች ዝቅ ብየ በዝምታ ቁጭ አልኩ። ሲጀመርም፡ የሚያውቀኝ ሰው የለም። ይህ ጥቁር ሰውዬ አይን አይኔን እያየ፡ "የት እንዳለ ታውቃለህ'ዴ? " ብሎ ጠየቀኝ፤

168 አሰብኩ። መዋሸት አለብኝ—ወይም የሆነ ነገር ማድረግ አለብኝ አልኩ። "ቆይ'ማ አንዴ፡" አልኩት።

"እሺ፡ ጌታዬ? " አለኝ።

"አንድ ነገር ልንገርህ ሰውዬው እኔው ነኝ፡" አልኩት። "እ—እኔ ነኝ፡" አልኩት።

"ታድያ፡ ወደ መድረክ ውጣ፡" አለኝ።

169 "አይ፡ አየህ፡ እኔ አልችልም፡" አልኩት። "የለበሰኩት ትንሽ ያረጀ ከፈይ ሱሪ እና ይህች ትንሽ ቲ-ሸርት ነው፡" አልኩት። "ስለዚህ መውጣት አልችልም፡" አልኩት።

170 እርሱም፦ "እነዚህ ሰዎች ስለ አለባበስህ ግድ የላቸውም፡ ዝም ብለህ ውጣ።" አለኝ።

"አይሆንም፡ አይሆንም፡" አልኩት። "አሁን ዝም በል፡ ምንም ነገር እንዳትል፡" አልኩት።

171 እና ከደቂቃ በኋላ ወደ ማጉያው መጣና፡ "ዊልያም ብራንሃም የት እንዳለ የሚያውቅ ሰው አለ? " ብለው ጠየቁ፤

172 "እዚህ አለ! እዚህ አለ! እዚህ አለ!" አላቸው፤ ኦህ፡ ማይ! ትንሿን ቲሸርት ለብሼ ተነሳሁ፣ ታውቃላችሁ። እና እኔ...

173 "ና አቶ/ ብራንሃም መልእክቱን እንድታደርስልን እንፈልጋለን፡" አለ። ኦህ፡ ማይ፡ በሁሉም ሰባኪዎች ፊት፡ አረ፡ በህዝቡ ሁሉ ፊት! ፊቴ ቀልቶ ጆሮዬ ግሎ። ታውቃላችሁ፡ እየተወላገድኩ ሄድኩ። እና እየተወላገድኩ ደረስኩና፡ ከፈይ ሱሪ እና ቲ-ሸርት የለበሰ፡ ሰባኪ፡ የባፕቲስት ሰባኪ ማይክራፎን ወዳለበት መድረክ ወጣ፡ ከዚያ ቀን በፊት አይቼ አላውቅም ነበር፡ እያችሁ።

174 ወጣሁና ቆምኩኝ፡ እየተንተባተብኩ፦ "እንጃ፡ እኔ—እኔ—ይሄን አላውቅም፡" አልኳቸው። ታውቃላችሁ፡ በጣም ፈራሁ። እና—እና እዚህ ሉቃስ 16 ከፈትኩና፣ እንዲህ አሰብኩ፦ "እንጃ፡ አሁን... " እና—እንዲህ "በሲኦልም ዓይኖቹን አነሣ፡ አለቀሰም፡" የሚል ርዕስ አገኘሁ። ይሄን ይዤ... መሰበክ ተመርኩ፡ ታውቃላችሁ፡ መሰበክ ሰጀምር ትንሽ ተሻለኝ። እኔም "ባለጸጋው በሲኦል ውስጥ ነበር፡ እና አለቀሰ፡" አልኩ። ትንንሽ ባለ ሶስት ቃላት፡ ልክ እንደነ "ይሄን ታምኛለሽን፣" የመሳሰሉ እንደ፡ "አለቱን ተናገረው፣" የመሳሰሉ ስብከቶች ሰሰብክ ሰምታችኋል። የዚያን ቀንም፡ "ከዚያም አለቀሰ" ነበር። "ልጆቹ የሉምና፡ በርግጥም የሉም፡ ከዚያም አለቀሰ።" አልኩኝ። ቀጠልኩና፦ "ምንም አበባዎች የሉምና። ከዚያም አለቀሰ። አምላክ የለምና። ከዚያም አለቀሰ። በዚያ ክርስቶስ የለም። ከዚያም አለቀሰ።" ብዬ እኔም አለቀስኩ። የሆነ ነገር ተቆጣጥሮኝ ነበር። አቤት! ኦህ፡ ማይ! በኋላ፡ ምን እንደተፈጠረ

እኔ አላውቅም። ወደ ራሴ መመለስ ስጀምር፡ ውጭ ቆሜ ነበር። ህዝብ ሁሉ ያለቅሳል ይጮኻል እና ሁሉም ይንጫጫል፡ እኔም፡ እንደው ከባድ ጊዜ ነበር።

175 ወደ ውጭ በወጣሁ ጊዜ የቴክሳስ ጫማ እና ኮፍያ የለበሰ አንድ ሰው፡ ወደ እኔ ቀረበና፡ መጥቶ፡ “አገልጋይ **እከሌ-እና-እከሌ** እባላለሁ፡” አለኝ። ካውቦይ ቡትስ፡ ካውቦይ ልብስ ለብሶ፡ ሰባኪ።

“እንዴ፡ ታዲያ የኔ ከፈይ ሱሪ ችግር የለበትማ፡” ብዬ ተጽናናሁ።

176 “ወደ ቴክሳስ እንድትወርድ እና ሪቫይቫል እንድትይዝልኝ እፈልጋለሁ፡” ብሎ ጋበዘኝ።

177 “አሀ-ሀህ፡ እሺ ልጻፈው፡ ጌታዬ።” እንደነገረኝ አድርጌ ጻፍኩት።

178 ሌላም የጎልፍ መጫወቻ ሱሪዎች መካከል፡ ጎልፍ የሚጫወቱበት፡ አይነት ሱሪ ለብሶ ሌላኛው መጣ፣ ታውቃላችሁ፡ ሱሪው ጫማ ውስጥ ጠቅጥቆታል። እርሱም፦ “አገልጋይ **እከሌ-እና-እከሌ** ከሚያሚ ነኝ። እባክህ እፈልግሃለሁ… ”

179 “እንጃ፡ ምናልባት ስለ አለባበስ ግድ የላቸውም።” አየሁትና፡ አሳብ ገባብኝ፦ “በጣም ጥሩ።”

180 እናም እነዚህን ነገሮች ይዤ ወደ ቤት ተመለስኩ። ሚስት አገኘችኝ፡ እንዲህ አለች፦ “በጣም ደስተኛ ያደረገህ ምንድነው፡ ቢሊ? ”

181 “ኦህ፡ የስብሉ ፍሬ አገኘኋቸው። አቤት፡ እስከ አሁን ካየነው ምርጡ ይህ ነው። ሰዎቹ በእምነታቸው አያፍሩም።” እና፣ ስለ ነገሩ ሁሉ፡ አጫወትኳት። “እና፡ የኔ ቆንጆ፡ ሰዎቹ የጠሩን፡ ይህ ሁሉ ግብዣ፡ ተመልከቺው!” አልኳት፤

“ወንበር ሰባሪዎቹ አይደሉም፡ አይደል? ” አለችኝ፤

182 “ምን ሰባሪዎች እንደሆኑ አላውቅም፡ ነገር ግን የሚያስፈልገኝ ነገር ያላቸው ሰዎች ናቸው፡” አልኳት። አየሽ? እኔ “የተረዳሁት—አንድ ነገር ይህ ብቻ ነው፡” አልኳት። “የዘጠና አመት፡ ሽማግሌ፡ ዳግም ወጣት ሲሆን አይቻለሁ፡” አልኳት። “በህይወቴ እንዲህ አይነት ስብከት ሰምቼ አላውቅም። ማለት፡ ባፕቲስት እንዲህ ሲሰብኩ አላየሁም።” አልኳት። እንዲህ አልኳት፦ “ጉልበታቸው ወለሉ ላይ እንበርክከው፡ ትንፋሽ እስኪያጥራቸው ድረስ ይሰብካሉ፣ ትንፋሽ ይሰበስቡና፡ እንደገና ይመለሳሉ። ሁለት ጎዳናዎችን አልፈሽ፡ ሲሰብኩ ትሰሚያቸውለሽ።” እና “እኔ—በህይወቴ እንዲህ አይነት ነገር ሰምቼ አላውቅም፡” አልኳት። እንዲህ አልኳት፦ “በማይታወቅ ቋንቋ ይናገራሉ፡ ሌላኛውም የተነገረውን ይተረጉመዋል። በህይወቴ እንደዚህ አይነት ሰምቼ አላውቅም!” “አብረሺኝ ትሄጃለሽ? ” ብዬ ጠየቅኳት።

183 “ውዴ ሆይ፡ አንተን ሳገባ፡ ሞት እስኪለየን ድረስ ከአንተ ጋር እጣበቃለሁ ብያለሁ፡” አለችኝ። እና “አብሬህ እሄዳለሁ፡” አለችኝ። “አሁን ዘመዶቻችንን እንነግራለን።”

184 “እሺ፡ አንቺ ሄደሽ ለእናትሽ ንገሪአት እኔም ለእናቴ እነግራታለሁ፡” አልኳት። ሁለታችንም… እኔ ሄጄ ለእናቴ ነገርኳት።

185 “እሺ፡ ይሁን፡ ቢሊ። ጌታ እንድትሰራው የጠራህን ስራ ሁሉ፡ ለመስራት ሂድ፡” አለችኝ።

186 እናም ወይዘሮ/ ብሩምባች ጠራችኝ። እና ሄድኩ። እና “የምሰማው ነገር ምንድነው? ” አለችኝ፤

187 እንዲህ አልኳት፦ “ኦህ፡ ወይዘሮ/ ብሩምባች፡” “እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ማናችሁም አይታችሁ አታውቁም፡” አልኳት።

“ዝም በል! ዝም በል!” አለችኝ፤

“እሺ፡ እመቤት፡” ብያት። “ይቅርታ፡” አልኳት።

“ለመሆኑ ወንበር ሰባሪዎች መሆናቸውን አውቀሃቸዋል? ” አለችኝ፤

188 እንዲህ አልኳት፦ “አላውቅም፡ እመቤት፡ ይሄን አላውቅም።” “እርግጥ እነዚህ—ሰዎች መልካም ሰዎች ናቸው፡” አልኳት።

189 እንዲህ አለችኝ፦ “ስታስበውስ! ልጄን በእነዚህ አይነት ነገሮች የምትዘፍቃት ይመስልሃልን!” “ቂላቂል! አብያተ ክርስትያናት ሁሉ የተጸየፉት ቆሻሻ ነው እንጂ ሌላ አይደለም፡” አለችኝ። “በእርግጥም! ልጄን እንደዚያ አይነት ነገር ላይ አትወሰድም፡” አለች።

190 እኔም አልኳት፦ “ግን’ኮ፡ አየሽ፡ ወይዘሮ/ ብሩምባች፣ በልቤ ውስጥ ጌታ ከእነዚህ ሰዎች ጋር እንድሄድ እንደሚፈልግ ይሰማኛል።”

191 እሷም፦ “ወደ ቤተ ክርስትያንህ ተመለስና መኖርያ ቤት እስኪያዘጋጁልህ ድረስ አብረህ ሁን፡ ስሜት የሚሰጥ ወንድ ምስል አለችኝ።” “ልጄን ግን ፈጽመህ አትወስዳትም፡” አለችኝ።

“እሺ፡ እመቤት፡” አልኳት። ፊቴን አዙሬ ወጣሁ።

192 ሆፕም ማልቀስ ጀመረች። ወደ ውጭ መጥታም፦ “ቢሊዬ፡ ማማ ምንም ብትልህም፡ እኔ ከአንተ ጋር እጸናለሁ፡” አለችኝ። ልቧን ይባርክ!

“እሺ፡ የኔ ማር፡ በጣም ጥሩነው፡” አልኳት።

193 እና ዝም ብዬ ተውኩት። “የማይጠቅሙ ፋይዳ ቢስ” ስለሆኑባት ልጅዋን እንደዚህ ካሉ ሰዎች ጋር እንድትሄድ አልፈቀደችም። እኔም ዝም ብዬ ችላ አልኩት። በዘመኔ ካጠፋኋቸው ጥፋቶች ሁሉ ትልቁ ጥፋት፡ ይህ ነበር።

194 ትንሽ ቆይቶ፡ ከጥቂት አመታት በኋላ ልጆች ተወለዱ። እና አንድ ቀን የ1937፡ የጎርፍ መጥለቅለቅ... ሆነ። ጎርፍ መጣ። ቤቶች እየፈራረሱ ነበርና፡ ያን ጊዜ እኔም ሮንዲ ወጥቼ ስለነበር... ሰዎች ከጎርፉ መጥለቅልቅ ለማትረፍ እየረዳናቸው ነበር። ባለቤቴም እጅግ ታማ፡ በኒሞንያ፡ በጸና ታምማ ነበር። መጥተው አወጧት... ይሁን እንጂ መደበኛው ሆስፒታል ሞልቶ ስለነበር ቦታ አላገኘንላትም፡ ስለዚህ መንግስት ወዳዘጋጀው ጊዜአዊ መጠለያ—ወሰድናት። እናም ከዚያ ጠርተው አመጡኝ። እኔ ዘመኔን በሙሉ ወንዙ አጠገብ ነበር የኖርኩት፡ የጀልባ ሰው ነኝ፡ እና ሰዎችን ከጎርፉ ለማትረፍ፡ የተቻለኝን እየረዳሁ ነበር። እና ከዚያ እኔ... አንድ...

195 እንዲህ ብለው ላኩብኝ፦ “በቸስት ኔት ጎዳና በኩል አንድ ቤት ጎርፍ ውስጥ ለመውደቅ ተቃርበዋል፡ ቶሎ ድረስ፡ አሉኝ። ቤት ውስጥ አንዲት እናት ከልጆቿ ጋር ቀርታለች፡” “በሞተር በጀልባህ፡ ልትደርስላቸው ከቻልክ፡” ብለው ጠሩኝ።

“እሺ፡ የምችለውን ሁሉ አደርጋለሁ፡” ብዬ መለስኩላቸው።

196 እኔም፡ ማዕበሉን እየቀዘፍኩ ሄድኩ። ኦህ፡ ማይ፡ዳርጃዎቹ ሁሉ… ተሰባብረዋል፡ ከተማዋን፡ ጠራርጎ እየወሰዳት ነበር። የቻልኩትን ያህል ነዳጅ እየሰጠሁ፡ በስተመጨረሻ መተላለፍያዎች እና ጎዳናውን አልፌ ደረስኩ። እና በአቅራቢያቸው ደረስኩና፡ የቆየ የውሃ መተላለፍያ ዳርቻ ወደነበረበት ተጠጋሁ። እና ሰው ሲጮህ ሰማሁ፡ አንዲት እናት በረንዳው ላይ ቆማ አየኋት። እየተገላባበጠ የሚያልፍ ግዙፍ ጎርፍ ነበረበት። እና፡ በቻልኩት ፍጠነት **በዚህ** መንገድ በኩል አለፍኩ፡ ምንጩን ገጭቼ ተመለስኩና ወደ አንድ ጥግ መለስኩት። እና የቆመ ምሰሶ፡ የበር ይሁን፡ የበረንዳው ምሰሶ አገኘቼ፡ ጀልባዬ በጊዜ የማቆምበት ቦታ ላይ ቆመችልኝ። በሩጫ ወጥቼ፡ እናትዬውን እና ሁለት ሶስት ልጆቿን ወደ ጀልባው አደረስኳቸው። ወድያውም ጀልባዬን ፈታሁና… አንስቼ መለስኳት። ወደ ታች አውርጄ፡ ከከተማው አንድ ማይል ከግማሽ ወደሚርቅ ቦታ፡ ወደ ዳርቻ፡ ድረስ ወደ ዳርቻው አደረስኳቸው። ልክ እንዳደረስኳቸው፡ ሴትዬዋ ራሷን ሳተች። እና “ልጄ! ልጄ!” እያለች… መጮኽ ጀመረች።

197 እኔም፡ ሕፃን ልጅ እቤት ውስጥ ትቼ ወጣሁ የምትል መሰሎኛል። ኦህ፡ ማይ! ሌሎች እሷን በሚያረጋጉበት ጊዜ እኔ ወደ ኋላ ተመለስኩ። በኋላ ግን፡ ልጇ የት እንዳለ ማወቅ… ወይም ከማን ጋር እንዳለ፡ ማወቅ እንደፈለገች ተረዳሁ። ሶስት አመት ገደማ የሆነው ልጅ አብሯት ነበር፡ እኔ ግን የመሰለኝ ገና ጡት ያልጣለ ወይም ጨቅላ መሰሎኝ ነበር።

198 እና ወደ ኋላ ተመልሼ ደረስኩ። ከጀልባው ወጥቼ ወደ ውስጥ ዘልቄ ህጻን ልጅ አለመኖሩን አየሁ፡ በረንዳው ተውጦ ቤቱ መወሰድ ጀምሯል። እና በፍጥነት ሮጥኩ እና—ጀልባዬን የሚንሳፈፍበት ቁራጭ ያዝኩ፣ ወደ ጀልባው ገብቼ፡ ሳብ አድርጌ ፈታሁት።

199 ከዚያ በኋላ ጎርፉ ያዘኝና ወደ ዋናው ማዕበል ገፍትሮ ወሰደኝ። ከምሽቱ አስራ አንድ-ተኩል ሆኖ፡ በረዶ እና ዶፍ እየወረደ ነበር። የማንሻውን ገመድ ይዤ ጀልባውን ለማንሳት ሞከርኩ፡ እና አልነሳም አለኝ፡ አሁንም ሞከርኩ አልነሳም አለኝ፡ እንደገናም ሞከርኩ። ብሎ ብሎ ወደ ማዕበሉ ወሰደኝ፡ ፏፏቴው ከበታቼ ነበር። በጣም በኃይል ሞከርኩት፡ እና፡ “ወይኔ—መጨረሻዬ ይህ ነው! በቃ፡ ይህ ነው!” አልኩ፤ እና በኃይል ሞካከርኩት። እና ደግሜ ደጋግሜ እየሳብኩት፡ “ጌታ ሆይ፡ እባክህ እንዲህ አይነት ሞት አትግደለኝ፡” አልኩት።

200 “ፋይዳ ቢስ አርገህ ቆጥረሃቸው ሳትሄድ የተውካቸውስ? ” የሚል ነገር ወደ ልቤ መጣብኝ፤ አያችሁ? ኧህ-አህህ።

201 እጄን ጀልባው ላይ መልሼ፡ እንዲህ ማለት ጀመርኩ፦ “እግዚአብሄር ሆይ፡ ማረኝ። ሚስቴ እና ልጄ እንዲህ ታመው፡ እባክህ በዚህ ሁኔታ ሆነው ትቼአቸው እንድሄድ አታርገኝ! እባክህ!” ሳልታክት መጎተቴን ቀጠልኩ፡ አሁንም አይነሣም። ወደ ታች፡ እየተወረወረ፡ የሚገለባበጠውን ወራጅ ይሰማኝ ጀመር፡ ኦህ፡ ማይ፡ አልቆልኛል… ጥቂት ደቂቃዎች ርቀት ቀረኝ። “ጌታ ሆይ፡ ይቅር ካልከኝ፡ ማንኛውንም ነገር እንደማደርግ ቃል እገባልሃለሁ፡” አልኩት። ዶፉ ፊቴን እየገረፈኝ፡ ጀልባው ውስጥ ተንበረከኩ። እና “አንተ አድርግ የምትለኝ ሁሉ አደርጋለሁ፡” ብዬ ጸለይኩ። ደግሜ ስጎትተው፡ ወድያው

ተነሣልኝ። ያገኘሁትን ጋዝ ሁሉ ገልብጬ፡ በስተመጨረሻ ዳርቻው ላይ ደረስኩ።

202 ከዛ በኋላ መኪናውን ፍለጋ፣ የሮንዲውን መኪና ፍለጋ ተመለስኩ። አንዳንድ ሰዎች “መጠለያው በጎርፍ ተወሰዷል፡ የሚል ወሬ፡” ሲያወሩ ሰምቼ… አሳብ ገባብኝ። ሚስቴ እና ልጄ፡ ሁለቱም ልጆቼ በዚያ ውስጥ ነበሩና።

203 በተቻለኝ ፍጥነት ወደ መጠለያው ደረስኩ፡ አስራ አምስት ፊት ያህል ሙሉ በሙሉ በውሃ ተጥለቅልቆ አገኘሁት። ሜጀርን አገኘሁትና፦ “ሜጀር፡ ምን ጉድ ነው ሆስፒታሉ ምን ሆነ? ” አልኩት፤

እርሱም “አይዞህ፡ አትጨነቅ። ሰው ነበረህ’ዴ? ” አለኝ፤

“አዎን፡ የታመመች—ሚስት እና ሁለት ህጻናት፡” አልኩት።

204 “ሁሉም ወጥተዋል፡” አለኝ። “በጭነት መኪና ወደ ቻርለስታውን እያመሩ ናቸው፡” አለኝ።

205 በሩጫ፡ ጀልባዬ ላይ ወጣሁ… ማለት ጀልባዬን ከኋላ ጭኜ፡ መኪናዬ ላይ ወጣሁ፡ እና በፍጥነት ሄድኩ… ወንዙ ከሁለት ተኩል እስከ ሶስት ማይል ድረስ ሰፍቶ ነበር። እና ሌሊቱን በሙሉ ሰኳትን… አንዳንዶች “መኪናው፡ የጭነት መኪናው፡ ወደ ተሸጋጋሪው ድልድይ በደረሰ ጊዜ በጎርፍ ተወሰደ፡” ብለው አወሩ።

206 እኔም፡ በአንዲት ትንሽ ደሴት ተዘግቶብኝ፡ ሶስት ቀናት ቆየሁ። ተራ ወሬ ነው ወይስ እውነት ለማሰብ ሰፊ ጊዜ ነበረኝ። “ሚስቴ የት ናት? ” ፍለጋ ብቻ።

207 ከጥቂት ቀናት በኋላ ወጥቼ ተሻግሬ፡ እስከ ኮሎምበስ፡ ኢንዲያና፡ ድረስ ርቃ፡ ጊዜአዊ—ሆስፒታል ብለው ባዘጋጁት የባፕቲስት አዳራሽ ውስጥ፡ በመንግስት የበሽተኞች አልጋ አገኘኋት። እናም የት እንዳለች እየፈለግኳት፡ “ሆፕ!” “ሆፕ!” “ሆፕ!” እየጮህኩኝ፡ የቻልኩትን ያህል ወደ እሷ ሮጥኩ፤ ዙርያውን እየሁና፡ ቲቢ ክፉኛ አጥቅቷት፡ አልጋ ላይ ተኝታ እየኋት።

አጥንት ብቻ የቀረውን እጇን ወደ ላይ አርጋ፦ “ቢሊ፡” አለችኝ።

ወደ እሷም ሮጥኩና፦ “ሆፕ፡ የኔ ማር፡” አልኳት።

“በጣም አስቀያሚ መስያለሁ፡ አይደል? ” አለችኝ፤

“አልመስልሽም፡ የኔ ማር፡ ደህና ነሽ፡” አልኳት።

208 ላለፉት ስድስት ወራት ህይወትዋን ለማትረፍ፡ ባለን አቅም ሁሉ ሰርተናል፡ ይሁን እንጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተዳከመች።

209 አንድ ቀን ስራ እየሰራሁ ራድዮ ሃሎ በርቶ ነበረ፡ የሰማኋቸው መሰለኝ፡ በራድዮ ድውላችሁ ጥሩት፦ “ዊልያም ብራንሃም፡ ባለቤትህ ደክማለችና፡ በሆስፒታል ትፈለጋለህ፡” ሲሉ ሰማሁ። ቀዩን መብራት እና ሳይረን አብርቼ፡ በቻልኩት ፍጥነት ሁሉ፡ ወደ ሆስፒታል አመራሁ። ሆስፒታል ደርሼ—አቆምኩና፡ ወደ ውስጥ ተቻኩልኩ። ወደ ሆስፒታል ሰገባ—ከእኔ ጋር አሳ ወደ ማጥመድ የሚወጣ፡ አንድ ጓደኛዬ አገኘሁ፣ ህጻናት ሆነንም አብረን ሮጠናል፡ ሳም አዴር ይባላል።

210 ዶክተር ሳም አዴር፡ በቅርብ ጊዜ በራእይ ስለ ክሊኒክ መልእክት የመጣለት ሰው ነው። እንዲህ ብሎ፡ ራእዩን የሚጠራጠር ማንም ሰው ቢኖር፡ እውነት ይሁን ስሕተት ማወቅ የፈለገ ሰው ካለ፡ ይደውልልኝ ብሎ ነበር።

211 እና ያኔ ኮፍያውን እጁ ላይ ይዞ፡ ወደ ውጪ ወጣ። ገና እኔን እንዳየኝ ማልቀስ ጀመረ። ወደሱ ሮጬ፡ አቀፍኩት። እሱም አቅፎኝ፡ "ቢሊ፡ እየሞተች ናት፡" አለኝ። "በጣም አዝናለሁ። የምችለውን ሁሉ አድርጌአለሁ፡ እስፔሻሊስቶች እና ሌሎች ሁሉ ሞክሬአለሁ፡" አለኝ።

"አትለኝም ሳም፡ እሷ አትሞትም!" አልኩት፤

"አዎን፡ እየሞተች ነች፡" አለኝ። "ቢል፡ አትግባ ይቅርብህ፡" አለኝ።

"መግባት አለብኝ፡ ሳም፡" አልኩት።

"ይቅርብህ። ይቅርብህ፣ እባክህ ተው ይቅርብህ፡" አለኝ።

"ልግባ ግድ የለም፡" አልኩት።

እርሱም "እሺ እኔም አብሬህ ልግባ፡" አለኝ።

212 "አይ፡ አንተ እዚህ ቆይ። በቀሯት ደቂቃዎች አብሬአት ልሁን፡" አልኩት።

"እራሷን አታውቅም፡" አለኝ።

213 እና ወደ ክፍል ውስጥ ገባሁ። ነርሷም ተቀምጣ፡ ሆፕ እና እሷ የትምህርት ቤት ጓደኛሞች ስለነበሩ ታለቅስ ነበር። ዞር ዞር አልኩና፡ ማልቀሷን ጀመረች፡ እጆቿን ከፍ አርጋ ምልክት ሰጠችኝ። ወደዛ ሄድኩኝ።

214 አየኋት እና፡ ወዝወዝ አረግኳት። ወድቃለች፡ ከመቶ ሀያ ፓውንድ፡ ወደ ሰልሳ ገደማ ወርዳለች። እንደገናም—ወዘወዝኳት። ከዛ በኋላ የተፈጸመው ነገር፡ በህይወት ከቆየሁ ከመቶ አመት በኋላም በፍጹም አልረሳውም። ዞር አለችና፡ በትላልቅ አይኖቿ አየችኝ። ፈገግ ብላ። "ቢሊ፡ ለምን መለስከኝ? " አለችኝ።

"አሁን ገና ነው የሰማሁት፡ የኔ ማር፡" አልኳት።

215 በመቶዎች ዶላሮች የዶክተር እዳ ተይዘናል፡ የምንከፍለውም የለንም። ስለዚህ መስራት ነበረብኝ። እና ስራ መስራት ነበረብኝ። በቀን ሁለት ሶስቴ፡ በዚያ ሁኔታ ስለነበረች፣ በየምሽቱ እሷን እያታለሁ።

እና ጠየቅኳት "ምን ማለትሽ ነው 'መለስከኝ' ማለት? " አልኳት፤

216 "ቢል፡ አዎን ሰብከኸዋል፣ አዎን ተናግረኸዋል፣ ምን አይነት እንደሆነ ግን አንተ አታውቀውም፡" አለችኝ።

"ምኑን ነው የምትናገሪው? " ብዬ ጠየቅኳት፤

217 "መንግስተ ሰማይ፡" አለችኝ። እንዲህ አለችኝ፡- "ሰማኝ፡" አለችኝ፡- "የሆኑ ወንዶች ይሁኑ ሴቶች እንጃ፡ ሰዎች አጅበው ወሰደውኝ ነበር። ሰዎቹ ነጭ የለበሱ ናቸው።" "በሰላም እና እረፍት ውስጥ ገብቼ ነበር፡" አለች። "የሚያማምሩ ወፎች ከዛፍ ወደዛፍ ይበርሩ ነበር፡" አለች። "አሁንም ብቻዬን እንዳለሁ አይምሰልህ፡" አለችኝ። "ቢሊ፡ ስሕተታችን ምን እንደሆነ እነግርሃለሁ፡" አለችኝ። "ቁጭ በል፡" አለችኝ። ቁጭ አላልኩም፡ ተንበርክኬ፡ እጇን ያዝኩ። እና ጠየቀችኝ፡- "ጥፋታችን ምን እንደሆነ አውቀኸዋል? "

“አዎን፣ ውዴ፣ አውቀዋለሁ፡” አልኳት።

218 እንዲህ አለችኝ፦ “እናቴን መስማት አልነበረብንም። እነዚያ ሰዎች ልክ ነበሩ አለችኝ።”

“አውቄዋለሁ፡” አልኳት።

219 እንዲህ አለችኝ፦ “ወደ እነዚያ ሰዎች እንደምትሄድ፡ ቃል ግባልኝ፡” “ምክንያቱ እነሱ ትክክል ናቸው፡” አለችኝ። “ልጆቼንም በዚያ መንገድ አሳድጋቸው፡” ብላ ተናገረችኝ። እኔ... “አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ፡” አለችኝ። እንዲህም ብላ ተናገረችኝ፦ “እኔ አሁን እሞታለሁ፡ ግን” አለችኝ “አሁን... መሄዴ—ምንም አያስፈራኝም።” “በጣም—በጣም ቆንጆ ነውና፡” አለችኝ። “ቢል፡ አንተን ትቼ በመሄዴ፡ የሚያሳዝነኝ አንድ ነገር ብቻ ነው። የምታሳድጋቸው ሁለቱ ልጆች መኖራቸው ስለማውቅ ነው፡” አለችኝ። “ሳታገባ ቀርተህ—ልጆቼ ከአንዱ ምሰሶ ወደ ሌላኛው ምሰሶ እንደማይከራተቱ ቃል ግባልኝ፡” አለችኝ። ሃያ-አንድ-አመት-ለሆናት እናት በጣም ከባድ ነገር ነው።

“ሆፕ፡ ይሄን ቃል አልገባልሽም፡” አልኳት።

220 “እባክህ ቃል ግባልኝ፡” አለችኝ። “ሌላም አንድ የምነግርህ ነገር አለኝ፡” አለችኝ። ጠመንጃ በጣም እወዳለሁና። እንዲህ አለች፦ “ያቺ ጠመንጃ ታስታውሳታለህ? ” “ያኔ ጠመንጃ መግዛት ፈልገህ ቅድመ ክፍያ ለመፈጸም የሚያስችል በቂ ገንዘብ አልነበረህም፡” አለችኝ።

“አዎን”፡ አልኳት።

221 እንዲህ አለችኝ፦ “ያንን የጠመንጃ ቅድሚያ ክፍያ ለመክፈል ገንዘቤን፣ አምስት ሳንቲሞቼን፡ እያጠራቀምኩልህ ነው።” “ስለዚህ አሁን፡ ይህ ሁሉ አልቆ ወደ ቤት ስትመለስ፡ ታጣፊው... ማለት የሚታጠፈው አልጋ ስር ፈልገህ፣ ከአልጋው ስር ያስቀምጥኳት ወረቀት አለች፡ በዚያም ውስጥ ገንዘቡን ታገኘዋለህ አለችኝ።” “ያንን ጠመንጃ እንደምትገዛም ቃል ግባልኝ፡” አለችኝ።

222 ሰባ አምስት-ሳንቲም ዶላር (በየአምስት ሳንቲሞች) ተቀምጦ ሳይ ምን እንደተሰማኝ አታውቁም። ጠመንጃውን ገዝቼዋለሁ።

223 እሷም እንዲህ አለችኝ፦ “ወደ ፎርት ዋይን እየሄድን ጥንድ ስቶኪንጎችን ልትገዛልኝ ፈልገህ፣ መሀል ከተማ ስትሄድ ታስታውሳለህ? ”

“አዎን፡” አልኳት።

224 ዓሣ ከማጥመድ ገና መግባቴ ነበር፡ እና እሷ... በዚያ ምሽት መሰበክ ስለነበረብኝ፡ ወደ ፎርት ዋይን እየሄድን ነበር። እና እንዲህ አለችኝ፦ “ታውቃለህ፣ ነግሬሃለሁ፡ ‘ሁለት የተለያዩ ዓይነቶች አሉ።’” አንዱ “ሺፎን ነው።” ሌላኛው ምን ነበር፡ ራዮን? ልክ ነው? ራዮን እና ሺፎን። ብቻ፡ የትኛውም ይሁን፡ ሺፎኑ ግን የሚያምር ነበር። ልክ ነው? እና “አሁን፡ ሙሉ ስታይል ያለው ሺፎን አምጣልኝ፡” አለችኝ። ያንን በስቶኪንግ ጀርባ፡ በላይ በኩል የሆነ ነገር ያለውን ነገር ታውቁታላችሁ? ስለ ሴቶች አለባበስ ምንም አላውቅም ነበር፡ እና...

225 በመንገድ ላይ፦“ሺፎን፣ ሺፎን፣ ሺፎን፣ ሺፎን፡” እንዳልረሳው “ሺፎን፣ ሺፎን፣ ሺፎን፡” እያልኩ ሄድኩ።

እንድ ሰው “ሰላም ነው፡ ቢሊ!” አለኝ፤

226 “ኦህ፡ ሰላም፡ ሰላም፡” ብዬ “ሺፎን, ሺፎን, ሺፎን, ሺፎን, ሺፎን፡” ቀጠልኩ።

227 እና መሸጫው ጋር ደርሼ አቶ ሰፖንን አገኘሁት። እሱም “ሄይ፡ ቢሊ፡ ከመጨረሻው ዓምድ አጠገብ ፐርች እየተጫወተ እንዳለ አውቀሃል? ”

“ተው እንጂ፡ እውነትህን ነው? ” አልኩት፤

“አዎን።”

ትቼው ስሄድ፡ “እቃው ምን ነበር? ” ለማስታወስ ሞከርኩ፡ እና ረሳሁት።

228 ቴልማ ፎርድ፡ የተባለች ሴት ቴን-ሴንት መደብር ውስጥ ትሠራ ነበር። የሴቶች እስቶኪንግ እንደሚሸጡ አውቃለሁ፡ እና ሄድኩኝ። “ሰላም ነሽ፡ ቴልማ፡” አልኳት።

“ሰላም፡ ቢሊ። እንዴት ነህ? ሆፕ ደህና ናት? ” አለችኝ፤

229 “ደህና።” አልኳት፤ “ቴልማ፡ አንድ ጥንድ ካልሲ ለሆፕ ፈልጌ ነበር፡” አልኳት።

“ሆፕ ካልሲ አያስፈልጋትም፡” ብላ መለሰችልኝ።

“አዎን፡ እመቤት፡ በእርግጠኝነት ትፈልጋለች፡” አልኳት።

“ሰቶኪንግ ማለትህ ነው፡” አለችኝ።

230 “ኦህ፡ ትክክል፡” “እሱ ነው፡” አልኳት። “ኧረ-እንደው፡ አላዋቂነቴን አሳየሁ፡” በማለት አሰብኩ።

“ምን አይነት ትፈልጋለች? ” አለችኝ፤

አሰብኩትና፡ “ኧረ-እንጃ!” “ምን አይነት ይኖራችኋል? ” ብዬ ጠየቅኳት፤

“ይሄው፡ ሬዮን አለን፡” አለችኝ።

231 ልዩነቱን አላውቅም ነበር። ሬዮን፣ ሺፎን፣ ሁሉም ነገር ተመሳሳይ መሰሎኛል። “የምፈልገው ይሄ ነው፡” አልኳት። እሷም... እንዲህ አልኳት፡- “ጥንድ ፋል ስታይል፡ አዘጋጂልኝ።” እሷም... ተሳሰቻለሁ። ምን ነበር? ፋል ፋሽን። “ፋል ፋሽን።” ስለዚህ “ጥንድ አዘጋጂልኝ አልኳት።”

232 ልታመጣልኝ በሄደች ጊዜ ግን፣ ሰላሣ ሳንቲም፣ ሃያ ወይም ሰላሣ ሳንቲም፡ ብቻ የዋጋው ግማሽ ብቻ ሆኖ አገኘሁት። እና፡ “ሁለት ጥንድ ሰጪኝ፡” አልኳት። አያችሁ?

233 ወደ ቤት ተመለስኩና፡- “ታውቂያለሽ፡ ማር፡ እናንተ ሴቶች ገብያውን ለመደራደር ከተማውን ሁሉ ትዞራላችሁ።” እንደው መጮህ እንዴት እንደምትወዱ። “እየሽ እኔ ግን፡ አንዱን በምትገዢበት ዋጋ፡ ሁለት ገዝቼልሽ መጥቻለሁ፡” አልኳት። አያችሁ? እንዲህ አልኳት፡- “እየሽ፡ ይህ—የኔ ልዩ ችሎታዬ ነው።” እየሽ፡ አልኳት—“ቴልማ ናት የሸጠችልኝ፡” አልኳት። ,“ምናልባት በግማሽ ዋጋ ሸጣልኝ ይሆናል፡” ብዬ ነገርኳት።

እሷም፡ “ሺፎን አግኝተሃል? ” ብላ ጠየቀችኝ፤

234 ለእኔ ሁሉም ተመሳሳይ ነበር፡ ምንም ልዩነት እንዳለው አላወቅኩምና። “አዎን፡ እመቤት፡” አልኳት።

235 እና አሁን፡ “ቢሊ፡” አለችኝ። ፎርት ዌይን ስንደርስ እንግዳ ነገር አሰብኩ፡ ሌላ ጥንድ ስቶኪንጎችን ለመግዛት ወርዳ ነበርና። እንዲህ አለችኝ፦ “ለአንተ እናት ስጥቻታለሁ፡” ‘የአሮጊቶች ዓይነት ነውና፡” ነገረችኝ። “ይሄን በማድረጌ ይቅርታ አርግልኝ፡” አለች።

“እረ፡ ችግር የለውም፡ ሃኒዬ፡” አልኳት።

236 ስለዚህ አሁን፡ “እደራ—ሳታገባ እንዳትኖር።” እርሰዋም... ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ምን እንደሚከሰት አላወቀችም። እናም የእግዚአብሔር መላእክቶች ሲሸከሟትት ውድ እጆቿን ይዤ ነበር።

237 ወደ ቤት ሄድኩኝ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር። በሌሊት ተኝቼ እና የሆነ ነገር ሰማሁ... እንደሚመስለኝ አንዳንድ ወረቀቶች ባስቀመጥንበት ሳጥን ውስጥ፡ ትንሽ አይጥ የገባች መሰሎኝ ነበር። እና በሩን በእግሬ ዘጋሁት፣ እና ልብሷን ከኋላ አንጠለጠልኩት፣ (እና በሬሳ ክፍል ውስጥ አስተኛኋት)። እና ትንሽ ቆይቶ አንድ ሰው ጠራኝ፣ “ቢሊ!” “ልጅህ ልትሞት ቀርባለች፡” አለኝ። ወንድም ፍራንክ ብሮይ ነበር።

“የኔ ልጅ? ” አልኩት፤

238 “አዎን፡ ሻሮን ሮዝ፡” አለኝ። “ዶክተርም በዚያ ነው፡ ‘ከእናቷ ወተት ስትጠባ፡ ቲዩበርክሎሲስ ማንጀይትስ ተላልፎባታል፡’” ብሏል። “እየሞተች ነው፡” አለኝ።

239 መኪና ውስጥ ገባሁ፣ ወደዚያ አመራሁ። ጣፋጯ ትንሽ ነገር፡ በዚያ አየኋት። እናም በፍጥነት ወደ ሆስፒታል ወሰዷት።

240 እሱን ለማየት ወጣሁ። ሳምም መጥቶ እንዲህ አለኝ፦ “ቢሊ፣ ወደዚያ ክፍል አትግባ፣ ስለ ቢሊ ፖል ማሰብ አለብህ።” “እሷ እየሞተች ናት፡” አለኝ

“ዶክ፡ ልጄን—ማየት አለብኝ፡” አልኩት።

241 እሱም፦ “አይ፡ መግባት አትችልም።” አለኝ፦ “ቢሊ፡ እሷ የማጅራት ገትር በሽታ ተይዛለች፡ አንተም ለቢሊ ፖል እንዳታስይዘው።”

242 እና እስኪወጣ ድረስ ጠበቅኩት። እሷን ስትሞት ቆሜ የማየት አቅም የለኝም፡ እናቷም በቀብር አስፈጻሚ ተቋም ውስጥ ተኝታለችና። እላችኋለሁ፡ የበደለኞች መንገድ ግን ሻካራ ናት። እና ሄጄ—በሩ ጋር ተደበቅኩ፡ ሳም እና ነርሷ ከወጡ በኋላ፡ ወደ ምድር ቤቱ ወረድኩ። አነስተኛ ሆስፒታል ነው። ገለልተኛ ስፍራ ላይ ነበረች፡ ትናንሽ አይኖቿ ላይ ዝምቦች አርፈው ነበር። ከአይኖቿ በላይም... ማን ነበር የሚሉት “የወባ ትንኝ አጎበር፡” ወይም ትንሽ መረብ አርገውላታል። እና በከባድ ህመም... ሆና ወፋፍራም እግሮቿን እና ትንንሽ እጆቿን፡ በዚያ ህመም ውስጥ፡ እንዲህ ወደ ላይ ወደታች ታደርጋቸዋለች። እና ተመለከትኳት፡ የምታምር የስምንት ወር አካባቢ፡ ቁንጅናዋ እስኪታይ ድረስ አድጋለች ።

243 እና እኔ ልመጣ ስል፡ እናቷ ግቢው ላይ በባለ-ሶስት እግር ላይ፡ እንደምታውቁት፡ ቁጭ ታደርጋት ነበር። እና የመኪናውን ጥሩምባ ሳጮህላት፡ እንደው፡ “ጉ-ጉ፣ ጉ-ጉ፣” እያለች ወደ እኔ ትመጣለች።

244 አሁን ግን ውዴ ተኝታ፡ እየሞተችብኝ ናት። ዝቅ ብዬ አየኋት፡ እና እንዲህ አልኳት፦ “ሻሪ፡ ዳዲን ታውቂዋለሽ? ታውቂዋለሽ ዳዲን፡ ሻሪዬ? ” እና

ስትመለከት... እንዳቸው የሚያምሩ ትናንሽ ሰማያዊ አይኖች እስኪሻገሩ ድረስ በጣም ተሠቃየች። ልቤን ከውስጤ ቀድጄ ባወጣኋት ተመኘሁ።

245 ተንበርክኬ፦ “ጌታ ሆይ፡ ምን በደልኩህ? በየጎዳናው ጥግ ወንጌልን አልሰበክሁምን? ማድረግ የምችለውን ሁሉ አድርጌያለሁ። በእኔ ላይ በደል አትቍጠርብኝ። እኔ ሰዎቹን ‘ቆሻሻ’ አላልኳቸውም። እነዚያን ሰዎች ‘ቆሻሻ’ ያለቻቸው ሴትየዋ ናት።” “ይህ ሁሉ በመሆኑ አዝናለሁ። ይቅር በለኝ። ልጄን አትውሰድብኝ፡” አልኩት። እና እየጸለይኩ ሳለሁ ጥቁር መሰሎ... እንደ አንሶላ ወይም እንደ ጨርቅ ሲወርድ አየሁ። እንዳልተቀበለኝም አወቅኩ።

246 ስለዚህ፡ በህይወቴ ከባዱ እና ፈታኝ ወቅት ይህ ነበር። ቀና ብዬ ሳያት፡ ሰይጣን ልቤ ውስጥ ሀሳብ ጨመረ... አወጣሁ አወረድኩና፦ “እንዴ፡ ይሄን ያህል በኃይል ሰብከህ፡ የኖርክለትን ኑሮ ሁሉ፣ አሁን ግን ወደ ገዛ ልጅህ ሲደርስ፡ ምነው አሳፈረህ? ”

247 “ትክክል ነው። ልጄን ማዳን ካልቻለ፣ እኔም አል... ” ብዬ፡ አቆምኩኝ። ምን—ምን ማድረግ እንዳለብኝ ግራ ተጋባሁ። ከዚያ በኋላ ግን፡ እንዲህ አልኩ፦ “ጌታ ሆይ፡ አንተ ለእኔ ሰጠሃት አሁንም አንተ ወሰድካት፡ የጌታ ስም ብሩክ ይሁን! ጨምረህ እኔን ብትወስድም፡ አሁንም እወድሃለሁ።”

248 እጄን፡ በላይዋ አደረግኩና፡ “ተባረኪ፡ የኔ ውድ አልኳት። ዳዲ ሊያሳድግሽ ይፈልግ ነበር፡ በሙሉ ልቤ እንዳሳድግሽ፡ ጌታ እንደምትወጂ አድርጌ ላሳድግሽ እወድ ነበር። የኔ ውድ፡ አሁን ግን መላእክት ሊወስዱሽ መጥተዋል። ዳዲ ግን ትንሿን አካልሽ ወስዶ ማሚ እቅፍ ውስጥ ያስተኛል። ከእሷ ጋር እቀብርሻለሁ። ከማማ ጋር ጠብቂኝ፡ አንድ ቀን ዳዲ መጥቶ ያገኝሻል።”

249 እናቷ በምትሞትበት ጊዜ፡ እንዲህህ አለች፡ መጨረሻ የተናገረችው፦ “ቢል፡ በአገልግሎት ማሳህ ላይ ቆይ፡” አለችኝ።

250 እኔም “እሺ እቆያለሁ... ” አልኳት፤ እሷም... እኔም፦ “እሱ እስኪመጣ ድረስ ማሳዬ ላይ ከጠበቅኩት፡ መጥቼ ልጆቹን አያለሁ። ካልሆነ ግን፡ ከጎንሽ እቀበራለሁ። አንቺም ሄደሽ በታላቁ በር ዘንድ በቀኝ በኩል ጠብቂኝ፣ ሌሎች ሁሉ ሲገቡ ስታያቸው፣ በዚያ ሆነሽ ያለሽን ኃይል ሁሉ ተጠቅመሽ ‘ቢል! ቢል! ቢል!’ ብለሽ ጥሪኝ። እኔም እዚያ አገኝሻለሁ አልኳት።” የሽኝት-ሰላምታ ሰማኋት። ዛሬ ሀያ አመት ገደማ አልፏል። እነሆ ዛሬም በማሳዬ አለሁ። ከሚስቴ ጋር ቀጠሮ አለን፡ ላገኛት እሄዳለሁ።

251 ህጻኗም በሞተች ጊዜ፡ ውሰድኳትና፡ በእናቷ እቅፍ አሰጥ አኖርኳት፣ ወደ መቃብር ሰፍራም ወሰድናቸው። እና ወንድም ስሚዝ፣ የቀብር ሥነ ሥርዓቱን የሰበከውን የሜቶዲስት ሰባኪ ሲሰብክ ሰማሁት፣ “አፈር ወደ አፈሩ፣ አቧራም ወደ አቧራው።” (እኔም “ልብ ደግሞ ወደ ልብ፡” ብዬ አሰብኩ።) በቃ ሄደች።

252 ከዚያ ብዙም ሳይቆይ፡ አንድ ቀን ጠዋት ቢሊን አመጣሁት። ገና ህጻን ልጅ ጨቅላ ነበር። ለእርሱም...

253 እሱ ከእኔ ጋር እኔም ከሱ ጋር የማንለያየው በዚህ ምክንያት ነው፡ እናት እና አባት (ሁለቱ) ሆኜ ነው ያሳደግኩት። ትንሿን ጡጦውን አዘጋጅለታለሁ። ሌሊት ወተቱን ማሞቅ የምንችልበት እሳት ስላልነበረን፣ በሰውነቴ ሙቀት ላብታውን ለመጠበቅ ከጎኔ በዚህ በኩል አስቀምጥለታለሁ።

254 እንደ ጓደኛሞች አብረን ኖረናል፡ ስለዚህ ከእለታት አንድ ቀን ማሳዬን ትቼ በምሄድበት ጊዜ ቃሉን ለእሱ አሰረክበዋለሁ፣ “አንተ ቀጥል፡ ቢሊ፡ ወደ ግራ ወደ ቀኝ አትበል።” እለዋለሁ። አንዳንድ ሰዎች እሱን ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ይዤ መዞሬ ይገርማቸዋል። ያለ እሱ አልችልም። አሁን ሚስት አግብቷል፡ “አብረኸው ሁን አትለየው፡” ብላ የተናገረችኝ ነገር ግን አሁንም ትዝ ይለኛል። እንደ ጓደኛሞች አንለያይም።

255 ጡጦውን ከብብቴ ስር አድርጌ፡ ከተማ ላይ ሸርሸር ስንወጣ፡ እሱም ሲያለቅስብኝ አስታውሳለሁ። አንድ ምሽት እኔ... እና እሱ በጓሮው ውስጥ ብቻችን ለሸርሸር ወጣን... (እሷ መጥታ ከያዘችው፡ ወድያው ታረጋጋዋለች፡ እኔ ግን... መቼ ሴት፡ ታውቃላችሁ።) እና ከጓሮው ጀርባ ካለው አሮጌ የዋርካ ዛፍ ወደ ኋላ እና ወደ ፊት እመላለሳለሁ። ማማዬ እያለ አለቀሰብኝ፡ እኔ እነኟት እናትህ ብዬ የማመጣለት ማማ አልነበረኝም። እንዲህ አንስቼ አቅፈውና፡ “ኦህ፡ የኔ ማር፡” እለዋለሁ። እለውና...

256 “ዳዲ፡ ማሚ የት ናት? ወደ መሬት ውስጥ አስገብተሃት ነው? ” ይለኛል፤

እኔም “አይደለም፡ የኔ ማር። እሷ ደህና ናት፡ ሰማይ ናት ያለችው፡” እለዋለሁ።

257 እና አንድ ቀን ከሰዓት፡ ሞትን እስክመኝ ድረስ፡ አንድ ነገር አለኝ። እያለቀሰ ቆየና፡ እና መሽቶ ነበር፡ **እንዲህ** አድርጌ በጀርባዬ አዝዬው፣ በትከሻዬ በኩል እንዲህ አሰሬው ከኋላ **እንዲህ** እጠበጥበዋለሁ። እና “ዳዲ፡ እባክህ ሄደህ ማሚን ወደዚህ አምጣት፡” አለኝ።

እንዲህ አልኩት፦ “ማማን ወደዚህ ማምጣት አልችልም፡ የኔ ማር። ኢየሱስ... ”

“ታዲያ ኢየሱስን፡ ማምዬን እንዲልክልኝ ንገረው። እኔ እፈልጋታለሁ፡” አለኝ።

258 እና እኔም “እሺ፡ የኔ ማር፡ አንድ ቀን እኔ... አንተ እና እኔ ሆነን ልናያት እንሄዳለን፡” አልኩት።

ቆም አደረገና፡ “ዳዲ!” አለኝ፤

እኔም “ወዬ? ” አልኩት፤

“ማሚዬን እዚያ ደመናው ላይ አያታለሁ፡” አለኝ።

259 ማይ፡ ነፍሰም አልቀረልኝም! ምንድነው፦ “ማይ! ‘እዚያ ደመና ላይ ማማን አየኋት።’” ራሴን ሰቼ ነበር። ልጁን **እንዲህ** አድርጌ ወደ ደረቴ እቅፍ አሰጠጋሁትና፡ እራሴን እንዲህ አቀርቅሬ ቀብሬ፡ መንገዴን ቀጠልኩ።

260 ቀናት አለፉ። ልረሳው አልቻልኩም። ለመስራት ሞከርኩ። ወደ ቤት መመለስ አልቻልኩም፡ ከእንግዲህ ቤት አይመሰልም። እና መቆየት ፈለግሁ። ከተቀደደው አሮጌ የቤት እቃ በቀር ምንም አልነበረንም፣ ለእኔ እና ለእሷ ለሁለታችን ግን ደስታችን ነበር። ቤታችን ነበር።

261 እና አንድ ቀን የመንግስት ሥራ አገልግሎት ውስጥ እየሰራሁ አስታውሳለሁ። እና አንድ ቀን በጥዋቱ፡ ወድቆ የተንተለጠለ፡ ሁለተኛው እስተላላፊ መሰመር ለመጠገን ሄድኩ። እና መሰቀለኛው ላይ ወጣሁ። (የህጻኗ ሞት

አልተዋጠልኝም ነበር። የሚስቴ መሞትዋስ ይሁን እሺ፡ የህጻኗ ሞት ግን፡ ገና'ኮ ጨቅላ ናት።) ላይ ወጥቼ፦ "እሩቅ በተራራው ማዶ፡ የማይመች መስቀል ቆሟል፡" የሚል ዝማሬ እየዘመርኩ ነበር። እና (እንደሚታወቀው) ቀዳሚው መሰመር ወደ ትራንስፎርመር ይፈስሳል ከዚያም ወደ ሁለተኛው መሰመር ይገባል። እኔም እዚያው ላይ ወጥቻለሁ። እዚያም ሆኜ ሳይ፡ ጸሐይ ከበስተኋላዬ መውጣት ጀምራለች። በዚያም፡ እጆቼን የዚያን—የተራራው መስቀል ምሳሌ አድርጌ ዘረጋኋቸው። "አዎን፡ ሐጥያቴ ነበር ያሰሰቀለው፡" ብዬ አሰብኩ።

262 እንዲህ አልኩ፦ "ሻሮን፡ የኔ ማር፡ ዳዲ አንቺን ማየት በኃይል ናፍቆታል፡ የኔ ማር። አንቺ ውዴ ትንሽ ነገር፡ ደግሜ በእጄ ውስጥ እንዴት ልይዘሽ ወደድሁ።" አጠገቤ አቀረብኩት። ሳምንታት አልፏል። የጎማ ጓንቴን አወለቅሁት። ሁለት ሺ-ሶስት መቶ ያህል ቮልት በጎኔ እያለፈ ነው። የጎማ ጓንቴን አወለቅሁት። "አምላክ ሆይ፡ እኔ አልችልም፡ ፋይዳ ቢስ ነኝ፡" አልኩ። "ሻራ፡ እና ማሚ ግን፡ ዳዲ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ያያችኋል።" በዚያ ሁለት ሺ-ሶስት መቶው ላይ፡ እጆቼን ለማድረግ፡ ጓንቶቼን ማውጣት ጀመርኩ። በአንዴ ይሰባብራቿል... እንዴ፡ የደም ሽታ አያስቀርላችሁም። እና እኔ—እኔ—ግን ጓንቱን ባወላለቅኩ ጊዜ፡ አንድ ነገር ሆነ። ወደ ቀልቤ ሰመለሰ ግን፡ እጆቼን ወደላይ፡ **እንዲህ** ወደ ፊቴ አድርጌ፡ መሬት ላይ ቁጭ ብዬ እያለቀስኩ እርሴን አገኘሁት። በእግዚአብሔር ጸጋ ባይሆን ኖሮ፣ እርግጠኛ ነኝ፡ ዛሬ እዚህ የፈውስ አገልግሎት አላደርግም ነበር። ሰጦታውን የጠበቀው እሱ እንጂ፡ እኔ አይደለሁም።

263 ተውኩትና፡ መሳርያዎቼ ሰበሰብኩ። ወደ ቤት ተመልሰኩ። ፊቴን አዙሬ "ወደ ቤቴ እሄዳለሁ፡" አልኩ።

264 ወደ ቤት ሰገባ፡ ይበርዳል፡ እና ገብቼ፡ ፖስታ አገኛቼ አነሳሁት። አንድ ጠባብ ክፍል ነበረችን፡ እኔ ትንሿ አልጋ ላይ እተኛለሁ፡ ያረጀች ምድጃም አለች፡ ውርጩ ይገባል። ፖስታውን ከፍቼ ፖስታውን ሳየው፡ የመጀመርያው ነገር ያየሁት ለገና ሰጦታዋ የተጠራቀመላት፡ ሰማንያ ሳንቲም ነበር፡ "ለሚስ ሻሮን ሮዝ ብራንሃም።" ይላል እና፡ አሁንም መጣ።

265 ደን ጥበቃ ሰራተኛም ሰለነበርኩ። እጄን ሰድጄ ጠመንጃ፡ ሽጉጥ፡ ከሰገባው አወጣሁ። "ጌታ ሆይ፡ እኔ—ከዚህ በላይ አልችልም፡ እኔ—እሞታለሁ። እኔ—በቂ ተሰቃይቻለሁ፡" አልኩ። ካርታውን ወደ መሳርያው ሰክቼ፡ ጨለማው ክፍል ውሰጥ አልጋ ላይ ተንበርክኬ፡ ጭንቅላቴ ላይ ወደርኩት። "በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፡ ሰምህ ይቀደስ። መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ ትሁን፣" ብዬ፤ ቃታውን፡ በኃይል ጫን አድርጌ ሰመታው፡ "ፈቃድህ በሰማይ በምድር ትሁን። የእለት እንጀራችንን ሰጠን ዛሬ፡" አልኩ። አሁንም አልተኩሰም አለ!

266 "አምላክ ሆይ፡ አሁንም እየሰባበርከኝ ነውን? ምን አደረግሁ? እንድሞት እንኳ አትፈቅድልኛምን፡" ብዬ አሰብኩ። እናም ጠመንጃውን ወረወርኩት፣ ሄዶ በክፍሉ ውሰጥ አምቧረቀ። "አምላኬ ሆይ፡ ሞቼ ከዚህ ሁሉ እንዴት አልገላገልም? በቃ ከዚህ በላይ መሄድ አልችልም። የሆነ ነገር አድርገኝ፡" አልኩት። እናም ተደፋሁና እዚያ ትንሸዬ፡ አሮጌ አልጋዬ ላይ ማልቀስ ጀመርኩ።

267 ከዚያ በኋላ ምን ኣንደተፈጠረ አላውቅም። ተኛቼ መሆን አለበት።

268 ወደ ምዕራብ መሄድ ሁሌም እመኛለሁ። እነዚያን ኮፍያዎች ማጥለቅ ደስ ይለኛል። አባቴም በወጣትነቱ ፈረሶችን አሰልጣኝ ነበር፣ እና ሁልጊዜም እነዚያን ኮፍያዎች እፈልግ ነበር። ትናንትና ወንድም ዴሞስ ሻካሪያን አንድ ገዝቶልኛል፣ እንዲህ የምዕራብ አይነቱ ኮፍያ፡ (ከኖረኝ) ይህ የመጀመርያ ጊዜዬ ነው።

269 እና ለጥ ባለ ቤዳ በኩል እየተጓዝኩ እንዲህ ብዬ፣ "የተሰበረ የጋሪ እግር ሰረገላው ላይ፡ 'ይሸጣል' የሚል ምልክት በግጦሽ ሜዳ ላይ፡" እያልኩ የምዘምር ይመስለኛል። እና እየሄድኩ ሳለሁ፡ አሮጌ ግጦሽ ላይ፡ እግሩ የተሰበረ፡ የተሸፈነ ፉርጎ ያለው ሰረገላ አስተዋልሁ። በእርግጥም፡ የተሰበረ ቤተሰቤን የሚወክል ነበር። እየተጠጋሁ ስቀርብ፡ በጣም ውብ የሆነች፡ የሀያ አመት፡ ወጣት ሴት—ቆማ አየሁ፣ ነጭ የለበሰች፡ ነጭ የሚፈስ ፀጉር እና ሰማያዊ ዓይኖች ያላት ሴት አየሁ። አየኋትና፦ "ጤና ይስጥልኝ? " ብያት፡ አለፍኩ።

"እንዴት ነህ፡ ዳድ፡" አለችኝ።

270 ወደ ኋላዬ ዞር ብዬ፦ "ዳድ? " አልኳት፤ "እንዴት፡" አልኳት፡ "እንዴት፡ እመቤት፡ እኔን የምታክዪ ሴት... እንዴት አባትሽ እሆናለሁ? "

271 "ዳዲ፡ የት እንዳለህ ስላላወቅክ'ኮ ነው፡" አለችኝ።

"ምን ማለትሽ ነው? " ብዬ ጠየቅኳት፤

272 "ይህ ገነት ነው፡" አለችኝ። "በምድር እያለሁ ትንሿ ልጅህ ሻሮን ነበርኩ፡" አለችኝ።

"እንዴ፡" "የኔ ማር፡ ህጻን ልጅ ነበርሽ'ኮ፡" አልኳት።

273 "ዳዲ፡ ህጻናት ወደዚህ ሲመጡ ህጻናት አይደሉም፡ ዘለአለማውያን ናቸው። አያረጁም አያድጉም፡" አለችኝ።

274 "ይገርማል፡ ሻሮን፡ የኔ ማር፡ አንቺ—አሁን ዉብ፡ ወጣት ሴት ሆነሻል፡" አልኳት።

"ማማ እየጠበቀችህ ነው፡" አለችኝ።

"የት? " አልኳት፤

"በአዲሱ ቤትህ ጋር፡" አለችኝ፤

275 እኔም "አዲስ ቤት? " አልኳት፤ የብራንሃም ልጆች ቤት የላቸውም፡ ከርታታ፡ ድሆች ናቸው... "እንጃ፡ ቤት ኖሮኝ አያውቅም፡ የኔ ማር፡" አልኳት።

276 "እዚህ ግን የራስህ ቤት አለህ፡ አባቴ፡" አለችኝ። እንደ ሕፃን መሆን ፈልጌ አይደለም፡ ነገር ግን በጣም እውነት ነው። [ወንድም ብራንሃም አለቀሰ—አርታዒ።] ስለሱ ማሰብ ሰጀምር፡ ሁሉም እንደገና መጣብኝ። በዚያ ማዶ ቤት እንዳለኝ እውቃለሁ፡ አንድ ቀን እሄዳለሁ። "እዚህ ግን የራስህ ቤት አለህ፡ አባቴ፡" አለችኝ። "ወንድሜ ቢሊ ፖል፡ የት አለ? " ብላ ጠየቀችኝ፤

277 "ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ ከነ ወይዘሮ/ ብሮይ ጋር፡ ትቼዋለሁ፡" አልኳት።

"እናቴ ልታይህ ትፈልጋለች፡" አለችኝ።

278 እኔም ዘወር ብዬ አየሁ፡ እነሆም ታላላቅ ቤተ መንግሥቶች አየሁ፡ የእግዚአብሔርም ክብር በዙሪያቸው ወጣ። “ቤቴ፡ ቆንጆዋ ቤቴ፡” የሚሉ የመላእክት ኳየር ሲዘምሩ ሰማሁ። ረጅም ደረጃዋችን፡ ባለኝ አቅም ሁሉ በሩጫ መውጣት ጀመርኩ። እና በሩ ላይ ሰደርስ፡ ነጭ ልብስ የለበሰች፡ ረጅም፡ ጥቁር ፀጉር፡ ወገቧ ላይ የወረደ፡ ቆማለች። ከስራም ሆነ ከሌላ ነገር ደክሜ ወደ ቤት ስመለስ ሁሌም እንደምታደርገው እጆቿን አነሳች። እጆቿን ያዝኳት እና እንዲህ አልኳት፡ “ውዴ፣ ሳሮንን አየኋት።” “ቆንጆ ልጅ፡ ሆና የለም’ዴ? ” አልኳት፤

279 “አዎን፡ ቢል፡” አለችኝ። “ቢል፡” አለችኝ። እጆቿን ትከሻዬ ላይ ጣል አርጋ፡ ትከሻዬ ላይ አረገችና፡ (እንዲህም አለችኝ) መታ መታ ማድረግ ጀመረችና፣ “ስለ እኔ እና ስለ ሻሮን መጨነቅ አቁም።”

“ማር፡ አልቻልኩትም፡” አልኳት።

280 “አሁን’ኮ እኔ እና ሻሮን ከአንተ ይልቅ በተሻለ ሰፍራ አለን፡” አለችኝ። “ከአሁን በኋላ ስለ እኛ አትጨነቅ። ቃል ትገባልኛለህ? ” አለችኝ፤

281 እኔም አልኳት፦ “ሆፕ፡” አልኳት፦ “አንቺ እና ሻሮን እጅግ ናፍቃችሁኛል፡ ቢሊም አንቺን ፍለጋ በየቀኑ ማልቀስ ብቻ ነው።” “ስለ እሱ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም።” አልኳት።

282 እርሰዋም፦ “ደህና ይሆናል፣ ቢል።” ብቻ “ከእንግዲህ እንደማትጨነቅ ቃል ግባልኝ፡” አለችኝ። “አትቀመጥም? ” አለችኝና፤ እና ዞር ብዬ ሳይ አንድ ትልቅ ወንበር ተዘጋጅቶ አየሁ።

283 ወንበር ለመግዛት አሰቤ እንደነበርኩ ትዝ አለኝ። አሁን፡ በመጨረሻ። አንድ ጊዜ ወንበር ለመግዛት ሞክሬ ነበር። ቁርሳችን የምንበላባቸው ተራ የተለመዱ—የእንጨት እግር ወንበሮች ብቻ ነበሩን። መጠቀም የነበረብን ብቸኛ ወንበራችን ናቸው። እና ወገባችሁን የምታስደግፉባቸው አይነት ወንበሮች አንዱን ለመግዛት በቅተን ነበር፡ እንደ... ቀላል-ማረፍያ ወንበሮች ናቸው አሁን አላስታውሳቸውም። ዋጋው አሰራ ሰባት ዶላር ነበር፡ ሶስት ዶላር ቅድመ ክፍያ በማድረግ በየሳምንቱ አንድ ዶላር የሚፈል ነበር። እና አንድ ገዛን። እና፡ ኦህ፡ አንድ ቀን ሰራ ውዬ፡ በየጎዳናው ወይም በየሰፍራው እሰከ እኩለ ሌሊት ድረስ ሰሰብክ አመሻለሁ... ወደ ቤት መጣሁ።

284 አንድ ቀን ግን—መክፈል የምንችልበት አቅም አጣን። አልቻልንም፡ እና ቀን በቀን ተደራረበ፡ በመጨረሻም መጡና ወንበሬን ይዘውብኝ ሄዱ። የዚያን ቀን ማታ፡ በህይወቴ አልረሳትም፡ ቼሪ ፓይ ጋግራ ጠበቀችኝ። ምስኪን ፍቅር ነገር፡ ያዝናል—ብላ—ሰላሰበች ነው። እና ከእራት በኋላ “ዛሬ ማታ ምን ጥሩ ነገር አግኝተሽ ነው ማር? ” ብዬ ጠየቅኳት፤

285 እንዲህ አለችኝ፦ “አይ፡ ዛሬ ልጆቹ ሰፈር ውሰጥ አሳ የምታጠምድባቸው ነፍሳት ቆፍረው እንዲያወጡልህ ልኬአቸው ነበር። ወደ ወንዝ ወርደን ጥቂት ጊዜ አሳ ማጥመድ ያለብን አይመሰልህም? ”

እኔም፦ “አዎ፡ ግን... ”

286 እና ማልቀስ ጀመረች። የሆነ ችግር እንዳለ ገባኝ። ቀድመው ማስጠንቀቂያ ልከውብን ስለነበር መረጃው ነበረኝ። እና ያንን ዶላር በሳምንት መክፈል

አልቻልነም። አልቻልንም፡ አልሆነም… አቅም አልነበረንም። እጇቿን ታቀፈችኝ፡ እና ወደ በሩ ሄድኩኝ እና ወንበሬ ተወሰዷል።

እና ያንን አስታወሰችኝ፡ "ቢል፡ ያቺ ወንበር ትዝ ትልሃለች? " አለችኝ፤

"አዎን፡ የኔ ማር፡ አስታውሳለሁ፡" አልኳት።

"እያሰብክበት የነበረው ነገር ነው አይደል? " አለች፤

"አዎን።"

287 "ይሄን እንኳ፡ ተከፍሎበታልና፡ አይወሰዱትም፡" አለችኝ። "አንድ ደቂቃ ቁጭ በልና፣ ላናግርህ እፈልጋለሁ፡" አለችኝ።

"ማር ምንድነው፡ ይህ አልገባኝም፡" አልኳት።

288 እርሰዋም፦ "ቢሊ፣ ቃል ግባልኝ፣ አሁን ትመለሳለህ። ከእንግዲህ እንደማትጨነቅ ቃል ግባልኝ፡" አለችኝ። "እንደማትጨነቅ ቃል ግባልኝ፡" አለችኝ።

"ይህን ማድረግ አልችልም፡ ሆፕ፡" አልኳት።

289 እና ልክ እንደተመለሰኩ፡ ክፍል ውስጥ ጨለማ ነበር። ዙርያዬን አየሁ፡ እና እጇቿ አቅፈውኝ እናዳሉ አወቅሁ። "ሆፕ፡ እዚህ ክፍል ውስጥ ነሽ? " ጠየቅኳት፤

290 መታ መታ አደረገችኝ። "ቃል ትገባልኛለህ፡ ቢል? እንደማታሰብ… እንደማትጨነቅ ቃል ግባልኝ፡" አለችኝ።

እኔም "ቃል እገባለሁ፡" አልኳት።

291 ሁለት ሶስት ጊዜ መታ መታ አርጋኝ፡ ጠፋች። ተነሳሁ እና መብራቱን አበራሁ፡ ሁሉንም ቦታ ተመለከትኩ፡ እሷ ግን ከክፍሉ ወጥታለች። ጠፍታለች። በርግጥ አልጠፋችም፡ ህያው ናት። ክርስትያን ናትና።

292 እኔና ቢሊ ለእናቱ እና ለእህቱ ትንሽ አበባ ይዘን ከተወሰነ ጊዜ በፊት ወደዚህ መቃብር ሄድን፣ የፋሲካ ማለዳ ነበር፡ እና ቆምን። እና ህጻኑ፦ "ዳዲ፡ እናቴ እዚህ ውስጥ ናት፡" ብሎ ማልቀስ ጀመረ።

293 እኔም፦ "አይደለችም፡ የኔ ማር። አይደለችም፡ እዚህ ውስጥ አይደለችም። እህትህም እዚህ አይደለችም። እዚህ የተዘጋ መቃብር አለን፡ በባሕር ማዶ ግን ኢየሱስ የተነሳበት መቃብራችን የተከፈተ ነው። እና አንድ ቀን ይመጣል፡ ማሚን እና እህትህን ይዟቸው ይመጣል።"

294 ወዳጆቼ ሆይ፡ እኔ ዛሬ በሰልፍ አውድማዬ እገኛለሁ። ከዚህ—በላይ ለመናገር አቅም የለኝም። እ… [ወንድም ብራንሃም አለቀሰ—አርታዒ።] ጌታ ይባርካችሁ። ለጥቂት ደቂቃዎች አንገቶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

295 ጌታ ሆይ! ብዙ ጊዜ፡ እርግጠኛ ነኝ፡ ጌታ ሆይ፡ እነዚህ ነገሮች እንዲህ በቀላሉ ሲመጡ፡ ሰዎች ይህን አይገባቸውም። ነገር ግን ኢየሱስ የሚመጣበት እና እነዚህ ሁሉ ሀዘኖች የሚወገዱበት ታላቅ ቀን ይመጣል። የሰማይ አባት ሆይ፡ መዘጋጀት እንድንችል እንድትረዳን፡ እጸልያለሁ።

296 የእኔም ያኔ በዚያ ቀን ጉንጯን ሰሜ፡ በዚያን ቀን እንገናኛለን፡ ብዬ ቃል ገብቻለሁና። በሩ ላይ እንደምትቆም፡ ስሜን ጮኸ ብላ እንደምትጠራኝ

እምናለሁ። ጌታ ሆይ፡ ከዚያ በኋላ ለገባሁት ቃል በመላው ዓለም፣ በተለያዩ ሰፍራዎች፣ ወንጌልን ለማዳረስ፡ ታምኜ ቆይቻለሁ። አሁን አርጅቼ፣ ደክሞኛል፣ ጨርሻለሁ። ከእነዚህ ቀናት አንዱ ይህን መጽሐፍ ቅዱስ ለመጨረሻ ጊዜ እዘጋለሁ። አሁንም፡ አምላክ ሆይ፡ ለቃሌ ታማኝ አርገኝ። ጌታ ሆይ፡ ጸጋህን በህይወቴ አብዛ። ከዚህ በላይ ላለው ነገር ልኑር እንጂ፡ የዚህን ህይወት ነገር እንዳላይ እርዳኝ። ቅን እንድሆን አግዘኝ። ጌታ ሆይ፡ የኔ ክርስቶስ በዚያ ሁሉ ሰቃይ አልፎ ሳለ፡ ሌሎቹም እንደሱ ዓይነት፡ በመከራ ሞተዋልና። እኔን የአበባ አልጋ ይነጠፍልኝ በፍጹም አልልም። ይቅለልልኝ አልልም። ጌታ ሆይ፡ ብቻ ቅን፡ እና ታማኝ ልሁን። ወደ አንተ እንድመራቸው የሰው መውደድ ሰጠኝ። ሁሉም ነገር አልፎ አንድ ቀን በለምለም ዛፎች ስር በተሰበሰብን ጊዜ፡ የአንገሉስ ቴምፕል ሰዎች እና ሌሎችን ሁሉ እንዳሳያቸው፡ እጆቿን ይዤ መዞር እናፍቃለሁ። ያኔ ድንቅ ጊዜ ይሆናል።

297 በእያንዳንዳችን ላይ ምህረትህ እንዲያርፍ እጸልያለሁ። እዚህ ያሉት፣ ጌታ ሆይ፣ ላያውቁህም ይችላሉ። ምናልባትም ቤተሰቦቻቸው ከአድማስ ማዶ የተለዩባቸው ሊኖሩ ይችላሉ። ጌታ ሆይ፡ ቃላቸውን በፍጹም ያልፈጸሙ ከሆኑ፡ አሁን እንዲፈጽሙ እርዳቸው።

298 እንገታችንን ደፍተን፣ ዛሬ ከሰአት በኋላ በዚህ ትልቅ አዳራሽ ውስጥ ስንቶቻችሁ ናችሁ፦ "ወንድም ብራንሃም፡ እኔም፡ ቤተሰቦቼን ማግኘት እፈልጋለሁ። እ—እኔ—እኔም ጥቂት ቤተሰቦቼ ከአድማስ ማዶ አሉ የምትሉኝ ስንቶች ናቸሁ"? ምናልባት እንገናኛለን ብላችሁ ቃል የገባችሁላቸው፡ ምናልባት እናታችሁ በመቃብሩ ላይ "ደህና-ሁኚ" ያላችኋት፣ ታናሽ እህታችሁን፡ ወይም ወላጅ አባታችሁን ወይም ሌሎችን፡ በመቃብር ላይ "ደህና-ሁን፡" እንገናኛለን ያላችኋቸው፡ ነገር ግን ገና ያንን ዝግጅት ያላደረጋችሁ። ይሄን ለማድረግ አሁን ጥሩ ጊዜ አይመስላችሁምን?

299 እንዲህ መሆኔ ይቅርታ አርጉልኝ። ግን፡ ኦህ፡ ማይ፡ ወዳጆቼ፡ እናንተ አልገባችሁም። መሰዋዕቱ— አልገባችሁም! የህይወት ታሪክ ቦታ፡ በፍጹም፡ አይደለም።

300 አሁን ስንቶች ተነስታችሁ ለጸሎት ወደዚህ መምጣት ትፈልጋላችሁ፡ "የምወዳቸውን ሰዎች ማግኘት እፈልጋለሁ"? የምትሉ፤ በጉባኤው ቁሙ እና ወደፊት ውጡ። ትታዘዛላችሁን? ያንን ዝግጅት ያላደረገ ማንም ሰው እዚህ ካላችሁ። ጌታ ይባርክህ፡ ጋሼ። አንድ ጥቁር ሽማግሌ ሰው እየወጣ እየዋለሁ፡ ሌሎችም እየመጡ ነው። እናንተ እዚያ በበረንዳው ላይ ያላችሁ፡ ተላለፉ፡ እና ወደዚህ መድረክ ቅረቡ። ወይም እናንተ በጸሎት ቃል መታሰብ የምትፈልጉ ሁላችሁ፡ ባላችሁበት ቁሙ። አዎን እንደሱ። በእግሮቻችሁ ቁሙ። በጣም ጥሩ። እናንተ፡ በያላችሁበት፡ እየቆማችሁ፡ "በዚያ አድማስ ማዶ አባቴ አለ፣ እናቴ ወይም ዘመዶቼ በዚያ ማዶ አሉ የምትሉ። ላያቸው እናፍቃለሁ። በሰላም እንዳገኛቸው እፈልጋለሁ።" በጉባኤው በያላችሁበት፡ በእግሮቻችሁ ብቻ ቁሙ፡ ተነሡ ብቻ። በእግሮቻችሁ ቁሙና፦ "መቀበል እፈልጋለሁ፡" በሉ።

301 እግዚአብሔር ይባርክሽ እመቤት። እዚያ ከኋላ እግዚአብሔር ይባርክህ። እና እዚያ ጋርም ብሩካን ሁኑ። እዚህ ጋር ጌታ ይባርኮት፡ ጋሼ። ትክክል ነው። እዚያ ጋር በረንዳው ላይ፡ ጌታ ይባርካችሁ። በየሰፍራው፡ በየትኛውም

ቦታ ያላችሁ ሁላችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ እዚህ በልባችን ውስጥ ሊ——ሊ——ሊሰባብረን ተዘጋጅቶ ሳለ፡ አሁን ለጸሎት ቃል በእግሮቻችሁ ቁሙ።

302 ዛሬ ቤተክርስትያን የሚያስፈልጋት ነገር ታውቃላችሁ መሰባበር ነው። ወደ ሸክላው ሰሪ መውረድ አለብን። በተቤታችን የሰራነው ግትር ቲኦሎጂያችን እንዳንዴ እርባና ቢስ ነው። እኛ የሚያስፈልገን የጥንት-አይነት የልብ ንስሓ፡ ለእግዚአብሄር ምቹዎች ሆነን፡ መሰባበር ነው። ለመቆም የተዘጋጀ ይህ ብቻ ነው?

እንግዲያውስ ለጸሎት አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

303 እኛን ሁላችንም፡ በእምነት በኩል መጽደቃችን እናምን ዘንድ... ኢየሱስን ዳግም ከሙታን መካከል ያነሳኸው፡ ጌታ ሆይ። አንተን ለመቀብል በእግሮቻቸው ስለቆሙት ሁሉ፡ ጌታ ሆይ፡ እጸልያለሁ፡ ይቅርታ ታደርግላቸው ዘንድ እጸልያለሁ። እና፣ ጌታ ሆይ፣ እንደ እዳኛቸው፣ ንጉስ እና አፍቃሪ አድርገው እንዲቀበሉህ እጸልያለሁ፣ እና ምናልባት እናት ወይም አባት ወይም አንድ ሰው ከአድማስ ማዶ ይኖራቸው ይሆናል። እርግጠኛ የምንሆንበት፣ አዳኝ አግኝተዋል። ኃጢአታቸው ይሰረይላቸው፣ በደላቸውም ሁሉ ይደመሰስ። ነፍሳቸው በበጉ ደም ታጥባ፡ ከዚህ በኋላ በሰላም ትኑር።

304 አንድ ቀን ሁሉም ነገር አልፎ፡ እንደማይበታተን ቤተሰብ፡ ሆነን ወዲያ ማዶ፣ የሚጠብቁንን ቤተሰቦቻችንን ማግነት እንድንችል በቤትህ መሰብሰብ ይሁንልን። እነዚህንም፡ ለአንተ አደራ ሰጠናቸው፡ እነዚህን “ልባቸው በእርሱ ዘንድ የጠበቁትን ሁሉ በፍጹም ሰላም ጠብቃቸው።” ለአንተ አደራ፡ አሳልፈን፡ እንደሰጠናቸው ጌታ ሆይ ሰማን። በልጅህ በጌታ በኢየሱስ ሰም። ኣሜን።

305 እግዚአብሄር ይባርካችሁ። አገልጋዮች ያላችሁበትን አይተዋል፡ በትንሽ ደቂቃ ወደያላችሁበት ይመጣሉ።

306 እና አሁን የጸሎት ካርዶችን ለሚቀበሉ ሰዎች። ቢሊ፡ ጂን እና ሊዮ የት አሉ፡ ከኋላ ናቸው? የጸሎት ካርዶችን በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ለመስጠት ተዘጋጅተዋል። ወንድማችን ጉባኤውን በጸሎት ያሰናብታል፣ የጸሎት ካርዶቹም ይሰጣሉ። ለታመሙ ለመጸለይ ከአፍታ በኋላ፡ ወደዚህ እንመለሳለን። እሺ፡ ወንድሜ።

**የሕይወት ታሪኬ** AMH59-0419A

(My Life Story)

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ሚያዝያ 19፡ 1959፡ እሁድ ከሰዓት፡ ዩ.ኤስ.ኤ. ሎስ ኤንጀልስ፡ ካሊፎርኒያ ከሚገኝ ኤንግለስ ቤተመቅደስ፡ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይስ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግስ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈለጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org